ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ) ተሰብስቦ በአንድ ተቀናበረ

ቅፅ - ፰



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.215383

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡.....1. ወ/ሮ አርሴማ ኤልያ- } ጠበቃ አበበ ዘበነ ቀርበዋል፡፡
2. የርገን ቫንድራ ቬድ }

ተጠሪ፡.....የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የጉድፈቻ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር አመልካቾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ በመ.ቁ.274588 በ22/11/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ 1ኛ አመልካች እና 2ኛ አመልካች ባልና ሚስት ሲሆኑ፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች የማትወለደውን ህጻን ልጃቸውን ህጋዊ ባለቤታቸው ለሆነው ለ2ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ለመስጠት ያደረጉትን ስምምነት እንዲጸድቅላቸዉ ዳኝነት ጠይቀል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ አመልካች (ሚስት) ጉዲፈቻ ሰጪ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ስትሆን 2ኛ አመልካች (ባል) ጉዲፈቻ ተቀባይ የውጪ አገር ዜጋ መሆናቸዉ ከቀረበዉ አቤቱታ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች የማትወልዳትን ልጅ በጉዲፈቻ ዉል ስምምነት ለ2ኛ አመልካች ለመስጠት የተፈራረሙ ቢሆንም ጉዲፈቻ ለዉጭ አገር ዜጋ በአዋጅ ቁ.1070/2010 መሰረት የተከለከለ መሆኑ የቀረበዉን የጉዲፈቻ ውል ስምምነት ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጎታል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች ጥቅምት 16 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ጉዲፈቻ ሰጪ ኢትዮጵያዊ የሆኑና ጉዲፈቻ ተቀባይ የደች ዜግነት ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ጋብቻቸውን በመፈፀም ሕጋዊ ባልና ሚስት ሆነን ኢትዮጵያ ውስጥ ልጅ ወልደው እየኖርን ያለን በመሆኑ፤ ጉዲፈቻ ተሰጪ ሕጻንም ከእናቷ ጋርና ከእንጀራ አባቷ ጋር እየኖረች በስሙም እየተጠራች አብረው የሚኖሩ በመሆኑ፤ ጉዲፈቻዉም አባትነትን እንጂ እናትነትን በተመለከተ ወላጅ እናቷን የማይነካ በመሆኑ፤ ጉዲፈቻዉ ከዉጭ ዜጋዉ ከተወለደዉ ወንድሟ ጋር እኩል በማድረግ በጉዲፈቻ ተደራጊዋ ህጻን አእምሮ ሊፈጠር የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስቀረት ለህጻኗ ጥቅም የታሰበ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የጉዲፈቻ ዉል ስምምነቱን በልዩ ሁኔታ በማየት ከተለያዩ ሕጎችና አዋጆች አንጻር እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ዓላማና መንፈስ አንጻር በመረዳት መወሰንን ሲገባቸዉ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የጉዲፈቻ ዉሉን በመከልከል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ አመልካቾች ያደረግነዉ የጉዲፈቻ ዉል ስምምነት እንዲጸድቅልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ ጉዲፈቻ ሰጪ እና ጉዲፈቻ ተቀባይ ባልና ሚስት መሆናቸው ከመረጋገጡ አንፃር ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት አዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ይህን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉ ጉዳይ ሲታይ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊት ስትሆን፣ 2ኛ አመልካች የዳች የዉጭ አገር ዜጋ ሲሆን፣ ግራ ቀኞቹዉ ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመዉ አንድ ልጅ ወልደዉ አብረዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት መሆናቸዉ፤ እንዲሁም ሕጻን አቪያ ቫንድራ ቬድ 1ኛ አመልካች የወለደችና ከ2ኛ አመልካች ያልተወለደች ልጅ ከግራ ቀኙና ከጋራ ልጃቸዉ ጋር በአንድ ቤት እየኖረች እና አሁንም በ2ኛ አመልካች ስም የሚትጠራ መሆንዋን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካቾች በትዳር አብረዉ እየኖር ያሉ በመሆናቸዉ፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር ያልወለዱትን ልጅ 2ኛ አመልካች የልጅቷ እንጀራ አባት በመሆኑ፣ በጋራ ከወለዱትና ካላቸዉ ልጅ ጋር ይህችን ልጅ እኩል ለማሳደግ ሲባል 1ኛ አመልካች የልጅቷ እናትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 2ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ስምምነት መሰረት የልጅቷ የጉዲፈቻ

አባት ለመሆን፣ የጉዲፈቻ ስምምነት ፈርመዉ፣ ይህም ስምምነት በፍ/ቤት እንዲጸድቅላቸዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ይህ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አግባብነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ናቸዉ ወይስ ይህን የተሻሻለዉን የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በምዕራፍ አሥር ከአንቀጽ 180–196 ድንጋጌዎች ሥር ስለጉዲፈቻ የሚመለከቱ መሆናቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ በአንድ ሰዉና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 180 ሥር ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ ያገባ ሰዉ የሚያደርገዉን የጉዲፈቻ ስምምነት በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ 187 ሥር በተደነገዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የጉዲፈቻ አድራጊዉ ያገባ በሚሆንበት ጊዜ፣ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸዉ የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ እንደማይቻል የሚደነግግ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉዲፈቻዉ ልጅ፣ የጉዲፈቻዉ ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈጻሚነት እንደማይኖረዉ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ባልና ሚስት በጋራ የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ የሌላ ሰዉ ልጅን በጉዲፈቻ ማሳደረግ እንደሚችሉ፣ እንዲሁም በጋራ ያልወለዱትን የባል ወይም የሚስት የሆነዉን ልጅ ባል ወይም ሚስት በጉዲፈቻ ስምምነት ማሳደግ እንደሚችሉ ነዉ፡፡ የጉዲፈቻዉ ልጅ የባል ወይም የሚስት በሆነ ጊዜ ሌላኛዉ ተጋቢ በጉዲፈቻ ስምምነት የአንደኛዉን ልጅ በጉዲፈቻ ስምምነት ማሳደግ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ ይህ ድንጋጌ የባል ወይም የሚስት የዜግነት ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ ያስቀመጠዉ ክልከላ የለም፡፡ ነገር ግን ባል ወይም ሚስት የኢትዮጵያ ዜጎች ብቻ መሆን አለባቸዉ፤ ከመካከላቸዉ አንዳቸዉ የዉጭ አገር ዜጋ ሊሆን አይችልም የሚያስብል ሁኔታ የለም፡፡ ምክንያቱም ባል ወይም ሚስት ከሁለቱ አንዳቸዉ የዉጭ ዜጋ ከሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ ወይም በዉጭ አገር ጋብቻቸዉን በሕግ አግባብ ፈጽመዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ መኖር አይችሉም በማለት በሕግ የተጣለ ግልጽ ክልከላ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሻሻለዉን የቤተሰብ ሕግ ለማሻሻል አዋጅ ቁጥር 1070/2010 ወጥቶ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 መሰረት የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193 የተሻረ መሆኑን፣ የአዋጁ አንቀጽ 194 (3፣ መ) ተሰርዞ ነባሩ ፊደል ተራ (ሠ) ፊደል ተራ (መ) ሆኖ መሸጋሸጉን፣ እና የአዋጁ አንቀጽ 194 (4) መሰረዙን ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚመለከቱት በዉጭ አገር ዜጋ የሚደረግ የጉዲፈቻ ጉዳይ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193 ድንጋጌ የጉዲፈቻ አድራጊዉ የዉጭ አገር ዜጋ በሚሆንበት ጊዜ የጉዲፈቻ ስምምነቱ ተቀባይነት ሊኖረዉ የሚችልበትን አግባብ የሚያመለክተዉ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 (1) ድንጋጌ መሻሩን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 194 (3፣ መ) እና (4) ድንጋጌዎች የጉዲፈቻ አድራጊዉ የዉጭ ዜጋ የሚመለከቱ በመሆናቸዉ በአዋጅ ቁጥር

1070/2010 አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሰረዛቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የጉዲፈቻ አድራጊዉ የዉጭ አገር ዜጋ የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ አንድ ኢትዮጵያዊ/ዊት ልጅን በጉዲፈቻ መዉሰድ እንደማይቻል ያሳያል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች እና ተጠሪ ባልና ሚስት ሆነዉ፣ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊት ዜጋ ሲትሆን፣ 2ኛ አመልካች የዳች አገር ዜጋ ሲሆን፣ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ያልወለደችዉን ልጅ፣ የእርሷ እናትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 2ኛ አመልካች የልጅቷ የጉዲፈቻ አባት እንዲሆን ለማድረግ፣ በትዳራቸዉ በጋራ ካገኙት ልጃቸዉ ጋር ይህችንም ልጅ ለማሳደግ በማሰብ 2ኛ አመልካች የጉዲፈቻ አባት እንዲሆን ለማስቻል፣ የጉዲፈቻ ስምምነት ፈርመዉ ፍ/ቤቱ እንዲያጸድቅላቸዉ ያቀረቡ መሆናቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ የሆነችዉ የ1ኛ አመልካች ልጅ፣ አመልካቾች በትዳራቸዉ ዉስጥ ከወለዱት ልጃቸዉ ጋር እያሳደጓት ያሉ እና ይህች ልጅ አሁንም በ2ኛ አመልካች ስም እየተጠራች በአመልካቾች ዘንድ የሚትኖር መሆንዋ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ አመልካቾች የሚኖሩት በኢትዮጵያ ዉስጥ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ አመልካቾች ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመዉ በትዳር አብረዉ በመኖር ልጅ ማፍራት የሚከለችላቸዉ ሕግ እስከሌለ ድረስ፣ ከትዳራቸዉ በፊት የባል ወይም የሚስት ልጅ የሆነዉን ሌላኛዉ ተጋቢ በጉዲፈቻ ስምምነት መዉሰድ አይችልም የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 መሰረት የአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193፣ 194 (3፣ መ) እና (4) ድንጋጌዎች መሰረዛቸዉን እንጂ የአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 187 ድንጋጌ መሰረዙን ወይም መሻሻሉን የሚያመለክት አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ የሚገባዉ የአዋጅ ቁጥር 1070/2010 ሳይሆን የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አግባብነት ያላቸዉ ደንጋጌዎች ናቸዉ፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኞቸዉን የባልና ሚስት ግንኙነት፣ አንድ ልጅ በትዳራቸዉ ወልዳዉ ያላቸዉ መሆናቸዉን፣ 1ኛ አመልካች የጉዲፈቻ ተደራጊዋ ልጅ እናት መሆንዋ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አመልካቾች የጉዲፈቻ ተደራጊዋን ልጅ አሁንም አብረዉ እያሳደጓት እና በኢትዮጵያ ዉስጥ እየኖሩ መሆናቸዉን ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ፣ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 መሰረት ጉዲፈቻ ለዉጭ አገር ዜጋ ተከልክሏል በማለት አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲጸድቅላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን ግንኙነት ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ ጉዲፈቻ ለዉጭ አገር ዜጋ ተከልክሏል በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.127142 በ9/9/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274588 በ22/11/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲጸድቅላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. አመልካቾች በዚህ ችሎት በነበረዉ ክርክር የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ.215435

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....ወ/ሮ ጽጌ ጅማ - ጠበቃ በፍቃዱ ስዩም ቀረቡ

ተጠሪ፡.....1. አቶ ፀጋዬ ፈሲሳ

2. ወ/ሮ አለምነሽ ፈሲሳ ተተኪ ወራሽ ዋሲሁን ደጀኔ

3. አቶ ሰይፉ ፈሲሳ

4. አቶ ግዛቸዉ ፈሲሳ

5. ወ/ሮ አልማዝ ፈሲሳ

አልቀረቡም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የዉርስ ይጣራልን ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ጣልቃ ገብ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር አመልካቾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274845 በ28/01/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪዎች (የሥር አመልካቾች) በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ሚች አባታችን አቶ ፈሲሳ ሉቤ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁ.161 ውስጥ እየኖሩ ባደረባቸዉ ሕመም ምክንያት በ13/10/1959 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆኑ፣ የሚች የውርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፤ በፍ/ቤት የውርስ አጣሪዉ ተሹሞ የዉርስ ሀብቱ ተጣርቶ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን አመልካች (የሥር ጣልቃ ገብ) ለይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍ/ቤቱም ባሳለፈዉ ዉሳኔ ጣልቃ ገብ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በቅድሚያ በማከራከርና ወደ ፍሬ ነገር የሚያስገባም ከሆነ አከራካሪዉ ቤትና ይዞታ ሚችና ጣልቃ ገብ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ሀብት መሆን አለመሆኑ ግራ ቀኙን እንደገና እንዲያከራክርና የመሰለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡

በዚህ መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደገና ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በተመለከተ በሰዉ ምስክሮች በማጣራት፣ በሰጠዉ ብይን የሥር 3ኛ እና 5ኛ አመልካቾች በግራ ቀኙም ምስክሮችና ክርክር በተነሳበት ቤትና ይዞታ ላይ ከጣልቃ ገብ ጋር እየኖሩበት እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆናቸዉ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ ጣልቃ ገብም ይህንን በማመን ታማሚ በመሆናቸው በቤቱ እንዲኖሩ ተደረጉ እንጂ መብትና ጥቅም የላቸዉም ቢሉም እነዚህ አመልካቾች መብትና ጥቅማቸውን የተዉ መሆናቸዉን ያላረጋገጡ በመሆኑ፣ የሥር አመልካቾች የወራሽነት መብቱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት በጣልቃ ገብ የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ምስክሮቻቸዉን እንዲቀርቡ ያዘዘ ሲሆን፣ የሥር አመልካቾች የሰዉ ምስክሮች አቅርበዉ ያሳሙ ሲሆን፣ ጣልቃ ገብ ግን የሰዉ ምስክሮችን ባለማቅረቧ የተሰመ ምስክር አለመኖሩን በማመልከት፤ የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ እና የሰዉ ምስክሮችን ቃል በመመርመርና በመመዘን፣ ባሳለፈዉ ዉሳኔ የሥር አመልካቾች ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ክርክር የተነሳበትን ቤት ሚች አቶ ፈሲሳ ጣልቃ ገብን ከማግባታቸዉ በፊት በጭሰኝነት በማገኘት ሶስት ክፍል ቤቶች የሰሩበት መሆኑንና አሁን በሥር አመልካቾችና በጣልቃ ገብ ተይዞ የሚገኝ መሆኑን የመሰከሩ በመሆኑ፤ የቤቱ ማህደርም በጣልቃ ገብ የተደራጀና በ1938 ዓ.ም የተገኘ መሆኑን ቢገልጽም በምን አግባብ እንደተገኘ የማይገልጽ በመሆኑና የቀረቡት ምስክሮች ሚች በጭሰኝነት እንዳገኙት ያስረዱ በመሆናቸዉ፤ የሥር አመልካቾች ቤቱ የሚች የግል ሀብት ነዉ ጣልቃ ገብን አይመለከታትም በማለት ያልተከራከሩ በመሆኑ፤ ጣልቃ ገብ በቤትና ይዞታው ላይ የተደረገን ለውጥ ባለማስረዳታቸው፤ ምንም እንኳን ቤትና ይዞታ በጣልቃ ገብ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም በትዳር ውስጥ የተፈራ ስለሆነ፣ ቤትና ይዞታዉ የሚችና የጣልቃ ገብ የጋራ ሀብት በመሆኑ ግማሹ የሚች የውርስ ሀብት ነዉ በማለት የዉርስ አጣሪን ዉጤት አጽድቆታል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የተጠሪዎች አባት የሞቱት በ1959 ዓ.ም በመሆኑና ተጠሪዎች የዉርስ ጥያቄ ያቀረቡት አባታቸዉ ከሞቱ 50 ዓመታት ካለፈ በኋላ ስለሆነ ጥያቄአቸዉ በይርጋ የሚታገድና በይርጋ ላይ የሰዉ ምስክሮችን

መስማት ሳያስፈልግ ምስክሮች ሰምቶ ዉሳኔ ማሳለፉ፤ የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በህመም ምክንያት መጥተው አከራካሪዉ ቤት ዉስጥ እየኖሩ ያሉ ከመሆናቸው ውጪ ቤቱ በአመልካች ብቻ ተመዝግቦና ተይዞ ያለ በመሆኑ፤ 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የቤቱ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸዉ ነገር በሌለበትና ያቀረቡት ክርክር በይርጋ ቀሪ ሆኖ ሳለ፤ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት በመሆኑ፤ አመልካች የሰዉ ምስክር ለማቅረብ ብጠይቅም ያልተፈቀደልኝና ለተጠሪዎች መፈቀዱ፤ በአምልካች ብቻ የተገነባውን ቤት የዉርስ ሀብት ነዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ ስህተት በመሆኑ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ብቻ በአከራካሪዉ ቤት ዉስጥ ከአመልካች ጋር አብረው መጠቀማቸዉ ከመሆኑ አንጻር የ1ኛ፤ 2ኛና 4ኛ ተጠሪዎች ክርክር በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የሰጠው ውሳኔ ህጋዊነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ18/6/2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተነጣጥሎ የቀረበ ክስ የለም፣ ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ በጋራ አመልካቾችና የጋራ መከላከያ ያቀረብን በመሆኑ፣ ተጠሪዎች አንዱ በሌላዉ ላይ የይርጋ መቃወሚያ ያላነሰ በመሆኑ፣ የአሁን 3ኛና 5ኛ ተጠሪዎች በቤቱ መኖራቸው ከተረጋገጠ፣ ሌሎቹ ተጠሪዎች በቤቱ ቢኖሩም ባይኖሩም ክርክራችን በይርጋ አይቋረጥም፤ በ3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ መቃወሚያ ዉድቅ ከተደረገ በውርስ ሀብቱ ላይ ክርክር ሊኖር የሚችለው በወራሾች መካከል ብቻ ነው እንጂ አመልካች የሚያጡትም ሆነ የሚያገኙት ነገር የለም፤ አመልካችም በስር ፍ/ቤት በ1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ሊጠይቁ አይገባም በማለት ያልተከራከሩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ 3ኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብቱ ተልፏል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ባነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተጠሪዎች አባት በ1959 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆኑ ተጠሪዎች የአባታችን የዉርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ክስ አቅርበዉ ዳኝነት የጠየቁት ከ50 ዓመታት በኋላ ስለሆነ ክሳቸዉ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት የተከራከሩ ሲሆን፤ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር የዉርስ ሀብት የሆነዉን የመኖሪያ ቤት 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በቤቱ መኖራቸዉ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪዎች በጋራ አመልክተንና መከላከያ ያቀረብን በመሆኑ 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በቤቱ ቢንኖርም ባንኖርም ክሳችን በይርጋ ሊቋረጥ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ መርምሮ መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሕግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የሰዉ ምስክሮች ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ብቻ ከአመልካች ጋር በአከራካሪዉ ቤት እየኖሩና እየጠቀሙበት መሆኑን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አከራካሪዉ ቤት እየኖሩበትና እየተጠቀሙበት መሆናቸዉ የምስክርነት ቃላቸዉን በሰጡት የሰዉ ምስክሮች አልተረጋገጠም እንዲሁም ተጠሪዎችም በቤቱ እየኖሩበትና እየተጠቀሙበት መሆናቸዉን በግልጽ ጠቅሰዉ የተከራከሩት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በዚህ ቤት የማኖሩበትና የማይጠቀሙበት መሆናቸዉ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በሥር ፍ/ቤት ከግራ ቀኙቸዉ ክርክር አንጻር የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አከራካሪዉና በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 161 የሆነዉ የመኖሪያ ቤት አመልካች እና ባለቤታቸዉ አቶ ፈሲሳ ለቤ በትዳር አብረዉ እያሉ በጋራ ያፈሩት የጋራ ሀብታቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የሟች አቶ ፈሲሳ ለቤ ልጆችና ወራሾች መሆናቸዉ ያላከራከረና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ አቶ ፈሲሳ ለቤ በ1959 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆናቸዉ፣ የአመልካች እና የአቶ ፈሲሳ ጋብቻ በሞት ምክንያት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የፈረሰ መሆኑን ያመለክታል፡፡ አመልካች የሟች አቶ ፈሲሳ ለቤ ሚስት ሲሆኑ፣ ተጠሪዎች ደግሞ የሟች ልጆችና ወራሾች በመሆናቸዉ፣ ይህ ክርክር በወራሾች እና ወራሽ ባልሆነ ሰዉ መካከል የሚነሳ ክርክር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

እንደሚታወቀዉ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.25664 ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም (ቅጽ 6) ባሳለፈዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ‹‹በወራሾች እና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የዉርስ ሀብትን የተመለከተ ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1677 (1) መሰረት በአንቀጽ 1845 አግባብ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን መወሰኑን›› ማየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.44025 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም (ቅጽ 10) ባሳለፈዉ አስገዳጅ ዉሳኔ የዉርስ ሀብቱን በእጅ አድርጎ ይዞ የሚገለገልበትና የሚያስተዳድር ወራሽ የሚያነሳዉ የዉርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ማለት እንደማይቻል መወሰኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ አስገዳጅ ዉሳኔ መሰረት ወራሽ የዉርስ ሀብቱን ይዞ የሚጠቀምበት እንደሆነ ወራሹ የሚያቀርበዉ የዉርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች አከራካሪዉን የዉርስ ሀብት የሆነዉን የመኖሪያ ቤት ከአመልካች ጋር እየኖሩበትና እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆናቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሟች አባታችን የዉርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ያቀረቡት የዉርስ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት የሟች አባታችን የዉርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በአከራካሪዉ የዉርስ ሀብት በመሆነዉ የመኖሪያ ቤት እየኖሩበት እየተጠቀሙበት አለመሆናቸዉ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ፣ እነዚህ ተጠሪዎች የሟች አባታችን የዉርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ያቀረቡት የዉርስ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1677 (1) መሰረት በአንቀጽ 1845 አግባብ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባሳለፈዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት የዉርስ ይጣልን ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ ሳለ፣ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ የህግ ድጋፍ የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሟች አባታችን የዉርስ ሀብት እንዲጣራልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ የሚነቀፍ ባይሆንም፣ 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ ግን በይርጋ የሚታገድ ሆኖ ሳለ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ.141226 በ23/9/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274845 በ28/01/2014 ዓ.ም ያሳለፈዉ ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 1ኛ፣ 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በተመለከተ ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.215452
ህዳር 30/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ ወልዳይ ገ/ማርያም

ተጠሪ፡ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ገደብ የተደረገበትን ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን የውጭ ሀገር ገንዘብ ይዞ መገኘት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀፅ 26(1(ሀ(1))) እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 346 ድንጋጌን ጠቅሶ በአሁን አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን ድንጋጌ በመተላለፍ ገደብ የተደረገበት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት የውጭ ሀገር ገንዘብ መሆኑን እያወቀ በዲኪላራሲዮን ያልተመዘገበ 5,000(አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ይዞ ህዳር 17/2013 ዓ.ም ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት አካባቢ በመገናኛ ባቡር ፌርማታ ባቡር ሊሳፈር ሲል በወቅቱ በነበሩት የፀጥታ ኃይሎች በተደረገ ፍተሻ የተያዘ በመሆኑ የውጭ ሀገር ገንዘብ አከማችቶ ይዞ መገኘት ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለዚህ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን አምኖ በአፈፃፀም ረገድ ጥፋተኝነቱን ክዶ የተከራከረ በመሆኑ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች እንዲቀርቡ ተደርጎ ሁለት ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቀን የፍተሻ ስራ ላይ የነበሩ የፖሊስ ባልደረቦች መሆናቸውን ገልፀው በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን መጠን የአሜሪካን ዶላር በአመልካች እጂ ማግኘታቸውን፣ ከ3,000(ሶስት ሺህ) በላይ የሆነ የአሜሪካን ዶላር ይዞ የሚንቀሳቀስ ሰው ካገኙ በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከመስሪያ ቤታቸው በተሰጣቸው አቅጣጫ መሰረት አመልካችን ከእነ ገንዘቡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የወሰዱት መሆኑን በመናገራቸው አመልካች ክሱን እንዲከላከል ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ ማህደር ትዕዛዙ የተባሉት ግለሰብ ከኩዌት ሀገር ለእናታቸው ህክምና ወጪ እንዲውል ወ/ሮ አልማዝ ግደይ በተባሉት ግለሰብ በኩል ወደ ሀገር ቤት ልከው አመልካች ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም በቦሌ አየር ማረፊያ ገንዘቡን ከወ/ሮ አልማዝ የተቀበሉ መሆኑን እንደሚያውቁ ተናግረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር FXD/49/2017 አንቀፅ 4.1(ለ) መሰረት ከ3,000(ሶስት ሺህ) ዶላር በላይ ይዞ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር የሚገባ ሰው ዶላሩን ዲክሌር ማስደረግ የሚገባው ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም ክስ የቀረበበት ገንዘብ ዲክሌር ያልተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፤ አመልካች ገንዘቡን በአደራ ከሌላ ግለሰብ የተቀበሉ ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃቸው ያስመሰከረ ቢሆንም ገንዘቡን ሲቀበሉ ዲክሌር ስለመደረጉ ያረጋገጠው ነገር ባለመኖሩ ህግን ያለማወቅ ከህግ ተጠያቂነት የሚያስመልጥ አይደለም፤ ገንዘቡን ተቀብልኩ ያለውም ጥቅምት 30/2013 ሆኖ እያለ በእጁ እስከተያዘበት ህዳር 17/2013 ዓ.ም ድረስ ይዞ መቆየቱ ገንዘቡን መደበቁን የሚያሳይ በመሆኑ ይዞ መገኘቱ ብቻ ጥፋተኛ ያደርገዋል በሚል ምክንያት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ክስ በቀረበበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ብሎት በ3/ሶስት/ ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን አዟል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 17/2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የቅጣት ውሳኔ የሰጠበት አግባብነት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የብር እና የውጭ ምንዛሪ አያያዝን በተመለከተ ካወጣው መመሪያ ቁጥር 49/2017 አንቀፅ 3 አኳያ በዚህ ችሎት እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ይህንን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

አመልካች የተከሰሰው ገደብ የተደረገበት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት የውጭ ሀገር ገንዘብ መሆኑን እያወቀ በዲክላራሲዮን ያልተመዘገበ 5,000(አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ይዞ ተገኝቷል በሚል ነው፡፡ አመልካች የተጠቀሰውን ገንዘብ ይዞ መገኘቱን አይክድም፡፡ ከዚህ ይልቅ እየተከራከረ ያለው ገንዘቡን ለሌላ ሰው በሚል ከውጭ ሀገር በእኔ በኩል በአደራ ተልኮ የተቀበልኩት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች አቅርቦ ያሰማቸው የሰው ምስክሮችም ከሞላ ጎደል በዚሁ መልኩ የመሰከሩ ስለመሆኑ የስር ፍርድ መዝገብ ያሳያል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከላካያ ምስክሮች ቃል መርምሮ መከላከያውም ሆነ የተሰጠው የምስክርነት ቃል የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን የሚያስተባበል አይደለም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

እንግዲህ ማስረጃ የሚያስፈልገው አንድን ክርክር የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ነው፡፡ የቀረበው ማስረጃ የተባለውን ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ወይም ስላለመኖሩ አስረድቷል ወይም አላስረዳም በሚለው ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የቀረበውን ማስረጃ መመርመር፣ ማገናዘብ፣

መተቸት በጥቅሉ መመዘን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መልኩ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማስረጃን በመመርመር እና በመመዘን የተደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ሰበር ችሎት ሊለወጥ የሚችለው ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀመው ስህተት ከተገኘ ብቻ ስለመሆኑ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱን በመካድ፣ በዚህ የሰበር ክርክር ደግሞ ድርጊቱ ወንጀል አይደለም የሚል መከራከሪያ ከማቅረብ ባለፈ የስር ፍርድ ቤት ከማስረጃ ምዘና አንፃር የፈፀመው የምዘና መርህ ጥሰት ስለመኖሩ የቀረበው የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ለአመልካች መከራከሪያ መሰረት የሆነው ማስረጃ ተመዝኖ ተቀባይነት እንደሌለው ተወስኖ ባለበት ይኸው ማስረጃ መሰረት ተደርጎ ድርጊት ወንጀል አይደለም በሚል ክርክር ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የማይቻል በመሆኑ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ/274377 ላይ ጥቅምት 01/2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ 215524

ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋኖስ ባይልኝ --ተወካይ ሻረዉ ሞገስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. ወ/ሮ አቦዝነች ሞገስ

2ኛ. ወ/ሮ መሰረት ሞገስ

3ኛ. አቶ መሉነህ ሞገስ ከጠበቃ የሺጥላ አለሙ ጋር ቀረቡ

4ኛ. ወ/ሮ እልፍነሽ ሞገስ

5ኛ. አቶ ሻረው ሞገስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 19/02/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 228708 በቀን 29/07/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270863

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በቀን 09/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ከ1ኛ - 4ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ሲሆን የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ እንዲሁም የአሁኑ 5ኛተጠሪ በስር 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ።

ከሳሾች ባቀረቡት አቤቱታ ወላጅ አባታችን አስር አለቃ ሞገስ ጋሻው ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ውርስ አጣሪ እንዲሾምልን በማለት ጠይቀው ተከሳሾችም ክርክራቸውን አቅርበው ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ጥቅምት 24/2009 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ቀርቦ ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን በማረም አጽድቆታል። በዚህ ውሳኔ ላይ በይግባኝ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደርሶ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 177586 ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን የቤት ቁጥር 1285 የሆነ መኖሪያ ቤት በተመለከተ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን ጭብጥ ለይቶ በመመሪያ ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሷል። መመሪያ የተሰጠውም የአሁን አመልካች ከሚች ባለቤታቸው ፤ አለቃ ሞገስ ጋሻው በትዳር ሲኖሩ ለክርክር መነሻ የሆነውን የቤት ቁጥር 1285 የሆነ መኖሪያ ቤት በጋራ ያፈሩት ንብረት መሆን አለመሆኑን የግራቀኙን ማስረጃ እራሱ ፍርድ ቤቱ ሰምቶና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥበት በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) ነው።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የተመለሰለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና የምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ የምስክሮቹ ቃል ሲመዘን ሚች ፤ አለቃ ሞገስ ጋሻው ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ከተከሳሽ ጋር ከመጋባታቸው አስቀድሞ የነበራቸው መሆኑ እና ከተከሳሽ ጋር ከተጋቡ በኋላ ተጨማሪ ክፍሎችን መስራታቸውን የነበረው ቤት ላይም እድሳት ያደረጉ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ቤቱን አብረው ያፈሩት እንዳልሆነ ከምስክሮቹ ቃል መረዳት መረዳት ይቻላል፤ በቤቱ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች መስራታቸው እና የነበረውን ቤት ከሚች ጋር በትዳር ሲኖሩ ማደሳቸውም በከሳሾችም አልተካደም። በመሆኑም አከራካሪውን ቤት ሚች ከተከሳሽ ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት በግል ያፈሩት የግል ንብረታቸው መሆኑ ተረጋግጧል፤ ሚች እና ተከሳሽ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ የቤ.ቁ 1285 በሆነው ቤት ላይ በመቀጠል የሰሯቸው ክፍሎች እና ለእድሳት ያወጡትን ወጪ በተመለከተ ፍ/ቤቱ አስቀድሞ በነበረው ክርክር የግንባታ እና የእድሳት ወጪ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ጠቅላላ ወጪው ብር 43,246.19 (አርባ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ስድስት ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) መሆኑ ተገምቶ የቀረበ በመሆኑ የ1ኛ ተከሳሽ ድርሻ ግማሹ ብር 21,623.10 (ሀያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሀያ ሶስት ከአስር ሳንቲም) በመሆኑ ይኸው ገንዘብ ከሚች የውርስ ሀብት ላይ ለ1ኛ ተከሳሽ ሊከፈል ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው።

አመልካች በቀን 19/02/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የስር ፍርድ ቤት የስነድ ማስረጃዎችን አልፎ የሰው ምስክር ሰምቶ ምስክርነቱንም ሳያመዛዝን የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈፀመበት

በመሆኑ፤ ግንቦት 02 ቀን 1976 ዓ.ም ሟች እና አመልካች በጋብቻ ውል ስምምነታችን ቤቱን የጋራ ሀብት በማድረግ የጋብቻ ውል ፈጽመን በ09/04/2007 ዓ.ም ውሉ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርቦ ተመዝግቧል፤ ይህንኑ የጋብቻ ውል ይዘን በልደታ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር አመልክተን ሟች እና አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካርታ ቁ/ል-03/125/8429/00 በቀን 01/09/2005 ዓ.ም በባልና ሚስትነት በይዞታ ማረጋገጫ ላይ በሁለታችን ስም ተመዝግቦ ካርታ ተሰጥቶናል፤ ይኸው የሰነድ ማስረጃ ለውርስ አጣሪ ቀርቦ ጋብቻው የተፈጸመበት የሰነድ ማስረጃና ይዞታ ማረጋገጫ ካርታው እውነተኛ ሰነድ መሆኑን ከሰጠው ባለስልጣን ጠይቆ አረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ሰነዶችን አልፎ እርስ በእርሱ የሚጣረስ የሰው ምስክር ቃል ብቻ ሰምቶ የሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻር በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን ቤት በሚመለከት በካርታ ቁጥር ቁ/ል-03/125/8429/00 በ01/09/2005 ዓ.ም በባልና ሚስትነት የይዞታ ማረጋገጫ ላይ በሟች እና በአመልካች ስም ያለ መሆኑን ገልጸው ተከራክረው ባለበት የስር ፍ/ቤት አመልካች ለእድሳት የወጣውን ወጪ ብቻ እንዲካፈሉ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እበንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ከ1ኛ-4ኛተጠሪዎች በቀን 14/04/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ተጠሪዎች የስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 228708 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የውርስ አጣሪ ስልጣን ሳይኖረው ምስክር ሰምቶ የሰራውን ሪፖርት ሳይመረምር ውሳኔ በመስጠቱ ይህን ለማሳረም አስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔውን ሽሮ የስር ፍ/ቤት የሰው ምስክር ብቻ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥ መመሪያ በመስጠቱ በዚህ መልኩ ተሰምቶ መወሰኑ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ክርክር ያስነሳው ቤት የተሰራው አመልካች በሰራተኝነት በ1976 ዓ.ም ግንቦት ወር ተቀጥረው ወደ ቤት ከመግባታቸው በፊት ቤቱ ተሰርቶ 10 አመት ያለፈው ለመሆኑ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፤ አመልካች በቦታው ላይ ቤት ሰርቼ ስጠቀምበት የኖርኩት ነው ይበሉ እንጂ ቤቱን ስለመስራታቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፤ በምስክሮቹ የተረጋገጠው የተለያዩ እድሳት ማድረጋቸውን እንጂ አዲስ መሰረታዊ ለውጥ አድርገው ቤት ሰርተው ለመኖራቸው አይደለም፤ ቀደም ሲል ከዋናው ቤት ግድግዳ ጋር ተያይዞ የተሰራው ሽንት ቤትና ኩሽና ተደፍኖ አነስተኛ ቤት የሆነ፣ በረንዳው አንድ ቆርቆሮ ተቀጥሎ አንድ አነስተኛ ክፍል ቤት የተሰራ ለመሆኑ፣ ከአጥሩ ጋር ተያይዞ የተሰራ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሆነ አንድ ሱቅ እና አጥር አጥሬያለሁ ላሉት በተገቢው መንገድ በህጋዊ ገማቾች ተገምቶ ግምቱን እንዲወስዱ የተወሰነ በመሆኑ ይህም አግባ አይደለም ብለው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች የስር ፍ/ቤት በሰው ምስክር ብቻ ሰምቶ የሰነድ ማስረጃውን ሳይቀበል ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ያቀረቡት የስር ፍ/ቤት ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት በተሰጠው መመሪያ መሰረት የሰው ምስክር ሰምቶ እንዲወስን በመሆኑ ህጋዊ ነው ከሚሰኝ በቀር ስህተት የለውም፤ የሰነድ ማስረጃዎች አላቀረቡም እንጂ አቅርበው ቢሆን እንኳ ሰነዱ ተጭበርብሮ የወጣ በመሆኑ

ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ውሳኔ የሰጠው ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመመሪያ በተመለሰለት መሰረት ተገቢውን ትጋት አድርጎ መሆን አለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከፍሲል እንደተገለፀው ጉዳዩ ወደስር ፍርድ ቤት የተመለሰው አመልካች ከሚች ባለቤታቸው ፤ አለቃ ሞገስ ጋሻው በትዳር ሲኖሩ ለክርክር መነሻ የሆነውን የቤት ቁጥር 1285 የሆነ መኖሪያ ቤት በጋራ ያፈሩት የጋራ ንብረታቸው መሆን አለመሆኑ በግራቀኝ ማስረጃና ተገቢው ማጣራት ሁሉ ተደርጎ ውሳኔ እንዲሰጥበት ነው፡፡ ይሁንና የስር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር እንኳ ያልካዱትን በጋብቻ ጊዜ ቤቱ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች መሰራታቸው እና የነበረውን ቤት ከሚች ጋር በትዳር ሲኖሩ ማደሳቸው በምስክር ተረጋግጧል በማለት የባለሙያ ግምቱን አመልካች እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

እንደሚታወቀው የበላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን በነጥብ ሲመልስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማጣራት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ትጋት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) ድንጋጌ ይዘትና አላማ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚች ችሎት በሰ/መ/ቁ 72189 እና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ምስክር ብቻ ሰምቶ እንዲወስን የተሰጠ መመሪያ የለም፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔም ይህን አይልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በጋብቻ ጊዜ ቤቱ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች መሰራታቸው እና የነበረውን ቤት ማደሳቸውን ብቻ ሳይሆን ግንቦት 02 ቀን 1976 ዓ.ም በተደረገና በኃላም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተመዝግቧል በሚሉት የጋብቻ ውል የጋራ የተደረገ ንብረት መሆኑን፤ በጋብቻ ውሉ መሰረት ለመሬት አስተዳደር ከባለቤታቸው ጋር አመልክተው በሚች እና አመልካች ስም የካርታ ቁ/ል-03/125/8429/00 የተቀበሉበት የጋራ ንብረታቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም የሰነድ ማስረጃዎቹ ሀሰተኛ የሆኑና ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በዝርዝር በመመልከትና ተገቢውን ማጣራት ሁሉ በማድረግ ውሳኔ መስጠት እየተቻለ እንዲህ አይነት ጥረት ሳይደረግ ባልተካካዱበት ነጥብ ላይ በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት ውሳኔ መሰጠቱ አስቀድሞ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን የተሰጠውን ውሳኔ ያልተከተለና ክርክሩ የሚመራበትን ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አስቀድሞ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 177586 ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠውን መመሪያ ሳይከተልና የግራቀኙን ክርክር ተከትሎ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ

የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 228708 በቀን 29/07/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270863 በቀን 09/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ሙሉ ክርክር እና ማስረጃ በመመልከት እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 177586 ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለ ችሎት በሰጠው መመሪያ መሰረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰን ልከናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 215531

ቀን ፡- ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ታሪኳ ቶሎሳ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ኢትዮጵያ ግርማ
2. አቶ እሸቱ ግርማ
3. ወ/ሮ የሺመቤት ግርማ
4. አቶ ዘላለም ግርማ
ወኪል 5ኛ ተጠሪ ቀረቡ
5. አቶ አዲስ ግርማ፡- ቀረቡ
6. አቶ አባተ ተረፈ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ

ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር የመቃወም አመልካች፤ ተጠሪዎች የመቃወም ተጠሪዎች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 167 የሆነ የሚች አባታችን ግርማ አበበ የውርስ ንብረት 6ኛ ተጠሪ ስለያዘ ለቆ ያስረክበን በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን 6ኛ ተጠሪ ንብረቱ በውል ያገኘሁት የራሴ ንብረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበት ቤት ከ1ኛ-5ኛ ተጠሪዎች በውርስ የሚገባቸው ንብረት ነው በማለት 6ኛ ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የመቃወም ማመልከቻ ያቀረቡትም ውሳኔው መብቴን ነክቷል በማለት ሲሆን የማመልከቻው ዝርዝር ይዘትም ውሳኔ ያረፈበት ንብረት የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ-5ኛ ካሉት ተጠሪዎች አውራሽ በወኪሉ 6ኛ ተጠሪ አማካኝነት በብር 70,000.00 ገዝቼ ቤቱን ተረክቤያለሁ፡፡ ውሉ ባይመዘገብም ሳያስፈርሱ 10 ዓመት አልፏል፡፡ 6ኛ ተጠሪ ንብረቱን በአደራ እንዲጠብቅ አድርጌያለሁ፤ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ለ6ኛ ተጠሪ ተሸጦ የነበረ ቢሆንም ውሉም ስላልተመዘገበ ሚያዚያ 30 ቀን 1988 ዓ/ም በተደረገ ሥምምነት ፈርሷል፡፡ 6ኛ ተጠሪ የገዛሁት ቤት ነው በማለት ተከራክሮ ተረቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በሀሰት የቀረበ ነው፡፡ ውክልናው ላይ ያለው ፊርማ የአውራሻችን አይደለም፡፡ በውክልና የተደረገ የሽያጭ ውል ነው ቢባል እንኳን በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት ያልተመዘገበ ረቂቅ ውል ስለሆነ የመቃወም አመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 6ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በውክልና ሥልጣኔ ለአመልካች ቤቱን ሽጬላቸዋለሁ፤ ቤቱን በጠባቂነት ነው የያዝኩት፤ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ንብረቱ የራሴ ነው በማለት የተከራከርኩት በግንዛቤ ጉድለት ነው ብለዋል፡፡

የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ 6ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ውክልና ከሚች ግርማ አበበ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ረቂቅ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የቀረበው የመቃወም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የአመልካች ይግባኝ ማመልከቻን ውድቅ ያደረገ ሲሆን የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ/ም የተጻፈ ሲሆን ይዘቱም በሽያጭ ውሉ መሠረት ገንዘቡን ከፍዬ ቤትና ሠነዶቹን ተረክቤያለሁ፤ በፍ/ሕ/ቁ. 2189 መሠረት የወኪሉ ሥራ ጉድለት ካለበት መቃወም የሚችለው ወካዩ እንጂ ወራሾቻቸው መቃወም አይችሉም፤ ውሉ ፎርሙ አልተሟላም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ወካዩ ባይኖርም ወኪሉ ውሉን ስላመነ፤ ለታመነ ውል ፎርም ሊነሳ አይገባም በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 26887 የተሰጠውን ትርጉም ፍርድ ቤቱ አልተከተለም፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች የሻጭ ወራሾች በመሆናቸው እንደ 3ኛ ወገን ሊታዩ አይገባም፡፡ የሽያጭ ውሉ ፎርሙ አልተሟላም ካሉ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መቃወሚያ አቅርቤ መታለፉ

ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ቤቱን የገዙበት ውል ታምኖ እያለ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት አልተደረገም ተብሎ ክርክራቸው ውድቅ መደረጉ ከፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 ላይ ከሰጠው ትርጉም አንጻር ተገቢነቱን ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አሏል። ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ውሉን ክደን ነው የተከራከርነው፣ ገዛሁበት ያሉት ውል ረቀቂ በመሆኑ መብት አይሰጣቸውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው። ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል። 6ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ለአመልካች በውክልና የተደረገው ውል ስላልተመዘገበ ንብረቱን እኔ እንድገዛው ወራሾች ስለተስማሙ ቤቱን ልረከብ ይገባል በማለት ተከራክረዋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታው መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመረነው ክርክር ያስነሳው ንብረት በደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 167 ሲሆን ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠረዎች የሚች አባታቸው ግርማ አበበ ወራሾች በመሆናቸው 6ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው ንብረቱን እንዲረከቡ የተወሰነ ሲሆን አመልካች ባቀረቡት የመቃወም ማመልከቻ ንብረቱን ከሚች አባታቸው በወኪሉ 6ኛ ተጠሪ አማካኝት በብር 70,000.00 ገዝቼ ቤቱን ተረክቤያለሁ፣ ውሉ ባይመዘገብም ሳያስፈርሱ 10 ዓመት አልፏል፤ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት 6ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ውክልና ከሚች ግርማ አበበ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፣ ነገር ግን አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ረቂቅ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የቀረበው የመቃወም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። ጉዳዩ እስከ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን ተገንዝበናል።

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ። መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር። ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ

እንዲያከናውኑ ማድረግን አንዱ ዓላማው ያደረገው ይህ አዋጅ ካካተታቸው አዳዲስ ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነው፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነው፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለውን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳው የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ውጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ውስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ ሲሆን አቤቱታው የቀረበውም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም (አንቀጽ 58 ይመለከቷል)፣

ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ/ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ መሠረቱ ውልን መሠረት ያደረገ ሳይሆን የውርስ ንብረትን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ውርሱን ለመጠየቅ በሕግ በተመለከተዉ ጊዜ ክሱን አላቀረቡም የሚል ክርክር የላቸውም፤ የአመልካች ክርክር ውሉን በ10 ዓመት ጊዜ አላስፈረሱም የሚል ነው፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ክስ የውርስ ንብረት መብትን ለማስከበር ንብረቱን የያዘው ሰው ለቆ እንዲያስረክባቸው የቀረበ ዳኝነት እንጂ ውል እንዲፈርስ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም፡፡ ክስ የቀረበበት ንብረት ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በውርስ ያገኙት መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በመቃወም ማልከቻቸው ያቀረቡትን ንብረቱን ከአውራሻቸው ገዝቻለሁ የሚለውን ውል ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር የካዱ በመሆኑ አመልካች ቤቱን በውል በመግዛት ንብረቱ የተላለፈላቸው ስለመሆኑ በሕግ ተቀባይነት ባለው ማስረጃ የማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በአመልካች የቀረበው የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው ውል የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በሚደረግበት አካኋን በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) መሠረት በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ አመልካች በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል ካላቀረቡ በስተቀር ሕጋዊ የቤት ሽያጭ ውል አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በሕግ ፊት ሊጸና የሚችል ውል ስለመኖሩ ካልተረጋገጠ ደግሞ አመልካች ውሉ ሕጋዊና ውጤት ሊሠጠው የሚገባ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 202157 እና ሌሎች መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡ ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-13034 ጥቅምት 15 ቀን 2014 ዓ/ም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 013-6214 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119663 ሰኔ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጸፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር 215534

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ዉድነህ መንገሻ፡- ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት አካባቢ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ ቁጥጥር ባለስልጣን፡- ተወካይ አቶ ደመላሽ ቀረቡ

2. የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ፕብሊክና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ እንደሻው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ

ተሰጥቷል

ፍርድ

ጉዳዩ የመንግስት ሠራተኛ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ በ1ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት የአካባቢ ጥበቃ አየር ንብረት ለዉጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የስራ መደብ ላይ ተወዳድረዉ ምደባ ከተሰጣቸዉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት እንስፔክሽን ጉዳዩን ያለስልጣኑ አይቶ የተሰጣቸዉን ምደባ ሰርዞ ለሌላ ግለሰብ የሰጠ መሆኑን ጠቅሰዉ የእንስፔክሽኑ ዉሳኔ እንዲሻርላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ደግፎ የተከራከረ ሲሆን፣ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ መደቡ በጄኢጄ መሠረት ለቀጥተኛ የስራ ልምድ 100% ዋጋ የሚሰጥ ሲሆን

በዉድድሩም አመልካች የነበራቸዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን ሲሆን ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ሌላ ግለሰብ ከ10 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑ በመረጋገጡ የ2ኛ ተጠሪ እንስፔክሽን ክፍል በህግ በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የአመልካችን ምደባ በመሰረዝ የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል።

ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በጄኢጄ መመሪያ መሠረት ለመደቡ የሚፈለገዉ የስራ ልምድ ቀጥተኛ እንጂ ተቀራራቢ አለመሆኑን፣ በዚህ ረገድ የአመልካች ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ 1 ወር ሲሆን ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ግለሰብ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 11 ዓመት ከ 7ወር ያላቸዉ ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ የተጠሪ ቢሮ እንስፔክሽን የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ አጽንቶታል። አመልካች በዚህ ዉሳኔም ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ የ2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት እንስፔክሽን የክልሉ የመንግስት ሠራተኞች ህግጋትን በትክክል ስራ ላይ መዋል አለመዋላቸዉን የኦዲት ስራ በመስራት አካሄዶችን የማረም እንጂ ምደባን አስመልክቶ የሚነሱ ቅሬታዎችን መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም። የከተሞች አደረጃጀት ፕላን ዝግጅት ክትትል ስራ ሂደት አስተባባሪ ሆኜ የሰራሁት የ8 ዓመት የስራ ልምድ ወደ ጎን በመተዉ ፍርድ ቤቱ የተሻረ ህግ በመጠቀም መመሪያ ቁጥር 15/2009 ጂኢጂ መሠረት በማድረግ የስራ ልምድ 100% ግንኙነት ሊኖረዉ ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሰዉ ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል። የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በዚህም መሠረት 2ኛ ተጠሪ መጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የአመልካች የስራ ልምድ ለስራ መደቡ ያለዉ አግባብነት በመመሪያ ቁጥር 20/2011 አንቀጽ 62(3) መሰረት ታይቶ የተሰጠ እንጂ አመልካች እንደሚሉት በመመሪያ ቁጥር 15/2009 መሠረት አለመሆኑን እና ከዚህም አንፃር ሲታይ አመልካች ያላቸዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ1 ወር ሲሆን አቶ ተፈራ ማተቤ የተባሉት ሌላኛዉ ተወዳዳሪ ግን 11 ዓመት ከ7 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑ መረጋገጡን፤ 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በማናቸዉም መንገድ ህግ መጣሱን ወይም አድሎ መፈጸሙን ከደረሰበት ትክክል ያልሆነዉን አሠራር የማስተካከል በአዋጅ ቁጥር 175/2011 አንቀጽ 95 መሠረት ስልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ አድሎ ተፈጽሞብኛል በማለት በአንድ ሠራተኛ የቀረበዉን ጥቆማ መነሻ በማድረግ እንስፔክሽኑ መርምሮ ዉሳኔ መስጠቱ ከስልጣኑ ዉጪ ነዉ ለማለት የሚያስችል የህግ መሠረት የለም በማለት

ተከራክሯል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ስራ መደቡን መስጠቱን ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የ2ኛ ተጠሪን መልስ አስመልክቶ ባቀረበዉ የመልስ መልስ ክርክሩን በማጠናከር ተከራረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም በክልሉ ሲቭል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናዉን ዉሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ በደ/ብ/ብ/ክልል ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ አመልካች የብዙ ዓመት የስራ ልምድ ያላቸዉ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ ለሆነዉ የስራ መደብ በቀጥታ ተያያዥነት ያለዉ 9 ዓመት ከ 1ወር ብቻ መሆኑን እና በአንፃሩ ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ግለሰብ ከ11 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑን፣ በጀኢጀ መመሪያ መሠረት ተቀባይነት ያለዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ብቻ መሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተዉ የደ/ብ/ብ/ህዝቦች መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሲቭል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የደረሰበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ በመቀበል እንዲሁም የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት አመልካች የክልሉ የመንገግስት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 20/11 አንቀጽ 25(4) ላይ በተመለከተዉ መስፈርት መሠረት ለመደቡ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ ሌላኛዉ ተወዳዳሪ አቶ ተፈራ ማተቤ ሲሆኑ አመልካች ይህን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑን አለመሆናቸዉ መረጋገጡን እና የ2ኛ ተጠሪ ቢሮም ህግና መመሪያን በመጣስ የተከናወኑ ተግባራትን የማረም ስልጣን ያለዉ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ያጸና ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሊሚል ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ የሚሰጠዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት

ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የክልሉ ስቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77404 ላይ መስከረም 07 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰበር መ/ቁ/215762

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡1ኛ/ አቶ ጳውሎስ ኦርጂኖ

2ኛ/ ወ/ሮ አመለወርቅ ሁሴን } አልቀረቡም

ተጠሪ፡ አቶ ተስፋዬ ኤጌዶ -- ወኪል ታደሰ ኤጌዶ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ችሎት እንዲታረም በሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸም የሚመለከት ጉዳይ ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- ክርክሩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአሁኑ አመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካቾች በዱራሜ ከተማ ውስጥ

በ460.6 ካ.ሜ ላይ ያላቸውን መኖሪያ ቤት በብር 2,250,000.00 በቀን 24/01/2012 ዓ.ም በተደረገው ውል ሽጠውልኝ ቀብድ ብር 1,000,000 መቀበላቸዉን እንዲሁም የተጠሪ ወኪል በ1ኛ አመልካች የባንክ ሂሳብ ብር 800,000.00 ገቢ በማድረጋቸው በአጠቃላይ ብር 1,800,000.00 የተቀበለ መሆኑን ገልጸ አመልካቾች በውለ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክቡ እንዲወሰን ይህ ካልሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1885(2) መሰረት የተቀበሉትን ቀብድ አጠፌታ እና ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ህጋዊ ወለድ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ባቀረቡት መልስ የቤት ሽያጭ ውል ሲደረግ ቀብድ መሆኑ በውለ ስላልተገለጸ ቀብድ ነው በሚል አጠፌታ መጠየቅ ተገቢ ስላለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 26996 አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠቱን፤በውልም ሆነ በወኪላቸው ገንዘብ ያልተቀበለ ከመሆኑም በላይ የሽያጭ ውለ በሚመለከተው አካል ፊት ያልተደረገ እና ያልተመዘገበ የማይፀና ረቂቅ ውል በመሆኑ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለብንም፣የቀብድ ውል የሌለና የባንክ ሰነድ ቀብድ መሆኑን የሚገልጽ አይደለም፣ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራካራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል በቀን 24/01/2012 ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን፤1,000,000.00 ብር ቀብድ ሳይሆን ለቤቱ ሽያጭ የተከፈለ መሆኑን፤ብር 800,000ለቤት ሽያጭ የተከፈለ አለመሆኑን፤በሽያጭ ከተዋዋሉበት ዋጋ ቀሪውን ብር ተጠሪ ለአመልካቾች ከፍሎ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ከመረመረ በኋላ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህንን ዉሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፡-የሽያጭ ውል ነዉ የተባለዉ 2ኛ አመልካች በሌለሁበት እና ባልፈረምኩበት ድርሻዬን በሚመለከት ልዩ ጥንቃቄ አድርጎ መወሰን ሲገባው እና ተጠሪ የጠየቀው የቀብድ አጠፌታ እንዲመለስ የሚል ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ ከተጠየቀው የዳኝነት ውጪ

የቀብድ ውል የለም ካለ በኋላ የሽያጭ ውል አለ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነዉ፤ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል የለም፤የስር ፍ/ቤት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት ተመዝግቦ ማረጋገጫ ያገኘ መሆን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ የውሉ ሰነድ ከረቂቅ ያለፈ የህግ ጥበቃ የሚያገኝ ሰነድ ስለመሆኑ ሳይመረምር ውል አለ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካቾች የቤት ሽያጭ ውሉን በግልፅ ክደው ተከራክረው እያለ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ፤ተጠሪ ቀሪውን ገንዘብ ከፍሎ ቤቱን ይረከብ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ በአዋጅ ቁ/ 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 15/04/2014ዓ.ም ባቀረበው መልስ በቀብድ ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የአመልካቾች አይደለም በማለት ክደው የተከራከሩትን የስር ፍ/ቤት በፎረንሲክ ምርመራ ፊርማው የአመልካቾች መሆኑ ከማረጋገጡ በተጨማሪም የቤት ሽያጭ ውል መኖሩና በእማኞች ፊት ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ አሳማኝ እና በቂ በሆነ መልኩ በሰውና በሰነድ ተረጋግጦ ይህንን ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ አመልካቾች ስላላቀረቡ የተወሰነ እንጂ አንዳችም መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ሞጉጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካቾች የተቀበሉትን ቀብድ አጠፌታ እንዲመልሱ ወይም በዉሉ መሰረት የሸጡትን ቤት እንዲያስረክቡ የሚል ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ቤት ሽያጭ ዉል የለም፤ቀብድ አልተቀበልንም በማለት መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ዉል መደረጉን ያስረዳል የተባለዉ ሰነድ ላይ ያለዉን ፊርማ በባለሙያ አስመርምሮ እና ዉሉ ሲደረግ እማኝ ነበሩ የተባሉትን ሰዎች ምስክርነት ቃል ሰምቶ የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል በማለት አመልካቾች ቀሪ ገንዘብ ተቀብለዉ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በቅደም ተከተል በይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ በመሆኑ በዉሳኔዉ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ ስልጣን ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራቀኙን ያከራከረዉ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል በፍርድ ሃይል ሊፈጸም የሚችል የቤት ሽየጭ ዉል አለ ወይስ የለም የሚለዉ ነዉ፡፡አመልካቾች አጥብቀዉ የሚከራከሩት የቤት ሽያጭ ዉል የለም፤የቀረበዉ ሰነድም ረቂቅ ነዉ በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል፤ተገደዉ ሊፈጽሙ ይገባል ተብሎ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔና ህጉን የሚቃረን ነዉ በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የዉለታዉ ጉዳይ የሚቻል፣ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ካልሆነ እና ተዋዋይ ወገኖች ፈቅድ ወይም ችሎታ ጉድለት የሌለበት እንዲሁም በህግ የተደነገገዉን የዉል አደራረግ ስርዓት ተከትሎ ተዋዋይ ወገኖች ወደዉና ፈቅደዉ የሚያደርጉት ዉል ህግ ሆኖ የሚያስገድዳቸዉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር1678 እና 1731/1 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ እንደዉሉ ያልተፈጸመለት ወገን አንድም ዉሉ እንዲፈጸምለት ወይም ዉሉ እንዲሰረዝና ኪሳራ እንዲከፈለዉ መጠየቅ ይችላል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1771 ይመለከታል፡፡ ዉሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሚደረገዉ አንድም በህግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱና የዉሉ አደራረግ ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም ዉሉ እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሰናክል ሲፈጠር አሊያም አንደኛዉ ተዋዋይ ወገን ግዴታዉን ለመወጣት የማይችል መሆኑ በማያጠራጥር ሁኔታ ሲረጋገጥ ወይም የዉሉ አይነተኛ ጉዳይ የተነካ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰበት ከሆነ ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808፣1784 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች ይመለከታል)፡፡

የተያዘዉ ጉዳይ ግቀኙን ያከራከረዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ወይም ሌሎች መብቶችን ለማስተላለፍ ወይም ለማቋቋም የሚደረግ ዉል በጽሁፍ እና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግ እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ ድንጋጌ ይዘት ያሥገነዝባል፡፡እንደውለታው ዓይነት ወይም በህግ የተደነገገዉ የጽሑፍ ውል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) እንደተመለከተው በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል አስፈላጊ የሆነውን የውል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡በዚህ አግባብ ያልተደረገ የሽያጭ ዉል እንደረቂቅ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1720(1) እና 1723 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የምዝገባው ሂደት ባልተሟላበት ሁኔታ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ሕጋዊ ነዉ ሊባል እንደማይችል የፌዴራል

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.21448 በሰጠው ግልጽ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በሌሎችም መሰል ክርክሮች ላይ ተመሳሳይ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ሰበር መ/ቁ/34803 ቅጽ8፣መ/ቁ/ 78398 ቅጽ14 እና ሌሎች መዝገቦች መመልከት ይቻላል፡፡የሰበር ችሎት ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 ያላቸውን ልዩነት በግልጽ አስፍሯል፡፡(መ/ቁ21448 ይመለከታል)፡ይኸውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲረጋገጥ (authentication) ሂደት የማድረጉ አስፈሊጊነት በተዋዋይ ወገኖቹ መካከል የፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ (registration) ዓላማ ደግሞ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረዉ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡በሌላ በኩል ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ/36887 በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንዳመላከተዉ በሰበር መ/ቁ/ 21448 ላይ የተሰጠዉ ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም በሚል የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያጠቃልል አይደለም ምክንያቱም በፍ/ብ/ህግ ቁ/1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል በመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ክርክር አመልካቾች በስር ፍርድ በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ዉል የለም፤የቀረበዉ ሰነድም ረቂቅ ነዉ በማለት በግልጽ ተከራክረዋል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የቤት ሽያጭ ዉል አለመፈጸማቸዉን ክደዉ መከራከራቸዉን ያሣያል፡፡አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉል አልፈጸምንም ብለዉ ክደዉ ስለተከራከሩ ዉል እንዲፈጸምለት የጠየቀዉ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩን ማስረዳት የሚችለዉ በህጉ ቅቡልነት ያለዉን ሰነድ በማቅረብ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723(1) እና ከላይ የተጠቀሱት የሰበር ችሎቱ የሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ያስገነዝባል ነዉ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 36887 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ሳይሆን በመ/ቁ/ 21448 እና ሌሎች መሰል ዉሳኔዎች ናቸዉ፡፡በመሆኑም አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉሉን ክደዉ በመከራከራቸዉ ተጠሪ በበኩሉ ዉሉ በጽሁፍ መደረጉን ብቻ ሳይሆን ዉል ለማዋዋል ስልጣን ባለዉ አካል ፊት የተረጋገጠ ዉል በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ተጠሪ ያቀረበዉ ሰነድ በዚህ አግባብ የተረጋገጠ አለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ስርዓቱን ተከትሎ የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ባልቀረበበት ሁኔታ ረቂቅ ነዉ የተባለዉ ሰነድ ላይ ያለዉን ፊርማ እና የምስክሮች ቃል መሰረት አድርጎ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ተረጋግጧል በሚል የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መታረም የሚገባዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል ዉሉ ረቂቅ ነዉ አመልካቾች ተገደዉ የሚፈጽሙት የቤት ሽያጭ ዉል የለም ከተባለ ግራ ቀኙ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ተገቢ ነዉ፡፡ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡ይሁንና ተጠሪ በአማራጭ የጠየቀዉ ዳኝነት አመልካቾች የተቀበሉትን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ክርክራቸዉንና ማስረጃ መርምሮ አመልካቾች የተቀበሉት አንድ ሚሊዮን ብር መሆኑንና ገንዘቡም ቀብድ ሳይሆን የሽያጭ ዋጋ ከፊል ክፍያ መሆኑን አረጋግጧል፡፡አመልካቾች የተቀበሉት ቀብድ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የተቀበሉትን ገንዘብ ያህል መመለስ እንጂ አጠፌታ እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1885(2) እና 1815(1) ድንጋጌ ይዘት ይህንኑ ያመላክታል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾች የቤት ሽያጭ ዉል ክደዉ ተከራክረዉ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ሽያጭ ዉል መደረጉ ተረጋግጧል በሚል አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጡት ዉሳኔ የማይንቀሰቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል አደራረግ ስርዓት በሚመለከት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723/1/ የተደነገገዉን እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 21448 የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4-ሸ/ እና 10(1ሐ) ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉ ላይ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/17102 ላይ በቀን 10/02/2014ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ረቂቅ ዉል እንጂ አመልካቾች ቤት እንዲያስረክቡ የሚገደዱበት በህግ አግባብ የተቋቋመ የቤት ሽያጭ ዉል የለም ብለናል፡፡

3ኛ/አመልካቾች በረቂቅ ዉሉ መሰረት የጠቀበሉትን ብር አንድ ሚሊዮን ክሱ በስር ፍርድ ቤት ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ኪሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

4ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉን ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

5ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ22/03/2014ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ እግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ. 215842
ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሠፋ

ዐሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀመሪያ አህመድ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ የሱፍ ሰኒ
2. ወ/ሮ ዘውዲት አብደላ
3. ወ/ሮ እዮባ ሳኒ
4. ወ/ሮ ሰውዳ ሳኒ
5. አቶ መዘሚል ሳኒ
6. አቶ ሙሃመድአሚን ሳኒ

አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 252680 ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት፥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 199069 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ የአሁን አመልካች እና ከ2ኛ - 6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳዎች በመሆን ተከራክረዋል። አመልካች ንብረቶቹ የሚሸጡ ከሆነ የቀዳሚነት መብቱ ይጠበቅልኝ በማለታቸው ተጠሪዎችም የቀዳሚነት መብት ጠይቀዋል።

አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1060(2) እና 1261 (1) መሰረት ተጠሪዎችም በቀዳሚነት የመግዛት መብት አላቸው፤ ንብረቶቹ በሀራጅ ከተሸጡ የፍርድ ባለመብት እና ባለዕዳዎች እንደማንኛውም ሰው በጨረታው ተወዳድረው ለማሸነፍ ከቻሉ ለመግዛት እንሚችሉ ለፍርድ አፈጻጸም ዳሬክቶሬት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም አመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት እንዲሰጣቸው አመልክተው ተጠሪዎች ጥቅምት 6 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት አስተያየት የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄውን እንደሚቃወሙ እና የቅድሚያ መብት እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበዋል፤ በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ ከሆነ ደግሞ ለአንዱ የጋራ ባለሃብት የቅድሚያ ግዥ መብት የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም፤ ለጋራ ባለሃብቶች ከሌሎች 3ኛ ወገኖች በቅድሚያ የመግዛት መብት ከመስጠት ባለፈ በጋራ ባለሃብቶች መካከል በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ባሉ የጋራ ባለሃብቶች የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ ቢነሳ ከጋራ ባለሃብቶች መካከል ለአንዱ ተለይቶ ሊሰጥ እንደሚችል በህግ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም፤ ስለሆነም አንዱ የጋራ ባለሃብት የቅድሚያ ግዥ መብት እንዲሰጠው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ስምምነት የሌለ መሆኑን ከግራቀኙ ክርክር መረዳት የተቻለ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካች ከሚች ጋር የነበራቸው የጋራ ባለንብረትነት ከሆነ ልክ እንደ ፍርድ ባለእዳ ተቆጥረው የቀዳሚነት መበት ሊሰጣቸው ይገባል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካችን የሚች ሚስት ሆነው እያለ እንደ ወራሽ በመቁጠር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1060(2) መሰረት አመልካች እና ተጠሪዎች የጋራ ባለሃብቶች ናቸው በማለት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1386 እና 1093(2) መሰረት የቀዳሚነት መብት ሊሰጣቸው አይችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤ የተጠሪዎች ጥያቄ የገንዘብ ትርፍ የማግኘት ሲሆን የአመልካች ጥያቄ ደግሞ ከቤቱ ጋር ያላቸው ቁርኝነት ይከበርልኝ ነው፤ ተጠሪዎች አመልካች ያቀረቡትን የቀዳሚነት መብት ባልካዱበት እና የቀዳሚ መብትም ሆነ የመጫረት መብት በግልጽ አቤቱታ ባልጠየቁበት የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች ባቀረበችው የአፈጻጸም ክስ ላይ የሰጡትን መልስ መነሻነት በማድረግ የሰጠው ብይን የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 182 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 33945 እና በመ.ቁ. 54790 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ነው፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ እና ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ በመሆናቸው የቅድሚ መብት ይሰጠኝ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ የመደረጉ አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 443 አተገባበር አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

1ኛ ፣ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በግራ ቀኙችን መካከል የመብት መበላለጥ በሌለበት ሁኔታ ለአመልካች የቅድሚያ መብት የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም፤ በህጉ ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግማሽ ባለድርሻ የሆነ ሰው የቀዳሚነት ድርሻ ይሰጠዋል የሚል ሃሳብ ቢኖር አንኳን ተጠሪዎች የንብረቱን ግማሽ ባለድርሻ በመሆናችን የቅድሚያ መብት ይሰጠን ብለን አንድ ላይ አፈጻጸሙን ሊያዘው ፍርድ ቤት የጠየቅን በመሆኑ የተጠሪዎች ድርሻ ከአመልካች ድርሻ ያንሳል የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፤ ከጅምሩ ቤቱ ለኪራይ አገልግሎት ሲውል የነበረ ስለሆነ በቤቱ አካባቢ ማህበራዊ ግንኙነት አልተመሰረተም፤ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 33945 እና በመ.ቁ. 54790 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለግራ ቀኙችን አፈጻጸም ክርክር አግባብነት የለውም፤ በስር ፍርድ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ውጪ አመልካችን ጨምሮ የፍርድ ባለዕዳዎች መሆናችን በግልጽ ተሰይመን ባለበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪዎች በተለየ መልኩ ቅድሚያ የማግኘት መብት የላትም፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን እንደወራሽ ቆጥሯል በሚል የቀረበው ክርክር ሀሰት ነው፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ እና ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አመልካች መጥሪያ ስለማድረሳቸው በድጋሚ ቃለመሃላ ሰላቀረቡ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ስለሆነ መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጠ ውሣኔ እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማረናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት የግዢ ቅድሚያ መብት እንዲሰጣቸው ያመለከቱ መሆኑን እና ተጠሪዎች በቀረበው ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በፍ/ቤቱ ተጠይቀው የቅድሚያ መብት ጥያቄውን የማይቀበሉ እና የማይስማሙ መሆኑን ገልፀው የቅድሚያ መብት ግዢ እንዲፈቀድላቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀው የነበረ መሆኑን ከክርክሩ ይዘት ተመልክተናል።

እያከራከረ ያለው ንብረት በባልና ሚስት የተፈራ እና ባል በሞት በመለየታቸው ምክንያት የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ቀርቦበት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በመወሰኑ ምክንያት የቅድሚያ የመግዛት መብት ይገባኛል ጥያቄ ነው።ይህንኑ አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/88275፣160198፣168192 እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የባልና ሚስት የጋራ

ንብረት ክፍፍል ስርዓት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግጋት መንግስታት የተረጋገጠውን የእኩልነት መብት መሰረት አድርጎ መከናወን ያለበት መሆኑን፣ ክፍፍሉ የሚከናወንበት ስርዓትም የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀፅ 90 እስከ 93 ድረስ በቅደም ተከተል ባስመቀጣቸው መንገዶች መሆን፣ የጋብቻ ውጤት የሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍል ሊከናወን የሚገባው የእኩልነት መርህን መሰረት አድርጎና የተጋቢዎችን ፈቃድ በመመርኮዝ መሆኑን፣ የተጋቢዎች ስምምነት ከሌለ ደግሞ ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በሕጉ የተመለከተውን ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ሊሆን እንደሚገባ በመግለጽ ወስኗል። ይህ ስርአትም በአፈፃፀም ጊዜም ልንከተለው የሚገባ ሥርአት መሆኑን ከውሣኔው ይዘት መገንዘብ

የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል በሚከናወንበት ጊዜ የእኩልነት መርህን የተከተለ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የጋራ ንብረት ክፍፍል በሚፈፀምበት ጊዜም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ድንጋጌዎች መርህ አንፃር ግራ ቀኙ ከተስማሙ በዓይነት የሚካፈሉበት ይህ ካልሆነ ደግሞ በገበያ ዋጋ በጨረታ ተሸጦ እኩል ሊካፈሉ እንደሚገባ አስቀድሞ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 37508 እና 35003 በሆነው መዝገብ ላይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል። ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪዎች የድርሻ ክፍፍል ይደረግልን የሚሉ ቢሆኑም የሚከፋፈሉት ንብረት አመልካች እና የአመልካች ባለቤት የነበሩት የተጠሪዎች አባት በጋራ ያፈሩትን ንብረት በመሆኑ ተጠሪዎች ሟቹን የጋራ ባለሀብት ተክተው የአባታቸውን ድርሻ ለመካፈል በመሆኑ በንብረቱ ላይ እኩል ባለድርሻ ናቸው። በመሆኑም የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚስተናገደው የእኩልነት መርህን ተከትሎ በመሆኑ አመልካች የግዢ ቅድሚያ መብት ይሰጠኝ ብለው የጠየቁ ቢሆንም ተጠሪዎች ግን ቅድሚያ ግዢ መብት ለአመልካች ሊሰጥ አይገባም ይልቁንም ለእኛ ነው ቅድሚያ ግዢ መብት ሊሰጠን የሚገባው በማለት የተከራከሩ በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል በግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ላይ ስምምነት ያለመገኙቱን ተረድተናል።

በመሆኑም የግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ላይ ግራ ቀኙ ያልተስማሙ በሆነ ግዜ የግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ከግራ ቀኙ ለአንዱ ሊፈቀድ የሚይገባው እና ንብረቱ በጨረታ ተሸጦ ክፍፍል የሚደረግበት ሲሆን ነገር ግን ግራ ቀኙ እንደማንኛውም ተጫራች በጨረታው ተወዳድረው ንብረቱን ማስቀረት ከሚችሉ በቀር የቅድያ መብት ጥያቄው ለእኔ ሊሰጥ ይገባው ነበር በሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለን ተከታዩን ወስነናል።

ውሣኔ

1) *የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ/ 199069 በ30/11/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 252680 በ23/2/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል።*

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

3) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ታ

የሃሣብ ልዩነት

እኔ በአራተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ ግራ ቀኙ ባልተስማሙበት የግዢ ቅድሚያ መብት ሊጠበቅ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማፅናት በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ ያለኝን የልዩነት ሀሳብ እንደሚከተለው አሰፍሬያለሁ ፡፡

አመልካች የተቀዳሚነት መብት ይሰጠኝ አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.443 መሰረት ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በአፈፃፀም ምክንያት የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት ከሆነ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ ቀርቦ በንብረቱ ላይ ድርሻ ከሌለው የጨረታው ተሳታፊ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ በንብረቱ ላይ ድርሻ ላለው የጨረታ ተሳታፊ የቅድሚያ መብት የሚሰጥበትን የህግ አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በኔ እምነት በሰ/መ/ቁ.160198 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይህንን የድንጋጌውን መንፈስ የተከተለ ነው ብዬ ስማላምንና በድንጋጌው ላይ በምንም መልኩ ያልተካተተውን የንብረቱን ተጋሪዎች ስምምነት በመስፈርትነት ያስቀመጠ የህግ ትርጉም በመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔው በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 27 መሰረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ለተሰየሙበት የሰበር ችሎት ቀርቦ አስገዳጅ የህግ ትርጉሙ ሊሻሻል ይገባል እንጂ ይህንን አስገዳጅ የህግ ትርጉምና በሰበር መ/ቁ.168192 የተሰጠውን ከሀራጅ ሽያጩ በፊት ስላለው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በስምምነት አንዱ ወገን የሌላኛውን ድርሻ ከፍሎ ስለሚያስቀርበት አግባብ ትርጉም የተሰጠበትን እንዲሁም በሰ/መ/ቁ.88275 መልሶ ስለመግዛት መብት (Recovery Right)

የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና አይገባም ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቼ በሀሳብ ተለይቼያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 216018

ሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ወዕሚቹ በግጁ - ወኪል ከበደ ለንኩቦ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- አቶ ደምሴ ሲራጅ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በገጠር የእርሻ መሬት ላይ ተፈፅሟል የተባለን ሁከት ለማስወገድ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17163 ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

በከምባታ ጠንባሮ ዞን ጠንባሮ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጀመረው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥቅምት 9 ቀን 2013 ዓ/ም ፅፋ ባቀረበችው ክሷ የይዞታውን አዋሳኝ በመዘርዘር ሕጋዊ ይዞታዋና በይዞታዋ ላይ የሚገኘውን ባህር ዛፍ ተጠሪ በሰሜንና ምዕራብ በኩል ከ2012 ዓ/ም ጀምሮ ሁከት እየፈጠረባት በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ ያቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የይዞታውን አዋሳኝ በመዘርዘር ከሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በእጁ አድርጎ የሚጠቀምበት ይዞታው እንጅ የአመልካች አለመሆኑን ሁከትም አለመፍጠሩን ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤቱም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታና ንብረት የማን ነው? ተከሳሽ የፈጠረው ሁከት አለ? ወይስ የለም? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን ለማጣራት ግራ ቀኙ ያቀረቧቸው የሰው ትን ምስክርነት እና የሰነድ ማስረጃዎች ያረጋገጡን ፍሬ ነገር፤በቦታው በመገኘት ስለይዞታው እውቅና ያላቸውን ሰዎችን ጠይቆ ያገኘውን እውቀት እንዲሁም የሚመለከተው የመሬት አስተዳዳር አካል ማስረጃ እንዲቀርብ አዝዞ የተላከለት መልስ በማጣመር ከመረመረ በኋላ አመልካች የአከራካሪው ይዞታና ንብረት ባለይዞታም ባለንብረትም ስለመሆኗ አለመረጋገጡ፤ ይልቁንም ይዞታውን አመልካችና ተጠሪ በጋራ የሚጠቀሙበት መሆኑን ፤ባህር ዛፍ የተጠሪው ንብረት ስለመሆኑ መረጋገጡን ዘርዝሮ በተጠሪው የተፈጠረባት ሁከት የለም ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው በሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች በመፅናቱ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡አመልካች ሕዳር 1 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታዋ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ አመልካች ግብር የምትከፍልበት ይዞታ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቅርባ ባረጋገጠችበትና ደብተሩ ባልተሻረበት የሥር ፍ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪ ነው ሲል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲታረምላት ጠይቃለች፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ በአመልካች ስም በተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር 0434564 ተ.ቁ.1 ላይ ተመዝግቦ ሣለና ማረጋገጫው ባልተሻረበት ይዞታው የተጠሪ ነው በሚል ምክንያት ሁከት የለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት እንዲመረመር ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲቀርብ የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ተልኮለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ በቃለ-መሐላ በመረጋገጡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ ክርክሩ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ሣለ ይዞታውን በጋራ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ተርጋግጧል በሚል ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከመሠረታዊ የሕግ መመዘኛ መርህ አንፃር መመርመር እንዳለበት ታምኖበት በዚህ መሠረት ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ በሕጋዊ ይዞታዋና በንብረቷ ላይ ተጠሪ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሁከት የፈጠረባት መሆኑን በመግለፅ ሁከቱ እንዲወገዱላት በመጠየቅ ማስረጃዎች አቅርባለች፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ይዞታውን ከኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ይዞ የሚጠቀምበት የግሉ ይዞታ እንጅ የአመልካች አለመሆኑን በአመልካች ይዞታ ላይ ሁከት አለመፍጠሩን ተከራክሯል፡፡

የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን በሕግ የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ የቀረበለትን እንዲሁም በቦታው ተገኝቶ ካጣራ በኋላ ይዞታውን በሚመለከት በጋራ የሚጠቀሙበት መሆኑን ባሕር ዛፉን በሚመለከት ግን የተጠሪው ንብረት መሆኑን

አረጋግጧል፡፡ በአጣሪ ችሎቱ እንዲጣራ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሥር ፍርድ ቤትም የቀረበ ማስረጃ ነበር፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የማን እንደሆነ መሬትን ከማያስተዳድረው አካል ማስረጃ እንዲቀርብለት ጠይቆ የቀበሌው አስተዳዳር ይዞታው በጋራ የሚጠቀሙበት መሆኑን ሲያ ረጋግጥ፤ የወረዳው የመሬት አስተዳዳር በበከሉ የግራ ቀኙ ይዞታ በሚመለከት ማስረጃ የሌለው መሆኑን ገልጧል፡፡ ይህን ማስረጃ የፍትሐ ብሔር ማስረጃ ምዘና መርህን መሠረት በማድረግ የመዘነው የሥር ፍርድ ቤት ይዞታውን በጋራ የሚጠቀሙበት መሆኑ ተረጋግጧል አመልካችም ሁከት አልፈጠረም ሲል ወስኗል፡ አከራካሪውን ይዞታ ግራቀኙ በጋራ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ በአስተዳደሩም ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ባቀረበችው ማስረጃ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ ይዛ እንድትጠቀምበት የተፈቀደላት ቢሆን ኖሮ አስተዳደሩ ይዞታው የማን እንደሆን እውቅና የለኝም ሲል መልስ ሊሰጥበት የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ድንጋጌ መሠረት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሠረታዊ የሕግ አተርጓጎም ችግርን ማረም እንጂ ማስረጃ መዝኖ ፍሬ ነገርን ማጣራት አይደለም፡፡ በቀረበው ጉዳዩም ማስረጃ ምዘናን በሚመለከት እንጂ የሕግ አተረጓጎም ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17163 ጥቅምት 21 ቀን 2013ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው በአመልካች ይዞታ ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ብለው በወሰነው ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ ፀንቷል፡፡
2. ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራቁኙ የየራሣቸውን ይቻሉ
3. መዝገበ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ. 216155

ቀን ፡- ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ታደሰ ጉታ፡- ጠበቃ አበበ ጉታ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

2. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ } ዓ/ሕግ መሀመድ

3. የጅግጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት } ሁሴን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ለመስራት ውል ገብቼ በርካታ ማሽነሪዎችና ዕቃዎችን ወደግንባታ ቦታው ወስጃለሁ፡፡ ለግንባታው ለሚጠይቀው ከፍተኛ ገንዘብ ሲባል በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን በማሲያዝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና መጋዘን፣ ወርክሾፕና የሌሎች ሰዎችን ንብረት በማሲያዝ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ገንዘብ በመበደር የግንባታ ፕሮጀክቶችን በመፈጸም ከፍተኛ የሆነ ብደርና ዕዳ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያለምንም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጥፋት የግንባታ ሥራ ውሉን በመቋረጥ ለመረጧቸው ሌሎች የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በንዑስ ግንባታ የሥራ ውል አስተላልፈዋል፡፡ ማሽነሪዎች፣ መኪናዎች እና ዕቃዎች ከሶማሌ ክልል እንዳይወጡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሰጡት ሕገ-ወጥ የዕግድ ትዕዛዝ ከማገዳቸውም በተጨማሪ ንብረቶችን እያከራዩ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲጠቀሙባቸው ነበር፡፡ 1ኛ ተጠሪ መፍትሔ እንዲሰጠኝ ብጠይቅም ምላሽ ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ ስለሆነም፡-

1. ከ1991 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ማሽነሪዎችና መኪናዎች ባከራይ ላገኘው የምችለው ገቢ ስለተቋረጠ የኪራይ ገንዘብ ብር 127,938,480.00 እና ወለድ ብር 15,890,976.14 በድምሩ ብር 143,829,456.14 እንዲከፍሉ፣
2. ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የሸጠው በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 32,000,000.00 እንዲከፍሉ፣
3. ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የሸጠ በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00 እንዲከፍሉ፤
4. በሪቴንሽን የተያዘ ገንዘብ ብር 176,566.40 በድምሩ ብር 192,457,377.62 እንዲከፍሉ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ አመልካች ውል ያደረጉት ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ሊከሰስ አይገባም፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው፡፡ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ ውሉ የተቋረጠው በአመልካች ጥፋት ነው፡፡ የተበደሩት ለፕሮጀክቱ አይደለም፡፡ ማሽነሪዎችና ዕቃዎች ከሕግ ውጭ አልተያዙም፣ የተያዙት አመልካች እንደ ውሉ ያልፈጸመው መኖሩን እስኪረጋገጥና በፍርድ ቤት እግድ ነው፡፡ የተጠየቀው የጉዳት ካሳ የተጋነነ ነው፤ ለክሱ ኃላፊነት የለብንም ብለዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ውደቅ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ የተከሰሰው የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የበላይ አካልና ተቆጣጣሪ ከመሆኑም በላይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የፈጸሙት ተግባር መፍትሔ እንዲሰጥ ሲጠየቅ ምላሽ ያልሰጠ በመሆኑ በሕግ ያለበትን ኃላፊነት አልተወጣም በመባሉ ስለሆነ ክሱ በእርሱ ላይ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ የአመልካች ንብረት የሆኑትን ማሽነሪዎች ተጠሪዎች በመያዝ አመልካች ጥቅም ያጡ በመሆኑ ቢያከራዩ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ብር 96,447,600.00 እንዲሁም ሪቴንሽን ገንዘብ ብር 176,566.40 ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የሚከፈል በመሆኑና አመልካች ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ተይዘው ለቆዩበት ጊዜ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው ስለተወሰነ በባንክ የተሸጡ ንብረቶች ዋጋ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ከደረሰባቸው ጉዳት በላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ማሽነሪዎች በተጠሪዎች መያዛቸው አከራይቹ አገኝ ከነበረው ገቢ በተጨማሪ ተደራራቢ በገንዘብ ሊተመን የሚችል እና ሊተመኑና ዋጋ ሊወጣላቸው የማይችል ተደራራቢ ጉዳቶች ደርሰዋል፡፡ ማሽነሪዎች በመያዛቸው ሰርቼ ብደሩን መክፍል እንዳልችል አድርገው ንብረቴ የተሸጠ በመሆኑ በባንክ የተሸጡትን ንብረቶች የገበያ ዋጋ ብር 46,650,000.00 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች በባንክ ዕዳ ንብረቴ ተሸጦ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የጠየቁት ዳኝነት ውድቅ መደረጉ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከፍ/ሕ/ቁ. 2091 አንጻር ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘትም ለክሱ ኃላፊነት የለብንም፣ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204625 አቅርበን በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ አመልካች ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ካሣ እንዲከፈለው ስለተወሰነ በሐራጅ ለዕዳው በባንክ የተሸጡ ንብረቶችን ዋጋ ልንከፍል አይገባም፡፡ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ ከ1991 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ማሽነሪዎችና መኪናዎች ባከራይ ላገኘው የምችለው ገቢ ስለተቋረጠ የኪራይ ገንዘብ ብር 127,938,480.00 እና ወለድ ብር 15,890,976.14 በድምሩ ብር 143,829,456.14፣ ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የሸጠው በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 32,000,000.00፣ ማሽነሪዎችና መኪናዎች ከሕግ ውጭ በመያዛቸው ከባንክ የተበደርኩትን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሌ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የሸጠ በመሆኑ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00፤ በሪቴንሽን የተያዘ ገንዘብ ብር 176,566.40 በድምሩ ብር 192,457,377.62 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለክሱ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የውል ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በክስ ማመልከቻ የጠቀሱ በመሆኑ የቀረበው ዳኝነት በውል ግንኙነት መሠረት የተያዘ ገንዘብ ክፍያ እንዲፈጸም እና የውል ጉዳት ኪሣራን የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አመልካች የውል ግንኙነት የሌላቸው ሲሆን ክሱ በ1ኛ ተጠሪም ላይ የቀረበው አመልካች ውል የወሰዱበትን ሥራ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ለ3ኛ ወገን በማስተላለፍ ሂደት ላይ በመሳተፍና ለደረሰብኝ ጉዳት መፍትሔ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው ካለበት ኃላፊነት አንጻር ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠት ጉዳት እንዲደርስበኝ አድርጓል በሚል ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ ሁለት የክስ ምክንያቶች ተጣምሮ የቀረበበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ የአመልካች ንብረት የሆኑትን ማሽነሪዎች ተጠሪዎች በመያዝ አመልካች ጥቅም ያጡ በመሆኑ ቢያከራዩ ሊገኝ የሚችለው ገቢ ብር 96,447,600.00 እንዲሁም ሪቴንሽን ገንዘብ ብር 176,566.40 ተጠሪዎች ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል፤ ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የሚከፈል በመሆኑና አመልካች ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ተይዘው ለቆዩበት ጊዜ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው ስለተወሰነ በባንክ የተሸጡ ንብረቶች ዋጋ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ከደረሰባቸው ጉዳት በላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ጉዳይ ተጠሪዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204625 ያቀረቡት ይግባኝ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከማሽነሪዎች ሊገኝ ከሚችለው የተቋረጠ ገቢ በተጨማሪ በባንክ ዕዳ ለተሸጡ ንብረቶች የገበያ ዋጋም ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል የሚል ነው፡፡ ውል ያልፈጸመ ወገን በፍ/ሕ/ቁ. 1790 እና 1791 እንደተመለከተው ያልተፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውል ያልፈጸመው ወገን የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት፡፡ የሚከፈለው ኪሣራ ተዋዋዮች በፍ/ሕ/ቁ. 1889 መሠረት አስቀድመው የወሰኑት ከሆነ በውሉ የተመለከተውን መጠን ሲሆን ተዋዋዮች አስቀድመው ኪሣራውን ካልወሰኑ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤት ኪሣራውን በማስረጃ አጣርቶ የሚወሰንው ይሆናል፡፡ ከውል ውጭ ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ሲሆን ካሣ በፍ/ሕ/ቁ. 2090(1) እንደተመለከተው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት መርህ ተቀምጧል፡፡ ሕጎቹ የተለያዩ ቢሆኑም ልዩነቱ ካሣው የሚከፈልበት ግንኙነት መሠረት እንጂ ዓላማቸው ተመሳሳይ ነው፤ እርሱም ጉዳት የደረሰበትን ሰው መካስ ነው፡፡ ሕግ አውጪው ሕግ ሲያወጣ ጉዳት የደረሰበት ሰው ከጉዳቱ እንዲያተርፍ ታሳቢ አድርጓል ሊባል አይችልም፡፡

አመልካች ንብረቶቻቸው ከውል እና ከሕግ ውጭ በተጠሪዎች ተይዘዋል በሚል በንብረቶች ሊያገኙት ይችሉት የነበረው ገቢ ታስቦ በሥር ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ አመልካች በብድር ለወሰዱት ገንዘብ ባለመክፈላቸው ንብረታቸው ተሸጦ ዕዳው መከፈሉን በመጥቀስ ማሽነሪዎች በተጠሪዎች ባይያዙ ኖሮ ዕዳውን ሰርቼ በመክፈል ንብረቶችን ማስቀረት እችል ስለነበር ለጉዳቱ ተጠሪዎች ካሣ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ንብረታቸው በሐራጅ የተሸጠው ለወሰዱት ዕዳ ክፍያ በመሆኑ እንደጉዳት የሚታይ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ማሽነሪዎቹ በእጃቸው በቆዩ ከገቢው ቀንሰው ለዕዳው ክፍያ ሊያውሉት የሚችሉ በመሆኑና በሥር ፍርድ ቤት የ14 ዓመት ሙሉ ገቢ የተወሰነላቸው በመሆኑ፤ ለተሸጠው ንብረት ዋጋ በተጨማሪነት ከታሰበላቸው ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝና ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚለውን መርሕ የሚጥስ ትርፍ ክፍያ ስለሚሆን የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥሩ 1036(ሐ) የሆነ ቤትን የገበያ ዋጋው ብር 32,000,000.00 የሆነ እና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መጋዘን፣ ወርክሾፕና ቢሮ የንብረቱ የአሁን የገበያ ዋጋ ብር 14,650,000.00 ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 204961 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 236316 የካቲት 18 ቀን 2013 ዓ/ም በባንክ ዕዳ ለተሸጡ ንብረቶች ዋጋ ተጠሪዎች የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በሚል የሠጡት ውሳኔ ክፍል በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 216200

ቀን ፡- ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፍሬሕይወት ይልማ- ጠበቃ አምሀ ጌታቸው- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፋና ቦሌ ሸማቾች ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማሕበር- ጠበቃ ንጉሴ ጫኔ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ክስ በተጠሪ ማሕበር በምግብና መጠጥ ቁጥጥር ዋና ክፍል ኃላፊነት የሥራ መደብ ተቀጥሬ ስሰራ ከሕግ ውጭ የሥራ ውሌን በማቋረጡ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ሕግና በተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በሽምግልና ዳኞች እንዲታይ ዳኛ ለማስመረጥና ለማስመደብ ክስ አቅርቤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94768 ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች ሳይሆን በሥራ ክርክር ችሎት ነው የሚታይ በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ ሆነ በሰበር ችሎት ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ የሥራ ክርክር ችሎት ክሴን ተቀብሎ ወደሥራ እንድመለስ እንዲወሰንልኝ፣ ተጠሪ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት

ቅጣት፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ፣ በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ፣ በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈለኝ የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈለኝ፣ የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል። አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች የሥራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይገባም፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረቡትን መቃወሚያዎች መርምሮ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) የተመለከተውን የሥራ መሪ መስፈርት የማያሟሉ በመሆኑ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለሥራ ክርክር ችሎት መቅረቡ ተገቢ ነው። አመልካች የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከሁለት ዓመት በኋላ ያቀረቡት ክስ ሲሆን ቀደም ሲል በሌላ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 16648 በሠጠው ትርጉም መሠረት ይርጋን የማያቋርጥ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(4) መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውድቅ በማድረግ ወስኗል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16648 የሰጠው ትርጉም በመለወጥ በመዝገብ ቁጥር 36730 (በቅጽ 9 እንደታተመ) ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ ክርክር ላይ መቆየቱ ይርጋን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት መሆኑ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል። ነገር ግን አመልካች ቀደም ሲል ያቀረቡት ክስ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ክስ እስካቀረቡበት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ የሦስት ወርና የስድስት ወር ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም አሁን ከተያዘው ጉዳይ በፊት የቀረበው ክስ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 237627 እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ሄዶ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ እስከ ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ይርጋው እንደተቋረጠ መወሰድ ሲገባው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠበት ጊዜ መሠረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የቀደመው ክስ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ተወስኗል ከተባው አንጻር ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 ከሠጠው ትርጉምና ከአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ አኳያ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል። ተጠሪ ያቀረበው መልስ የቀድሞው ክርክር ከተወሰነ በኋላ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ስድስት ወር ጊዜ አልፏል። ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ካለ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ማቅረብ ሲገባቸው መዘግየታቸው ቸልተኛ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል። አመልካች የመልሰ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረቡት በተጠሪ ማሕበር ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ሕገ-ወጥ በመሆኑ ወደስራ እንዲመልሰኝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች ክሳቸውን የመሰረቱት አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ተፈጻሚ አድርገዋል፡፡ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም ነው፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 190(5) ላይ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ያለው ሲሆን በዳኝነት አካል ላይ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ጊዜ በነበረው ሕግ መሠረት ፍጻሜ እንደሚያገኙ አስቀምጧል፡፡ በመርሕ ደረጃ መሠረታዊ ሕግ ተፈጻሚ መሆን ያለበት በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በተከሰቱ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ለተጠሪዎች የሥራ ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነው ድርጊት የተከሰተው አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ስለሆነ የተግባሩ ሕጋዊነትም ሆነ መብቱ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ መመርመር ያለበት ይሕንኑ ሕግ መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ወደሥራ መመለስ፣ ወደሥራ መመለስ የማይችሉ ከሆነ የሕገ-ወጥ ስንብት ውጤቶች የሆኑ ክፍያዎች እንዲሁም በሥራ ላይ እያሉ በ2006 ዓ/ም ያልተከፈላቸው ክፍያ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ለቀረበው ክስ ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የይርጋ ክርክሩ የቀረበው አመልካች ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው (limitation of action) አልፏል በሚል ነው፡፡ ይርጋ መብትን (extinctive prescription) ወይም መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን ቀሪ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደተጠየቀው ዳኝነት ዓይነትና ባሕሪ የይርጋ ጊዜው ሆነ መብቱ የሚጠየቅበት ጊዜ የተለያየ ነው፡፡ ወደሥራ ለመመለስ የሚቀርብ ዳኝነት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(2) መሠረት የሥራ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ የሥራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የሚጠየቁ ክፍያዎች ደግሞ በአንቀጽ 163(4) መሠረት በስድስት ወር ጊዜ መቅረብ አለባቸው፡፡ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የደመወዝ ወይም ማንኛውም ሌላ ክፍያዎች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) መሰረት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 163(1) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ተያያዥ የሆኑ ዳኝነቶችን ከጥር 04 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ በሦስት ወር ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መጠየቅ አለባቸው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ጊዜው ካለፈ በኋላ ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው ግን በሕግ አግባብ ሊቋረጥና እንደ አዲስ መቆጠር ሊጀምር ይችላል፡፡ የአመልካች ክርክር የተመሰረተውም ይርጋው ቀደም ሲል በተደረገ ክርክር

ተቋርጧል በሚል ነው፡፡ በሕጉ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች የተመለከቱ በመሆኑ ከቀረበው ክርክር አኳያ ጉዳዩን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 164 ላይ ሦስት የይርጋ ጊዜ ማቋረጫ ያለ ሲሆን የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ክስ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚሰጠበት ቀን ድረስ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም ኃላፊነት በተሠጠው አካል አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ እና መብቱን በጽሁፍ ሲያምንለት ወይም በከፊል ሲፈጽምለት ናቸው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ ቀደም ሲል ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ያደረጉት ክርክር ይርጋውን ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 የሰጠውን ትርጉም መሠረት አድርጎ ወስኗል፡፡ ነገር ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ያለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ሥልጣን የለኝም ያለው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስቀረበበት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ የሦስት ወር ሆነ የስድስት ወር ይርጋ ጊዜ አልፏል በማለት ነው፡፡ አመልካች በክስ አቤቱታቸው እንደገለጹትና በቀደመው ክርክር ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማያያዝ ይርጋው ሊቋረጥ የሚገባው የመጨረሻውን ፍርድ በሰበር ችሎት ከተሰጠበት ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 በሰጠው ትርጉም በዋናነት ካስቀመጣቸው ምክንያቶች መካከል የዳኝነት አካል ክስ ሲቀርብለት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመጀመሪያ ተመልክቶ ወደክርክሩ ሳይገባና ተከሳሽ የሆነውን ወገን ሳይጠራ ክሱን በመሰረዝ ተከራካሪዎች ጊዜ እንዳያባክኑና መብታቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ መወጣት ያለበትን ኃላፊነት ባልተወጣበት ሁኔታ በክርክሩ የወሰደው ጊዜ ላይ የይርጋ ጊዜውን መቁጠር ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም የይርጋ ደንብ ከዓላማዎቹ አንዱ የማይተጋና ዳተኛ የሆነን ባለገንዘብ መቅጣት እንጂ መብቱን ለማስከበር ጥረት የሚያደርገውንና ትጋት ያለውን ከሳሽ መብቱን እንዳይጠቀም ማድረግ አይደለም የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አሁን ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት በሽምግልና ዳኞች እንዲታይ ባቀረቡት ክስ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94768 ክርክር ሲያርግ ቆይቶ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውን በመጠቀም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237627 አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ/ም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ለሰበር ችሎት አያስቀርብም ተብሎ ተሰርዟል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በመጀመሪያና በይግባኝ ደረጃ በክርክር መቆየቱ እንዲሁም አመልካች መብታቸውን ለማስከበር ትጋት ሲያደረግ የነበረ መሆኑ ሲታይ ክስ የማቅረቢያ የይርጋ ጊዜው የቀደመው ክርክር ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከተሰጠበት ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ መቋረጡን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዙ ዳኝነቶች ይርጋ ጊዜያቸው እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምረው ከሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ይሆናል፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች ወደሥራ ለመመለስ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ዳኝነኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(2) መሠረት

የሥራ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ ይርጋው እንደ አዲስ መቆጠር ከጀመረበት ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ሦስት ወር ሲቆጠር ከመስከረም 09 ቀን 2013 ዓ/ም ላይ የይርጋ ጊዜው የሚያልፈበት በመሆኑ አመልካች ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ወደሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። የሥራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የሚጠየቁ ክፍያዎች፤- ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የቀረበው ዳኝነትና የመዘግየት ቅጣት በአዋጁ አንቀጽ 163(4) መሠረት በስድሰት ወር ጊዜ መቅረብ አለባቸው። ከሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ስድስት ወር ሲቆጠር እስከ ታህሳስ 09 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ ሲሆን አመልካች የይርጋ ጊዜው ሳያልፍ ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የተጠየቁ ክፍያዎች በይርጋ ቀሪ አይሆኑም፤ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነቱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የደረሱበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። የሥራ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(1) መሠረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚጠየቅ በመሆኑና አመልካች ጊዜው ሳይደርስ ዳኝነት ያቀረቡ ስለሆነ ዳኝነቱ በይርጋ ሊታገድ አይገባም ብለናል።

በሌላ በኩል ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የደመወዝ ወይም ማንኛውም ሌላ ክፍያዎች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) መሰረት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ተደንግጓል። አመልካች ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ያልተያያዘ በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል። ክፍያዎቹ የአመልካች የሥራ ውል ከመቋረጡ በፊት ክፍያው ከበሰለበት ጊዜ ጀምሮ ሊጠየቅ የሚችል ነው። አመልካች ክፍያው አጠቃለው መጠየቅ የነበረባቸው እስከ 2007 ዓ/ም አጋማሽ ድረስ ነው። ክፍያውን ለመጠየቅ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ በ2007 ዓ/ም ያለፈ በመሆኑ ይርጋ ጊዜው ያለፈ ነገር ሊቋረጥና እንደ አዲስ ሊቆጥር ስለማይችል በ2011 እና በ2012 ዓ/ም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ክርክር የ2006 ዓ/ም ደመወዝና በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ከ2006 ዓ/ም እስከ 2007 ዓ/ም አጋማሽ ወራት ድረስ መጠየቂያ ጊዜው ያለፈን ክፍያ አዲስ መብት የሚሰጥ አይደለም። ስለሆነም አመልካች በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 274543 ነሀሴ 13 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121389 ሚያዚያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. አመልካች ወደሥራ ለመመለስ እና በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ የታገደ ነው መባሉ ተገቢ ስለሆነ ፀንቷል፡፡

3. አመልካች ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የቀረበውና የመዘግየት ቅጣት እንዲሁም የምስክር ወረቀት ይሰጠኝ በሚል ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡

4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሰቀስ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በማከራከርና ተገቢ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት እንደየአግባብነቱ በውሳኔ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተመለከቱ ዳኝነቶች ላይ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ የስር መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ
አለበ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 216211

ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጆኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሸምሱ አሊ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ላይላ ኢታጎ- ቀርቧል

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የአመልካች ጠበቃ ወላጅ እናት ሲታመሙ ቆይተው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ጠበቃው እናታቸውን ስያስታምሙ እና በሀዘን ላይ በመቆየታቸው ምክያንት የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸው መሆኑን በመግለጽ ሁለት የሰው ምስክሮች በመዘርዘር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበ አቤቱታ ቃለ መሃላው ሳይታይና የተቆጠሩት ምስክሮችም ሳይሰሙ ያለምንም ማስረጃ የቀረበውን ጊዜ ያለፈበት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ በቂ ምክንያት የለውም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም አመልካች ህዳር 6 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ በግራቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተነሳውን የንብረት ክርክር በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አይቶ በሥር ፍርድ ቤት ተጣሪቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባዋል ያለው ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍርድ ቤት ከመለሰ በኋላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የይግባኝ ቅሬታው የተዘጋጀ ቢሆንም ሲታመሙ የቆዩት የአመልካች ጠበቃ ወላጅ እናት ሚያዝያ 20 ቀን 2013 ዓ/ም ሞተው ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ/ም የቀብር ሥርዓታቸው በመፈፀሙ ምክንያት በወቅቱ ይግባኝ ማቅረብ ስላልቻሉ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችሉ እንድፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ታዘው በሰጡት ምላሽ የጠበቃው እናት ስለመሞታቸው ከሚመለከተው ወሳኝ ኩነት ወይንም ከአከባቢው እድር የቀረበ የሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ ክርክሩን በሰው ማስረጃ ለማስረዳት ማስረጃ መቆጠሩ ተገቢ ስላልሆነ የቀረበው ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የምክንያቱን በቂ መሆን አለመሆን በጭብጥነት ይዞ እንደመረመረው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው የሚያበቃው ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ/ም ሲሆን ውሳኔው ከተሰጠበት የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሚያዝ 20 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ ይግባኝ ያልቀረበበት ምክንያት ያልተገለፀ ሲሆን ውሳኔ የተሰጠ ቀን አመከልካች ስላልቀረቡ በሥር ፍርድ ቤት በጠበቃ መከራከሩን ውሳኔው የማያመለክት ከመሆኑም በላይ የጠበቃው እናት መታመም ሆነ መሞት አመልካች የተዘጋጀውን ቅሬታ ማቅረብ የማይከለክል በመሆኑና አመልካች የጠበቃዬ እናት ሞተዋል ከማለት ባለፈ የጠበቃው እናት ማን እንደሆኑ ፣ የሞቱበት አከባቢ የት እንደሆነ ያልተገለፀ እንዲሁም የጠበቃው እናት ስለመሞታቸው ከሚመለከተው የመንግስት አካል ወይንም ከአከባቢው ዕድር የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር ክርክሩን በሰው ምስክር ለማስረዳት መቅረቡ ተአማኒ ባለመሆኑ አመልካች ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ያቀረበው አቤቱታ በበቂና አሳማኝ ምክንያት የተደገፈ ባለመሆኑና የይግባኝ ጊዜው ያለው በአማልካች ጉድለት በመሆኑ ሊፈቀድለት አይገባም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ የሰበር አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው የጠበቃው እናት ሞተው መሆኑን በመግለጽ ይህንኑ በሰው ምስክር ለማስረዳት ጠይቀው ባለበት የተቆጠሩት የሰው ምስክሮች ሳይሰሙ ከወዲሁ አቤቱታው ውድቅ የመሆኑ አግባብነት ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 326 ድንጋጌ አንፃር መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- አመልካች በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያቀርብ የቀረበው የጠበቃው እናት ሞትን ምክንያት ከማድረግ ውጭ የሞቱትን የጠበቃውን እናት ስም ባካተተ መልኩ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ወይንም ከአከባቢው ዕድር ማስረጃ ማቅረብ ሲገባው በሰው ማስረጃ ማስረዳት ማሰቡ አቤቱታው በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበ ቢሆንም ተአማኒነት የሌለው ሆኖ ይልቁንም ይግባኙ በወቅቱ ሊቀርብ ያልቻለው በአመልካች ጠበቃ ጉድለት ሆኖ የሰነድ ማስረጃ በቀላሉ ማቅረብ እየቻለ እውነትነት በሌለው ቃለ መሃላ እንዲሁም በሰው ምስክር ላስረዳ ማለቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን መርህና

ሊደርስበት ያሰበውን አላማ የሚያዛባ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው በበቂ ምክንት ያልተደገፈ አቤቱታ ተቃባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውውን ሲመስል ቅሬታው ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባ ሲባል የተያውን ጭብጥ አግባብነት ካለው የሕጉ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸው የጠበቃቸው እናት ሲታመሙ ቆይተው በኋላም በመሞታቸው ምክንያት መሆኑን ገልፀው ክርክራቸውን ያስረዱልኛል ያሉትን የሰው ምስክር ቆጥረው ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ እንዲፈቀድላቸው በመሐላ ቃል ሥር ሆነው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በጠበቃ አልተከራካሩም የሚል መቃወሚያ በተጠሪ በኩል መቅረቡን መዝገቡ አያመለክትም፡፡ ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ለማቅረብ አስቀድሞ የፈቃድ ጥያቄ ይግባኙ ጊዜ ያልቀረበበትን ምክንያቱን ከሚገልጹ ማስረጃዎች ጋር የሚቀርብ ሆኖ ማስረጃዎቹም ውሳኔ ለመስጠት ብቁ ሆነው መገኘት እንዳለባቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 325 (1) ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤት በቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ማስረጃውን ከመረመረ በኋላ መሆኑን ከቁጥር 325(2) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈው በቂ በሚባል ምክንያት መሆን /አለመሆኑ አከራካሪ በሆነ ጊዜ አከራካሪው ጭብጥ የሚረጋገጠው በማስረጃ ሲሆን ሕጉ ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ለማስፈቀድ አግባብነት ያለው ማስረጃ የጽሑፍ (የሰነድ) ብቻ መሆኑን አያመለክትም፡፡ ለክርክሩ አግባብ ካልሆነ ወይንም ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ከሌለው በቀር ፍርድ ቤት በተከራካሪዎች የተቆጠረን ምስክር መስማት እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 138 የሚደነግግ ሲሆን በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃ በአግባቡ መስማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ሥርዓት መርህ መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 52546 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ እንዲፈቀድላቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 205 መሠረት በመሐላ ቃል ተደግፈው ምስክሮችን በመቁጠር ያቀረቡትን አቤቱታ የምስክሮቹን የሚስክርነት ቃል ሳይሰማ ፤ ያልሰማውን የሰው ምስክር መዝኖ ተአማኒት የለውም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 271645 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ተሸሯል*** ።
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸው በቂ በሚባል ምክንያት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት የቆጠሩት የሰው ምስክሮች ሳይሰሙ ያቀረቡት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ውድቅ መሆኑ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3. **የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር** 271645 **በማንቀሳቀስ አመልካች አቤቱታቸውን ያስረዱልኛል በማለት የቆጠሩትን የሰው ምስክሮች በመስማት እንዲሁም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ተገቢ ነው በሚለው ተጨማሪ ማስረጃ ክርክሩን በማጣራት በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር** 343(1) **መሠረት ተመልሶለታል፡፡**
4. **በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡**

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ 216299

ቀን ግንቦት 25 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. አቶ አበበ እንሰተ

2ኛ. አቶ ደረጀ እንሰተ

3ኛ. ወ/ሮ ተዋበች እንሰተ } አልቀረቡም፡

4ኛ. አቶ ሽመልስ እንሰተ

ተጠሪ፡ አቶ ኃይሉ ቦሬሳ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የን/ስ/ላ/ምድብ በኮ.መ.ቁ 176966 በ3/2/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 277758 በ29/2/14ዓ.ም በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት በ8/3/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በፍ/ቤቱ በመ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍርድ ቤቱ ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ህ/ቁ 998 መሰረት እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ወይም ውርስ አጣሪ ሪፖርት የጸደቀበትን የፍርድ ቤት ውሳኔ ለማሰረዝ የሚቀርብ ክስ መቅረብ የሚኖርበት በራሱ ሪፖርቱ በጸደቀበት መዝገብ እንጂ በአዲስ መዝገብ መሆን ስለሌለበት አመልካቾች እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት የውርስ አጣሪ ሪፖርት በጸደቀበት መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን የማቅረብ መብት ተጠብቆላቸዋል በማለት በሰጠው ትእዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ትእዛዝ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ብይን ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ትእዛዝ እና ብይን በመቃወም ሲሆን ይዙቱም የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 የተሰጠው ፍርድ የሚፈጸም ከሆነ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያ ማቅረብ እንደሚቻል ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኮ.መ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም ያጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት የሚፈጸም ባለመሆኑ ከላይ ከተገለጸው ድንጋጌ አንጻር አመልካቾች በማይፈጸም ፍርድ መቃወሚያ ልናቀርብ የማንችል ሲሆን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍርድ ያጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት የማይፈጸም መሆኑን መረዳት ሲገባው አመልካቾች እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት የውርስ አጣሪ ሪፖርት በጸደቀበት መዝገብ ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት ተጠብቆላቸው መዝገቡ ተዘግቷል በማለት የሰጠው ትእዛዝም ሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዚሁ ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ በመሰረዝ የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 45905(ቅጽ 11) በፍ/ቤቱ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማስረጃነት የሚያገለግል ሆኖ ይህን የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን በማስረጃነት ተጠቅሞ የድርሻ ክፍፍል ዳኝነት ለመጠየቅ የሚያገለግል እንጂ በቀጥታ ውሳኔው ለአፈጻጸም ችሎት የሚቀርብ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበት አይደለም ሲል ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር እንዲሁም የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ከደነገገው አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ ክርክሩ በከፊትነው አዲሱ የመ.ቁ 176966 ላይ እንዲቀጥል ውሳኔ እንዲሰጥልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ውርስ ተጣርቶ በጸደቀበት መዝገብ ላይ እንጂ እንደ አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም ተብሎ የዳኝነት ጥያቄያቸው ውድቅ መደረጉ በሰ.መ.ቁ 45905 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ27/4/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ

በ17/6/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ እና ብይን ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በ30/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እና ብይን እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ እና ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ.መ.ቁ 45905 (ቅጽ 11) በመጥቀስ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በዚሁ በተጠቀሰው የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ላይ የነበረው ክርክር በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ ተጣርቶ ቀርቦ በፍ/ቤቱ ከጸደቀ በኋላ ይህን የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በመያዝ የውርስ ሀብት ክፍፍል ድርሻ ክስ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ተካሂዶ የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔው መብታችንን ይነካል ያሉ አመልካች ፍርድ ይታረምልን ሲሉ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ያቀረቡትን የፍርድ መቃወም አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ ውርስ የተጣራው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተሾመው የውርስ አጣሪ ስለሆነ የውርስ ማጣራት ሪፖርቱ ደግሞ አመልካችን የማያውቃቸው መሆኑን በመግለጽ የፍርድ መቃወሚያው ሪፖርቱን ላጸደቀው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሚቀርብ በቀር የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔ ለሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው በመቅረቱ ምክንያት አመልካች እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረው ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች አቤቱታ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358ን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ሲሆን የአመልካችን መብት ይነካል የተባለው እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የተሰጠው በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመሆኑ አመልካች ከማስረጃነት ዋጋ ውጪ ሌላ ዋጋ የሌለውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ሊቃወም የሚችልበት አግባብ የለም በማለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናውን ውሳኔ በመሻር አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት በውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ላጸደቀው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይደለም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎና የግራቀኙን ቀሪውን ሁሉን ክርክር በመመርመር ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በመመለስ ውሳኔ የሰጠበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 176966 በሆነው መዝገብ ላይ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በመ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም በፍ/ቤቱ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲሰረዝልን የሚል ሲሆን ይህ አቤቱታ ከላይ የተገለጸው በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የታየውን ከውርስ አጣሪ ሪፖርት መጽደቅ እና ይህንኑ ሪፖርት መሰረት አድርጎ የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ክስ መቅረብ እና በዚሁ ላይም የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ውሳኔን ሂደት ያለፈ ሳይሆን በፍ/ቤት ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት

ይሰረዝልን የሚል ይዘት ብቻ ያለው በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 45905 ከላይ በተገለጸው መልኩ የተሰጠው ውሳኔ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ቤት ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ይሰረዝልን የሚል አቤቱታ በዛው ሪፖርቱ በጸደቀበት መዝገብ ላይ ሊቀርብ የሚገባው እንጂ ሪፖርቱ ከጸደቀበት መዝገብ ውጪ በሌላ የክስ መዝገብ ይስተናገድ የሚባልበት የህግ መሰረት አለመኖሩን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በመሆኑም የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትእዛዝ እና ብይን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የን/ስ/ላ/ምድብ በኮ.መ.ቁ 176966 በ3/2/14ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 277758 በ29/2/14ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 216384

ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡-1ኛ. አቶ ሰለሞን እሸቱ

2ኛ. አቶ ብርሃኑ ወርቅነህ } ቀረቡ

3ኛ. ወ/ሮ አብቤት ደሳለኝ

ተጠሪ፡- ሰዓዳ ጌቱ እና ጓደኞቻቸው ሻወርና መፀዳጃ ህ/ሽ/ማህበር- ስራ አስኪያጅ ፍሬህይወት ጉርሜሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 09/03/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 291552 በቀን 01/10/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

275453 በቀን 24/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ የተጠሪ ማህበር መስራች አባል መሆናቸውን ገልፀው ነገር ግን ማህበሩ 1ኛ አመልካችን የካቲት 2 ቀን 2013 ዓ.ም ፣ 2ኛ አመልካችን መጋቢት 2 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲሁም 3ኛ አመልካችን የካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከማህበር አባልነት አሰናብቷል:: በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ውስጠ ደንብ መሰረት ማህበሩ ፈጽማችኃል ያላቸውን ተግባሮች ያልፈፀምን ሲሆን ተፈጽመዋል ቢባል እንኳን ከአባልነት እንደሚያሰናበቱ አልተደነገገም። በመሆኑም ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ ተከሳሽ ማህበር ወደ አባልነታችን እንዲመልሰን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተጠሪ በሰጠው መልስ በአመልካቾች ላይ የተወሰደው እርምጃ የማህበሩን መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያደረገ ነው። 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በ29/08/2011 ዓ.ም በሌሎች የማህበሩ አባላት ላይ የስድብ፣ ዛቻና ማስፈራራት እንዲሁም የማህበሩን ስራ ትተው የመሄድ ተግባር ፈጽመዋል፤ ግንቦት 2 ቀን 2011 ዓ.ም ሁከትና ዛቻ በመፍጠራቸው ለፖሊስ ቀርቦ ጉዳዩ በይቅርታ ተፈቷል። 3ኛ አመልካች በማህበሩ ውስጥ ዝቅተኛ የስራ ተነሳሽነት ያላቸው እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት ለረጅም ግዜ ከስራ ጠፍተው በመምጣት ጥር 1 ቀን 2012 ዓ.ም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። 2ኛ አመልካችም በአባላት ስብሰባ የማይገኙ እና የተለያዩ ጥፋቶችን የሚፈጽሙ በመሆናቸው የገንዘብ ቅጣት ተጥሎባቸዋል። ከዚህ ባለፈ 2ኛ አመልካች ለ 2 ወራት ሙሉ የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ ሳይፈርሙና የማህበሩን ገንዘብ ገቢ ሳያደርጉ እየሰሩ የሚገኙ በመሆናቸው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እና የ 2 ወር ደሞዝ ቅጣት ተላልፎባቸዋል። በዚህም ስራቸው ሊታረሙ ባለመቻላቸው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የማህበሩን ገንዘብ ብር 6050.00 ገቢ ሳያደርጉ በመቅረታቸው እና ሲጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከማህበሩ አባላት ብር 450 ነጥቀው በመውሰዳቸው ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ አሰናብቷቸዋል። የማባረር እርምጃ መወሰዱ የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ተከትሎ የተደረገ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ ቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ ማህበር ውስጠ ደንብ አንቀጽ 24 ማንኛውም አባል የማህበሩን ንብረት በአግባቡ መያዝ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 20 መሰረት ተከሳሽ ማህበር አባላቱን የማባረር ስልጣን አለው። የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ቃል ከሳሾች የማህበሩን ገንዘብ ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸውን አስረድተዋል። ከሳሾች በምስክርነት ቃላቸው ገንዘቡን ገቢ ያላደረጉት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ባለመኖሩ መሆኑን ቢያስረዱም የማህበሩን ገንዘብ በማግስቱም ሆነ በቀጣዮቹ ጊዜ ገቢ ማድረግ የነበረባቸው እና የመብት ጥያቄ ካላቸውም ማህበሩን ከሚጠይቁ በቀር ገንዘቡን ለራሳቸው ለማድረግም ሆነ ለመብት ማስከበሪያ መጠቀም አይችሉም። በምስክርነታቸው ከሳሾች ገንዘቡን ለግላቸው አለማዋላቸው ቢገለጽም ገንዘብ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ በእጃቸው ካደረጉ በህግ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸው ለግላቸው በማዋል ሀሳብ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል። ከዚህ ባለፈ ተከሳሽ በመልሱ የጠቀሳቸውን ተግባራት ሲፈጽሙ እንደነበር የተከሳሽ ምስክሮች በአግባቡ ሲያስረዱ ከሳሾች ግን ይህን አላስተባበሉም። በመሆኑም ከሳሾች በውስጠ ደንቡ እንዲሁም በንግድ ህግ አንቀጽ 292 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማህበሩን ጥቅም ለራሳቸው በማድረጋቸው፣ በማህበሩ ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረሳቸው እንዲሁም አባላት ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ሁከት መፍጠራቸው በመረጋገጡ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 20 መሰረት ማህበሩ ለማባረር ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ከሳሾች ጥር 22 እና መጋቢት 2 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረጉ ጠቅላላ ጉባኤዎች መሰናበታቸው በአግባቡ በመሆኑ ማህበሩ ያስተላለፈው የስንብት ውሳኔ እንዲነሳ በሚል የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው።

አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ አመልካቾች በተጠሪ ማህበር ውስጥ የማህበሩ መስራችና አባል ስንሆን ተጠሪም ምንም የህግ ምክንያት ሳይኖረው ከማህበሩ አባልነታችን በማሰናበቱ በስር ፍ/ቤት ወደ አባልነታችን እንዲመልሰን ክስ አቅርበን በሰጠነው ምስክርነት አመልካቾች የሰበሰብነውን ገንዘብ ወደ አካውንቱ ልናስገባ ስንሄድ በባንኩ ማስገባት አትችሉም በመባላችን

ምክንያት ያላስገባን ስለመሆኑና ገንዘቡም በ1ኛ ከሳሽ ሂሳብ ውስጥ የሚገኝና ለግል ጥቅማችን ያላዋልነው ስለመሆኑ እንዲሁም ተከሳሽ የጠቀሰውን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ በማስረጃ አስረድተን እያለና የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 20 በግልጽ ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ የተያዘን የሚመለከት በመሆኑ ተከሳሽ በዚህ ረገድ ክርክር ባላቀረበበትና በቀረቡት ምስክሮችም ይኸው ስለመሆኑ ሳይረጋገጥብን ከውስጠ ደንቡ ውጭ ገንዘቡ በእጃችን ያለና ለግል ጥቅማችን ያላዋልን ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በፍርዱ ሀተታ ላይም ተመልክቶ እያለ ገንዘቡ በእጃቸው መሆኑ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነና ለማህበሩ ገቢ አለማድረጋቸው ለግላቸው ለማዋል ሀሳብ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው በማለት ፍርድ ቤቱ የተሳሳተ ግምት በመውሰድ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 20 ን ተላልፈዋል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘናና የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል። አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ባቀረብነው ምስክር በፈረቃ እንደማንገናኝ በመልሳቸው ላይ ጠቅሰው ያቀረቡትን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ አስረድተን እያለ በተጠሪ የተመሰከረባቸውን አላስተባበሉም በማለት የደረሰበት መደምደሚያም የተሳሳተ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ያለውን ተግባር ያልፈጸምን ስለመሆኑ በአግባቡ ያስረዳን ከመሆኑም በላይ የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 20 በዚህ ምክንያት ሊያሰናብት እንደሚችል ባልተደነገገበት ሁኔታና የተጠሪ ምስክሮች ይህን ባላስረዱበት ሁኔታ ከአባልነታችን ማሰናበቱ ተገቢ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን በማለት ቅሬታቸው አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ መተዳደሪያ ደንቡ የማህበሩ ገንዘብ ስርቆት መፈጸም እንደሚያሰናብት የሚገልጽ ሲሆን የአሁን አመልካቾች የማህበሩ ገንዘብ ያዥ እንዲቀበላቸው ጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በእጃቸው መቆየቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ለግላቸው ለማዋል ሀሳብ እንዳላቸው ተገንዝቤያለሁ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪ በቀን 10/06/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተጠሪ ማህበርን ህልውና የሚጎዳ ተግባር በየግዜው ከመፈጸማቸው በተጨማሪ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከጥር 01 ቀን 2013

ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰበሰቡትን ብር 6050.00 ለተጠሪ ገንዘብ ያዥ ገቢ እንዲያደርጉ እየጠየቅናቸው በእንቢተኛነት ወደ ራሳቸው አካውንት ገቢ ለማድረግ ጠይቀው ባንኩ ስላልተቀበላቸው 1ኛ አመልካች አካውንት ውስጥ ማስገባታቸው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ መሆኑን ስለሚያረጋግጥ፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ የማህበሩን ብር 450.00 ከማህበሩ አባላት ነጥቆ መውሰዱ በተጠሪ የውስጥ ደንብ አንቀጽ 20 መሰረት ከስራ ስለሚያሰናብት ተጠሪ የወሰደው የስንብት እርምጃ በአግባቡ ነው፤ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል። አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካቾች ክስ ለማቅረባቸው ቀዳሚ ምክንያት የሆነው የተጠሪ ጠቅላላ ጉባኤ ያሳለፈው የስንብት ውሳኔ ሲሆን ለውሳኔውም ምክንያት የሆነው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የማህበሩን ገንዘብ ብር 6050.00 ገቢ ሳያደርጉ መቅረታቸው እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከማህበሩ አባላት ብር 450.00 ወስደዋል መባሉ ነው። ከዚያ በፊት በአመልካቾች ተፈጽመዋል ለተባሉ የተለያዩ ግድፈቶች የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችም ተያይዘው በመከራከሪያነት ቀርበዋል።

የማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 24 ማንኛውም አባል የማህበሩን ንብረት በአግባቡ መያዝ እንዳለበት የሚደነግግ መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም። ማህበሩም በደንቡ አንቀጽ 20 መሰረት አባላትን የማባረር ስልጣን ቢኖረውም ይኸው ስልጣን በበቂ ምክንያትና ማስረጃ ላይ ተደግፎ ሊተገበር የሚገባ ነው።

ለስንብት ምክንያት የሆነውን የማህበሩን ገንዘብ አመልካቾች ገቢ ያላደረጉት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ባለመኖሩ መሆኑን፤ በባንክም ሄደው በአካውንት ለማስገባት ሞክረው በባንኩ ማስገባት አትችሉም በመባላቸው ምክንያት ገቢ ስላለመሆኑና ገንዘቡም ተጠቃሎ በ1ኛ አመልካች የሚገኝና ለግል ጥቅማቸው ያላዋሉት ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር በማስረጃዎቻቸው የተደገፈ ስለሆኑ የስር

ፍርድ ቤት ካሳለፈው ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል። የስር ፍርድ ቤት ይህን ፍሬ ነገርና ማስረጃ ተቀብሎ ነገር ግን ገንዘብ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ በእጃቸው ካደረጉ በህግ ንብረታቸው እንደሆነ የሚቆጠር ነው ለግላቸው ለመዋዋል ሀሳብ እንዳላቸውም ግንዛቤ ይወሰዳል በማለት የደረሰበት የግምት መደምደሚያ የግራቀኙን ክርክርና ህጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም።

በሌላም በኩል ተጠሪ በተለያ ጊዜ በአመልካቾች ተፈፀሙ ለሚላቸው ቀላል ጥፋቶች በይቅርታ መታለፋቸውን እንዲሁም በማህበሩ መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ማስጠንቀቂያና የገንዘብ ቅጣት ተጥሎባቸው መታለፋቸውን ከተጠሪም ክርክር መገንዘብ ይቻላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ አሁን ላደረገው ስንብት ህጋዊነት በድጋሚ በመከራከሪያነት ማቅረቡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤትም አስቀድሞ ማስጠንቀቂያና መሰል ቅጣት ተሰጥቶባቸው የታለፉ ጉዳዮችን ለስንብቱ እንደምክንያት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

በአጠቃላይ አመልካቾችን ከተጠሪ ሕብረት ሽርክና ማህበር ለማሰናበት የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት የለም። አመልካቾች ከማህበሩ አባላት ጋር ተስማምተው ለመስራት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መረዳት የሚቻል ሲሆን በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ አብሮ የመስራት ፍላጎት ባልጠፋበት ህጉ ካስቀመጣቸው አማራጮች መካከል የመጨረሻ አማራጭ የሆነውን ከማህበር ማሰናበት መወሰን ተቀባይነት የለውም። የሕብረት ሽርክና ማህበር የሚመሰረተው በአባላት መካከል ባለው መተማመን እና አብሮ የመስራት ፍላጎት ላይ ሲሆን ይህ ማለት ግን በሁሉም የማህበሩ አባላት መካከል ያለመስማማት አይፈጠርም ወይም አነስተኛ ጥፋቶች ሁሉ ለስንብት ያበቃሉ ማለት አይደለም።

ስለሆነም የአመልካቾች ተግባር የማህበሩን ህልውና ለማስቀጠል እንደማይችል ተደርጎ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ መወሰኑ የንግድ ህጉንም ሆነ የማህበሩን ደንብ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል። ተከታዩን ወስነናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 291552 በቀን 01/10/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 275453 በቀን 24/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. ተጠሪ ማህበር አመልካቾችን ወደ አባልነታቸው እንዲመልስ ወስነናል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ 216415

ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ አፈንዲ አብዲ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን አዳማ ቅርንጫፍ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 10/03/2014ዓ.ምበተጻፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 316816 በቀን 04/06/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 191678 በቀን 30/10/2013ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ።

አመልካች ባቀረቡት ክስ ፕራዶ ላንድክሩዘር መኪና የሰሌዳ ቁጥር 2-08636 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር JTEBX9FJOBKO47153 እና የሞተር ቁጥር 0991742TR የሆነ በአቶ ዑመር አብዱራህማን አህመድ በሚባል ሰው ተመዝግቦ የሚታወቅ በቀን 02/11/2011 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭና ግዥ ውል ገዝቼ ኦርጅናል የመኪና ሰነድ በእጄ አስገብቼ ሙሉ ውክልና ሰጥቶኝ

እየተጠቀምኩበት ነው። ይህ መኪና የአስመጪነት ፈቃድ ባለው ሰው አቶ መላኩ ወ/ግዮርጊስ በሚባል በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባና ለአቶ ዑመር አብዱራህማን የተሸጠ ሲሆን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማስረጃ ያለው ነው። ይሁንና ተከሳሽ በቀን 02/01/2012 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ገዝቼ እጄ ያስገባሁትን መኪና በህገወጥ መልክ የገባ ነው በማለት የወሰደብኝ በመሆኑ ተጠሪ መኪናውን መያዙ ህገወጥ ነው ተብሎ እንዲለቀቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተጠሪ በሰጠው መልስ ከሳሽ መኪናውን የገዛሁት ህጋዊ መሆኑን አጣርቼ ነው ይበል እንጂ እውነት አይደለም፤ የመኪናው ማስረጃ የሀሰት ማስረጃ መሆኑን አረጋግጠናል፤ መኪናው ወደ ሀገር የገባው በቀን 05/04/2019 ዓ.ም ተማም መሐመድ በሚባል ሰው ስም በቱሪስትነት ተመዝግቦ ለ25 ቀን ብቻ ሆኖ ተመልሶ መውጣት ሲገባው የሀሰት ማስረጃ ተዘጋጅቶለት ሲንቀሳቀስ የተያዘ ነው፤ መንግስት በቱሪስት ስም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎችን ካለምንም ጥፋት ገዝተው ለተገኙ ሰዎች መመሪያ አውጥቷል፤ ስለሆነም የመኪናው ጉዳይ መታየት ያለበት በመመሪያ ቁጥር 129/2010 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተደነገገው መሰረት በመሆኑ ቀረጥና ታክስ ቅጣት 50% ተቀጥተው (ከፍለው) መውሰድ እንደሚችሉ ተመልክቷል። አመልካች ይህን በአስተዳደር ያለውን ውሳኔ ሳያሰጥ በቀጥታ ፍርድ ቤት ክስ ሊያቀርብ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 ምዕራፍ 3 ስር በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ይግባኙን ለቅሬታ አጣሪ ዋና መ/ቤት ለተቋቋመው ማቅረብ እንዳለበት አንቀጽ 153(2)(1) ስር ተደንግጓል፤ ይግባኝ የሚቀርብበትም ሁኔታ በአዋጁ ቁጥር 155 ስር እና የደንበኞች ቅሬታ የሚስተናገድበት መመሪያ ቁጥር 129/2010 ወጥቷል። በአዋጁ ይግባኙን ባየው አካል የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ካለው ብቻ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚቻል በአንቀጽ 155(3) የሚደነግግ በመሆኑ ከሳሽ በዚህ አግባብ ሳይጨርስ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ የህግ ድጋፍ የለውም፤ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ መኪናውን በቅን ልቦና ገዛሁ ከማለት ባለፈ ተገቢው የጉምሩክ ስርዓት ተፈጽሞበት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪ ለመሆኑና የጉምሩክ ስርዓት የሚያስፈጽመው መልስ ሰጪ እስከሆነ ድረስ የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢነት የለውም፤ የጉምሩክ ስርዓት ሳይፈፀምባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መኪኖች በሀገር ውስጥ ሲሸከረከሩ ቢገኙ መልስ ሰጪ የመያዝ እና ተገቢ ያለውን አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እንዳለው የአዋጅ

ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 143 እና 153(2)(ለ) እና ተከታይ ቁጥሮች ያመለክታሉ፤ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ውሳኔውን አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 10/03/2014 ዓ/ም ያቀረቡት ማመልከቻ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነውን መኪና ያገኘው በሽያጭ መሆኑ እና ይህ ሽያጭም በመንግስት ተቋም የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 1198 መሰረት ታይቶ የሚወሰን ሆኖ ሳለ ግብር በዝቶብኛል የሚል ቅሬታ በማስመሰል ጉዳዩን የማየት ስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የስር ፍ/ቤቶች መዝገቡን መዝጋታቸው ስህተት የተፈጸመበት ነው። የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ለክርክሩ መነሻ ለሆነው ጉዳይ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የጉምሩክ አዋጅን ያለቦታው ጠቅሰው ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ስህተት ነው። አመልካች ከውል በመነጨ ያገኘውን መብት ለማስከበር ያቀረበውን እና በቀጥታ ከግብር እና ታክስ ጉዳይ ጋር የማይገናኘውን ክስ የጉምሩክ አዋጅ በመጥቀስ ጉዳዩን መደበኛ ፍ/ቤት ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል። ለክርክር መነሻ የሆነው መኪና ከማንኛውም እዳ እና እገዳ ነጻ መሆኑ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ተረጋግጧል። ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት እና ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑ ግዥ በሚፈጸምበት ግዜ ከምረጋገጡም በተጨማሪ ባለስልጣን መ/ቤቱ ፍ/ቤት ባዘዘው መሰረት በሰጠው ማብራሪያ መኪናው ህጋዊ መሆኑን አረጋግጧል። መኪናው እዳ እንኳን ቢኖርበት አመልካች መኪናውን የገዛው የመንግስት አካልን በማመን ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ 1198 መሰረት በአመልካች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሁሉ የትራንስፖርት ባለስልጣኑ ተጠያቂ ይሆናል። በመሆኑም የባለቤትነት ስም ዝውውር የሚመዘግብ የመንግስት አካል የሆነው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና ከማንኛውም ግብርና ታክስ እዳ ነጻ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች በግዥ ያገኘውን ንብረት የስር ፍ/ቤቶች ከአመልካች ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን የታክስ እና ግብር ጉዳይ አንስተው የጉምሩክ አዋጁን ያለ ቦታው ጠቅሰው ጉዳዩ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት መታየት አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ተብሎ እንዲሻር እና ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነውን መኪና ከማንኛውም ዕዳና ዕገዳ ነጻ መሆኑን አግባብነት ካለው አካል አረጋግጠው የገዙ ስለመሆናቸው ጠቅሰው ተጠሪ አላግባብ የወሰዱብኝ በመሆኑ እንዲመልስልኝ በሚል የቀረበ ሆኖ እያለ ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት መቅረብ የለበትም በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል በፌደራል

ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በቀን 15/01/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ ተጠሪ ውርስ ያደረገው ትክክለኛው የመኪና ሻንሲ ቁጥር JTEBX9FJOBK047153 በቀን 27/07/2011 ዓ.ም ከቀረጥ ነጻ በቱሪስት የገባ ሲሆን ነገር ግን አመልካች ከፊንፊኔ ኦሮሚያ ልዩ ዞን መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ደብተር ላይ የተሰጠው ሻንሲ ቁጥር JTEBX9FOBKV7153 ስለሆነ ተጠሪ ውርስ ካደረገው መኪና ጋር አንድ አይነት አይደለም፡፡ አመልካች አደረኩ ባለው የሽያጭ ውል፣ በውክልና ላይ ፣ መኪናው ይለቀቅልኝ በማለት በጻፉት ማመልከቻ፣ እንዲሁም በቀን 16/04/2019 ዓ.ም በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ላይ የተጠቀሰው ሻንሲ ቁጥር JTEBX9FOBKV7153 በመሆኑ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት መኪና እና ተጠሪ ውርስ ያደረገው መኪና የተለያዩ በመሆናቸው አመልካች መኪናው ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረብን ሲሆን በአማራጭም የጉምሩክ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 152-155 እና መመሪያ ቁጥር 107/2007 መሰረት በየደረጃው ያሉ የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ ሳያገኝ በቀጥታ ፍ/ቤቶች የማየት ስልጣን የላቸውም በማለት ተከራክረናል፡፡ ትራንስፖርት ባለስልጣን መኪናው ከእዳና እገዳ ነጻ ነው ወይ የሚለውን ሊያረጋግጥ ይችላል እንጂ መኪናው በምን አይነት ሁኔታ ወደ ሀገር እንደገባና ቀረጥ ተከፍሎበት ይሁን በነጻ የሚለውን ለማረጋገጥ የሚችልበት ስልጣን የለውም፡፡ አመልካች እንደሚሉት እና በማስረጃ እንደተረጋገጠው መኪናውን በዋስትና በማስያዝ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ተማም መሀመድ የሚባል ግለሰብ ሲሆን መኪናውን በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ከሀገር ካላስወጣ መኪናው እንዲወረስ ዋስትና ያስያዘ ስለሆነ ተጠሪ መ/ቤትም በተፈቀደለት ግዜ ውስጥ ተመልሶ ከሀገር ባለመውጣቱ አረጋግጦ ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት በቁጥጥር ስር ማድረጉ አግባብነት ያለው ነው፡፡በአዋጁ አንቀጽ 71(4) ስር በግዜያዊነት ወደ ሀገር የገባ መኪና ከገባበት አላማ ውጭ መጠቀም የተከለከለ መሆኑ ተደንግጎ እያለ አመልካች ህጉን ወደ ጎን በመተው በሽያጭ ውል እንዳገኘ በማስመሰል የሚያቀርበው ተቀባይነት የለውም፡፡ በጉምሩክ አዋጅ 859/06 መሰረት ቀረጥና ታክስ የማስከፈል ስልጣን የተሰጠው ለተጠሪ መስሪያ ቤት ሲሆን አመልካች እንደሚሉት የተከፈለም ቀረጥና ታክስ የለም፡፡ከቀረጥና ታክስ ነጻ መሆኑን ክሊራንስ የሚሰጠው ጉምሩክ እንጂ መንገድ ትራንስፖረትአይደለም፡፡ አመልካች የፍ/ህ/ቁ 1198 በመጥቀስ የሚያቀርቡት ለአሁኑ ክርክር አግባብነትና ተፈጻሚነት የሌለው ነው፡፡ በቱሪስት መልክ የገባ መኪና መንገድ ትራንስፖርት ስም ዝውውር የሚያደርግበት የህግ መሰረት የሌለና የአዋጁ አንቀጽ 130(7)ም የተደነገገው ቀረጥ ነጻ

ህጋዊ ዲክራስዬን የሚያቀርቡት እንጂ ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተው ለሚያቀርቡ የተደነገገ ባለመሆኑ አመልካች የህጉን ይዘትና ድንጋጌ በማዛባት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የጉምሩክ ስርዓት ሳይፈፀምባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መኪኖች በሀገር ውስጥ ሲሸከረከሩ ቢገኙ መልስ ሰጪ የመያዝ እና ተገቢ ያለውን አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 143 እና 153(2)(ለ) እና ተከታይ ቁጥሮች መደንገጉ፤ እንዲሁም ቀረጡን ከፍሎ መኪናውን ከማስለቀቅ ጋር የተያያዘ ክርክር ለተጠሪ ቀርቦ በየደረጃው ውሳኔ ከተሰጠበት በኃላ በይግባኝ ፍርድ ቤት የሚቀርብ መሆኑ አያከራክርም፡፡

ነገር ግን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የመኪና ሽያጭ እና የባለቤትነት ስም ዝውውር የሚመዘገበውና የመንግስት አካል የሆነው የፌንፌኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና ከማንኛውም ግብርና ታክስ እዳ ነጻ መሆኑንና በህጉ አግባብ የባለቤቱ ንብረት መሆኑን አረጋግጦልኝ ይህንኑ በማመን በግዥ ውል ያገኘሁትን ንብረት በመሆኑ ይለቀቅልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ የዳኝነት ጥያቄ በውል የተገኘ መብትን ለማስከበር የቀረበ በመሆኑ በግዥና ሽያጩ ውስጥ ተካፋይ የሆኑ ወገኖች ሁሉ እንዲሁም ተሸከርካሪው ከማንኛውም ዕዳና ዕገዳ ነፃ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰጥቶ የግዥ ውሉ እንዲፈፀም አድርጓል የሚባለው መንግስታዊ አካል የክርክሩ ተሳታፊ ተደርገው በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ የታክስ እና ግብር ጉዳይ ብቻ ነው ተብሎ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት መታየት አይችልም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በፍርድ ታይቶ ሊወሰን የሚችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለው ህግ ጠቅሰው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን እንደማይችልና ፍርድ ቤቶችም በቀጥታ ተቀብለው ለማስተናገድ ስልጣን እንደሌላቸው ያሳለፉት ውሳኔ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 316816 በቀን 04/06/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 191678 በቀን 30/10/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአከራካሪው መኪና ግዥና ሽያጩ ውስጥ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን ሁሉ፤ እንዲሁም ተሸከርካሪው ከማንኛውም ዕዳና ዕገዳ ነፃ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰጥቶ የግዥ ውሉ እንዲፈፀም አድርጓል የሚባለውን መንግስታዊ አካል የክርክሩ ተሳታፊ በማድረግ እንደ አስፈለሰጊነቱ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብበ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ</u>

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ከሰው በቅን ልቦና የገዛሁት መኪና ካለአግባብ ስለያዘብኝ ይልቀቅልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪም ተከሳሽ ካለአግባብ ተያዘብኝ የሚለው መኪና በቱሪስት መልክ ወደ ሀገር ውስጥ የገባና ጊዜውን ሲጨርስ የሚወጣ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት በመሆኑ እና ከህግ ውጭ በከሳሽ በአሁን አመልካች እጅ የተገኘ በመሆኑ ተይዞ በህጉ መሰረት ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል የተወሰነ በመሆኑ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡ መኪናውም በህገ ወጥ መንገድ በከሳሽ ተይዞ የተገኘ በመሆኑ መያዙ ተገቢ በመሆኑ ክሱ ወድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራክረው ጉዳዩ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ሲሉ የአሁን አመልካችን ክስ መዝገብ ዘግተውታል፡፡

የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን በተመለከተ ጉምሩክ የአሁን ተጠሪ ግብርና ታክስ ከማስከፈል በተጨማሪ በህገ ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን ተከታትሎ መያዝና ቀረጥና ታክስ ከፍለው ህጋዊ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ለአሁን ተጠሪ የተሰጠው ሥልጣን ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ጉዳይ የፍ/ቤት ሥልጣን ነው ሲል የሚያቀርበው ክርክር መኪናውን ከሰው በቅን ልቦና ከመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተረጋግጦ የገዛሁት በመሆኑ የጉምሩክ አስተዳደራው ውሳኔ እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን አይደለም በሚል ሲሆን መኪናው በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ የአሁን አመልካች በቅን ልቦና ገዛሁት ስላለ የጉምሩክ አስተዳደራዊ ውሳኔ የማያስፈልገው የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሥልጣን መሆኑን ያስቀረዋል ብሎ ማለት ተገቢ የሆነ ምክንያትና አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ሲያገኝ መያዝ እና ቀረጥና ታክስ ማስከፈል እንደሚችል የማያከራክር ጉዳይ ከሆነ አሁን ያከራከረውን መኪና የአሁን ተጠሪ ከህገ ውጪ በአሁን አመልካች ተይዞ ተገኝቷል ብሎ ታክስ እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና 155 ድንጋጌ መሰረት ለአሁን ተጠሪ

አስተዳደራው ውሳኔ ካቀረበ በኋላ የግብር ይግባኝ ጉባኤ የይግባኝ ቅሬታ ያቀርባል፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በህግ ጉዳይ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ የሚችል ነው፡፡ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ ግራ ቀኙን አከራክሮ ያከራከረው መኪና የአሁን ተጠሪ እንደሚከራከረው በህገ ወጥ መንገድ በአሁን አመልካች እጅ የተገኘ አይደለም በቅን ልቦና የገዛው በመሆኑ ሊያዝበት አይገባም ብሎ ሊወስን ይችላል፣ ወይ የአሁን ተጠሪ እንደሚከራከረው መኪናው በቱሪዝም መልክ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ እና የአሁን አመልካች ግዥውን ፈጽሞ ከሆነ ግዥውን ሲፈጽም ሊያደርግ የሚገባውን ግዴታ ሳይወጣ የፈጸመ በመሆኑ የቅን ልቦና ገዥ አይደለም ሊል ይችላል ወይ የቅን ልቦና ገዥም ቢሆን በአሁን ተጠሪ መያዙ ተገቢ ነው ሊል ይችላል፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው ግራ ቀኙን አከራክሮ በህጉ መሰረት ሊሆን ይገባል ያለውን ውሳኔ መስጠት በአዋጅ የተሰጠው ሥልጣን ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤው የግራ ቀኙን ክርክር ሲያጣራ ከሚመለከተው አካል ሁሉ ማስረጃ አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣኑ ያለው ሲሆን የአሁን አመልካች ያከራከረውን መኪና ከሌላ ሰው የገዛሁት ነው የሚለው ክርክር 3ኛው ወገን በክርክሩ መግባት አለመግባቱ ለግብር ይግባኝ ጉባኤው በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን የሚያስቀር በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ በቱሪዝም መልክ ሀገር ውስጥ ገብቶ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት በህገ ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀስ፣ ቀረጥና ታክስ መክፈል ያለበት መኪና ስለመሆን አለመሆኑ ጉዳይ እንጂ የንብረት መፋለም ክርክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ያከራከረው መኪና ህገ ወጥነቱ ከተረጋገጠና ለአሁን አመልካች ካለአግባብ ተሸጦለት ከሆነ ለሚደርስበት ጉዳት ህጉ በሰጠው መብት መሰረት መጠየቅ ህጋዊ መብቱ እንጂ በፍ/ቤት የሚሰጠው መብት አይደለም፡፡ በመሆኑም በቂ ባልሆነ ምክንያት ጉዳዩ የግብር ይግባኝ ጉባኤው ሥልጣን እንዳልሆነና የፍ/ቤት ሥልጣን ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብዬ ስለማላምን የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 216482
ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች :-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ጋዲሳ፡- ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ መገርሳ ጋዲሳ

2. ወ/ሮ ወርቄ አበራ } **ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋራ በስጦታ ተገኘ የተባለ ንብረት አጠቃቀም የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰዉን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘው 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ከተጠሪዎች ጋር በ2003 ዓ/ም አቶ ጣሰው አበራ የተባለ ግለሰብ በስጦታ ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥተዉናል፡፡በቦታዉም ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ቤት ሰርተንበት ይዞታችን አድርገን በቤቱም እስካሁን እየኖርንበት እንገኛለን፡፡ ሆኖም ግን ቦታውን እኩል መካፈል ስገባን ተጠሪዎች ግን ቦታውን በስማቸው የግል ይዞታቸዉ አድርገው እንዳስመዘገቡ ተረድቻለሁ፡፡በመሆኑም ስጦታ አድራጊው እኩል እንድንካፈል የሰጠንን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ያለአግባብ በድብቅና በሕገ-ወጥ መንገድ በተጠሪዎች ስም የተመዘገበው እንዲሰረዝ ፤ ይዞታው በአመልካች እና በተጠሪዎች ስም በጋራ እንዲመዘገብና እኩል 150 ካሬ ሜትር በየግላችን ተካፍሎ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አቶ ጣሰዉ በ2003 ዓ/ም ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ስላላስተላለፉ በክሱ ላይ የተገለጸዉ ፍሬ ነገር ሀሰት ነዉ፡፡አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/1 ፣2428 እና 2443 መሰረት በጽሁፍና በምስክሮች ፊት የተደረገ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የስጦታ ዉል በማስረጃነት ያላቀረቡ ስለሆነ ስጦታ ተደርጎልኛል በማለት ያቀረቡት ክስ የሕግ መሰረት የሌለዉ ነዉ፡፡ ክርክር የተነሳበት ይዞታ አቶ ጣሰው አበራ በቀን 20/02/1992 ዓ/ም ለተጠሪዎች በስጦታ ያስተላለፉት ነው፡፡ ተጠሪዎች በቦታው ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ ሳይኖር አሁን ያሉትን ግንባታዎች በራሳችን ገንዘብና ጉልበት ሰርተናል፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179/1 እና በሰ/መ/ቁጥር 36638 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የተጠሪዎች የግል ንብረት ነዉ፡፡ አመልካች የተጠሪዎች ጥገኛ ሆነዉ ተጠሪዎች በሰራነው ቤት ውስጥ ከመኖር ባለፈ በቤቱ ላይ ምንም መብት ስለሌላቸዉ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 129931 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና የአቶ ጣሰው አበራንና የወ/ሮ አረጋሽ ጫላን ምስክርነት ቃል ሰምቶና መዝኖ በቀን 09/02/2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ አቶ ጣሰዉ አበራ በ2003ዓ/ም ለአመልካችና ለተጠሪዎች በስጦታ እንዳስተላለፉ የመሰከሩ ቢሆንም አመልካች ቦታዉን በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 እና 2443 መሰረት ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት የተደረገ ወይም በግልጽ ኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት መሰረት የተደረገ የሰነድ ማስረጃ በማስረጃነት በማቅረብ አላስረዱም፡፡ይዞታዉን በስጦታ ሰጡ የተባሉት ግለሰብ በሰጡት ምስክርነት በይዞታዉ ላይ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ቤት ሰርተዉ የሚኖሩ መሆኑን ቢመሰክሩም ለተጠሪዎች ይዞታዉን ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ ያልፈረሙ መሆኑን በሰጡት ምስክርነት ቃል አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የስጦታ ውሉን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን መጠየቅ አይችሉም እንጂ በይዞታዉ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ይዞታዉን በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ በስጦታ ዉሉ መሰረት ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት ፍርድ ከሰጠ በኋላ ፍርዱ አመልካች ቤት ሰርተዉ እየኖሩበት ባለዉ ቤት እና ይዞታ ላይ መብት የላቸዉም የሚያሰኝ ዉጤት የለዉም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 279931 ላይ በቀን 22/02/2014 ዓ/ም በተሰጠ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡ አመልካች በቀን 13/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-የስጦታ ውል ስለመደረጉ ባልተካደበትና የስጦታ ዉሉ ፎርምን አልተከተለም በሚል ምክንያት አመልካች ክስ ለመመስረት መብት የላቸዉም መባሉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ የአጻጻፍ ስርዓት ያልተከተለ ዉል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈርስ እስካልጠየቁ ድረስ በሰ/መ/ቁጥር 53328 ላይ እንደተወሰነዉ ከጅምሩ ፈራሽ ነዉ የሚባል አይደለም፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ስጦታ የተደረገዉ በሌላ ሶስተኛ ወገን በመሆኑ ተጠሪዎች ስጦታ ተቀባዮች እንጂ ስጦታ በአድራጊዎች ካለመሆናቸዉም በተጨማሪ ሥጦታ አድራጊዉ ግለሰብ ቀርበዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በስጦታ መስጠታቸዉን መስክረዉ እያለ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1ን እና 2443ን ጠቅሶ ዉሉ ፎርማሊቲዉን አላሟላም ሲል የሰጠዉ ውሳኔ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡በተከራካሪ ወገን የዉል ፎርማሊቲን የሚመለከት ክርክር ቀርቦ ዉሉ እንዲፈርስ እስካልቀረበ ድረስ ፍርድ ቤቱ በራሱ

አነሳሽነት የአጻጻፍ ሥነ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ ውድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 43825 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት በአንድ በኩል የስጦታ ዉሉ ሰነድ እስካልቀረበ ዉሉ ከመሰረቱ የሕግ ዉጤት ስለሌለዉ አመልካች የመጠየቅ መብት የላቸዉም እያለ በሌላ በኩል አመልካች የሥጦታ ዉሉን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን መጤቅ አይችሉም እንጂ በይዞታዉ ላይ መብት እንዳላቸዉ አረጋግጫለሁ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስለዉሎች መፍረስና ሕጋዊ ዉጤት በሕግ የተደነገገዉን የተከተለ አይደለም፡፡ስጦታ አድረጊዎች ዉል በ2000ዓ/ም ፈርመናል እያሉ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ዉል ሳያስቀርብ የሰጠዉ ዉሳኔ ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ አለባቸዉ በሚል በሰ/መ/ቁጥር 22603 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ከአመልካች ጋር በጋራ በመያዝ ስንጠቀም የቆየነዉን ይዞታ ተጠሪዎች ለብቻቸዉ ማስመዝገባቸዉ ተገቢ አይደለም ተብሎ በጋራ የያዝነዉን ይዞታ እኩል 150 ካሬ ሜትር እንዲንካፈል ይወሰንልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ለአመልካችና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ የሰጡ ስለመሆኑ ባለይዞታዉ የነበሩት አቶ ጣሰው አበራ ስር ፍርድ ቤት በመቅረብ ባስረዱበት ሁኔታ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 26/04/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሳቸውንን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ አመልካች በስጦታ ተላልፎልናል ይበሉ እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881፣2427፣2428 እና 2447 መሰረት ቢያንስ በ4 ምስክሮች ፊት የተፈረመና በጽሁፍ የተቋቋመ የስጦታ ዉል በማስረጃነት በማቅረብ የማስረዳት ሸክም እያለባቸው የስጦታ ውል በማስረጃነት አያይዘው አላቀረቡም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ባልቀረበበት ሁኔታ አቶ ጣሰው አበራ አመልካችን ለመጥቀም ሲሉ ስጦታ ሰጥቻለው የሚል ምስክርነት ቢሰጡም ይህ ምስክርነት በሀሰት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እንደ በቂ ማስረጃ ሊቆጠር አይችልም፡፡አንድ ሰዉ ስጦታ ሰጥቻለሁ ስላለ ብቻ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል ሳይኖር ውል አለ የሚል የህሊና ግምት ማሳደር አይቻልም፡፡ እንዲሁም የግለሰቡ ምስክርነት በሰነድ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ የቀረበው አቤቱታዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 13/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በክሱ ላይ እንደገለጹት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን 300 ካሬ ሜትር ይዞታ አቶ ጣሰዉ አባራ ለእኔና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተዉን በየራሳችን ቤት

ሰርተንበት በቤቱ እየኖርን እየተገለገልንበት እያለ ተጠሪዎች ከሕግ አግባብ ውጭ በድብቅ የይዞታውን ስመ ሀብት በስማቸዉ እንዳስመዘገቡ ስለተረዳሁ በስማቸዉ የተመዘገበዉ ተሰርዞ ይዞታውን ለሁለት እኩል እንዲንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች ይዞታውን አገኘሁኝ ያሉበትን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 እና 2443 መሰረት የሕጉን ፎርማሊቲ አሟልቶ የተደረገ የስጦታ ዉል በማስረጃነት ካለማቅረባቸዉም በተጨማሪ ይዞታዉን አቶ ጣሰዉ አበራ ለተጠሪዎች ብቻ በስጦታ ሰጥተዉን ቤት ሰርተን ይዘን የምንገኝበት ስለሆነና አመልካች ከተጠሪዎች ጋር በጥገኝነት ከመኖር ባለፈ ባለይዞታ ስላልሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አቶ ጣሰዉ አበራንና የወ/ሮ አረጋሽ ጫላን ምስክርነት ሰምቶ እነዚህ ምስክሮችም ይዞታዉ የአቶ ጣሰዉ የነበረ መሆኑን፣በዚህ ይዞታ ላይ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ወንድማማቾች ስለሆኑ በይዞታዉ ላይ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ እየኖሩ እንሚገኙና ለተጠሪዎች ይዞታውን በስጦታ ለማስተላላፍ እንዳልፈረሙ ከሰጡት ምስክርነት ቃል ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ቤት ሰርተዉበት በሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ላይ መብት የላቸዉም ባይባልም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 እና 2443 መሰረት የተደረገ የሥጦታ ዉል በማስረጃነት ያላቀረቡ በመሆኑ የስጦታ ዉል መሰረት በማድረግ ክስ መመስረት አይችሉም ሲል መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ በተመለከተዉ መሰረት ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መረዳት የሚቻለዉ አመልካች በይዞታዉ ላይ የባለይዞታነት መብት አገኘሁበት የሚሉት የስጦታ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881 መሰረት የተደረገ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ በማስረጃነት አቅርበዉ ማስረዳት እንዳልቻሉ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ባላቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የአመልካች የክስ ይዘት እንደሚያሳየዉ አመልካች በክሳቸዉ ላይ ስለስጦታ ዉል የጠቀሱት የይዞታዉ ባለይዞታ የሆኑበትን መንገድ ለማሳየት እንጂ በቀጥታ የስጦታ ዉል ይፈጸምልኝ ለማለትና ክርክሩን የዉል ክርክር ለማድረግ አይደለም፡፡በክሱ የጠየቁትም ዳኝነት በስጦታ ዉሉ መሰረት ይፈጸምልኝ የሚል ሳይሆን በጋራ ይዘን ቤት ሰርተን የምንገለገልበትን ይዞታ እኩል እንዲንካፈል ይወሰንልኝ የሚል መሆኑ የሚያሳየዉም የክሱ መሰረት የባለይዞታነት መብት ለማስከበርና በይዞታዉ ላይ የተሰራዉን ቤት ከመፋለም ጋር የተያያዘ ስለሆነ የንብረት ክርክርን የሚመለከት እንጂ የዉል ክርክርን የሚመለከት አለመሆኑን ነዉ፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ የከሳሽን መብት ለመመስረት የሚያስችል እና/ወይም ለተከሳሹ መከላከያ ለመሆን የሚችል በክስ አቤቱታ፣ በመከላከያ መልስ፣ በማስረጃ ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ተከራካሪዎች ተመርምረዉ በሰጡት መልስ ላይ እና በሕግ ላይ ተመስርቶ የሚያዝ ነዉ፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች ክስ መሰረት የንብረት ባለመብትነትን መፋለምን የሚመለከት ነዉ፡፡እንዲሁም ተጠሪዎች የስጦታ ዉሉን ፎርማሊቲ የሚመለከት ክርክር ስላቀረቡ በዚህ ችሎት አመልካች በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ የሰ/መ/ቁጥር 43825 ጠቅሰዉ የፎርማሊቲ ክርክር ተጠሪዎች ሳያነሱ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ማንሳቱ ተገቢ አይደለም በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ሆኖም ተጠሪዎች የስጦታ ዉሉ አድራጊዎች አለመሆናቸዉ ፣ ክሱ ላይ ከላይ እንደተመለከተዉ ስለስጦታ ዉል የተገለጸዉ ይዞታዉ

የተገኘበትን መንገድ ለማሳየት ብቻ መሆኑና ክርክሩ ንብረትን መፋለምን የሚመለከት ክርክር መሆኑ ከግምት ገብቶ ሲታይ አመልካች ይዞታውን አገኘሁበት ያሉት የሥጦታ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881 ስር የተደነገገዉን የዉል አመሰራርት ፎርማሊቲን የሚያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ጭብጥ አይደለም፡፡

የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ እንደሚያሳየዉ የስር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ሰምቶ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአቶ ጣሰዉ አበራ እንደነበርና በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ የመሬት ይዞታውን ይዘዉ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡በአንድ ሰዉ የመሬት ይዞታ ላይ ባለይዞታዉ ሳይቃወም ሕንጻ የገነባ ሰዉ የህንጻዉ ባለቤት እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179/1 ስር ተደንግጓል፡፡ከዚህ የሕግ ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 30101 ላይ (በቅጽ 6 እንደታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 96628 ላይ(በቅጽ 17 እንደታተመዉ) አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች እየተከራከሩ ያሉት በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ ቤት መስራት የቻሉት ይዞታውን ባለይዞታዉ አቶ ጣሰዉ አበራ ቤት እንዲሰሩበት ለእሳቸዉና ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተዋቸዉ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ፡፡ በእርግጥ አንድን ይዞታ ባለይዞታዉ ቤት ሰርቶ እንዲገለገልበት ለሌላ ሰዉ በመፍቀድ የሚፈጽመዉ ድርጊት እና ይዞታውን በስጦታ ዉል መስጠት እንደነገሩ ሁኔታ በንብረት ሕግና በዉል ሕግ መሰረት ታይቶ ሕጋዊ ዉጤታቸዉ ሊወሰን የሚገባ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች ክስ መሰረቱ እና ዳኝነት ጥያቄያቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ባለመብትነትንና ባለይዞታዉ ላይ የተሰራ ቤት ባለሀብትነት መብትን በመፋለም ይዞታውን መከፋልን የሚመለከት እስከሆነ ድረስ በጭብጥነት ተይዘዉ ከማስረጃና ከሕግ አንጻር ተረጋግጠዉ ሊወሰኑ የሚገባቸዉ ጭብጦች፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ አመልካች ቤት በሰሩበት ጊዜ የማን የነበረ ነዉ? አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ የያዙትና በይዞታዉ ላይ ቤት የሰሩት ባለይዞታዉ ፈቅደዉላቸዉ ነዉ ወይ? በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የየራሳቸዉን ቤት ሰርተዉ እየኖሩ ከሆነ የየራሳቸዉን ቤት መስራት የቻሉት ባለይዞታዉ ይዞታውን ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ በጋራ ሰጥተዉ ወይም ፈቅደዉላቸዉ ነዉ ወይስ አይደለም? ወይም ባለይዞታዉ አከራካሪዉን ይዞታ ቤት ሰርቶ እንዲገለገልበት የፈቀዱት ወይም በስጦታ የሰጡት ለማነዉ? የሚሉ ናቸዉ፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እነዚህን ጭብጦች በመያዝ በግራ ቀኙ በተቆጠሩ ማስረጃዎች እና ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ የሰማቸዉ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል አንጻር መርምሮና መዝኖ በሚያረጋግጠዉ ፍሬ ነገር ላይ ተመስርቶ በአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ላይ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ጉዳዩን ከሥጦታ ዉል ፎርማሊቲ አንጻር ብቻ በማየት አመልካች የሕጉን ፎርማሊቲ በጠበቀ መልኩ የተደረገ የስጦታ ዉል ሰነድ በማስረጃነት ስላላቀረቡ በተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት የምስክሮች ቃል እና ሌሎች ማስረጃዎችን ሳይመረምርና ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ የክርክር አመራርና የማስረጃ ምዘና መርሆዎች አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 129931 ላይ በቀን 09/02/2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 279931 ላይ በቀን 22/02/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከላይ በፍርዱ ክፍል የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ የተጠቀሱትን እና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ በማስረጃ አጣርቶና ማስረጃዎችን መዝኖ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስከለ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ ዳኛ በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ ስላማልስማማ የልዩነት ሃሳቤን እንደሚከተለዉ አስፍረያለሁ፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አቶ ጣሰዉ አበራ በ2003 ዓ.ም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ሰጥቶአቸዉ ተረክበዉ ቤት ሰርተዉ ሲኖሩበት እንደነበረ እና በኋላ ይዞታዉን ለሁለት እንካፈል በሚል ስጠይቀዉ 1ኛ ተጠሪ ፍቃደኛ ካለመሆኑም በላይ ይዞታዉን በግሉ አስመዝግቧል የሚል ሲሆን፣ የጠየቀዉ ዳኝነትም ይዞታዉ ለሁለት እኩል እንዲንካፈል ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ አቶ ጣሰዉ ይዞታዉን ለተጠሪዎች እንጂ ለአመልካች አልሰጠም እንዲሁም ቤቱን ያለምንም ተቃዉሞ በራሳቸዉ ገንዘብና ጉልበት የሰሩ መሆኑንና በአመልካች ገንዘብ የተሰራ ቤት አለመኖሩን ጠቅሶ ተከራክረዋል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ እና ግብ የፍትሐብሔር ጉዳዮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን፣ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም ህጉ የተለያዩ መርሆዎችን እና ደንቦችን ይደነግጋል፡፡ በህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በክርክር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ክርክሩ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን ባረጋገጠ መልኩ የሂደቱ ፍትሐዊነት እዉን በማድረግ በመጨረሻ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔም ፍትሐዊ እንዲሆን የሚስያችል ስለመሆኑ እመን ነዉ፡፡ በህጉ በተለያዩ ድንጋጌዎች ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች እና መርሆዎች ዉስጥ አንዱ የጭብጥ አያያዝ ሥርዓትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህም የህጉ አንቀጽ 246(1) ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ

ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸውን ትክክለኛ ጭብጥ መያዝ እንዳለባቸዉ የሚያስገነዝብ ሲሆን፤ ጭብጥ የሚያዘዉም ግራ በጽሁፍ ያቀረቡትን ክስ እና መልስ፣ በህጉ አንቀጽ 241 መሠረት ክስ ሲሰማ ግራ ቀኝ ያነሱትን ክርክር እንዲሁም ማስረጃን መሠረት በማድረግ እንደሆነም በአንቀጽ 248 ላይ ከተመለከተዉ ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች ይዞታው በጋራ የተሰጠን ነዉ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪዎች ስጦታዉ በጋራ አልተሰጠንም የሚል ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ እልባት ለመስጠት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ለአመልካች እና ለተጠሪዎች በጋራ የተሰጠ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚል ነዉ። እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ላይ እንደተመለከተዉ የገጠርም ሆነ የከተማ ይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት ወይም፣ በህግ አግባብ በሚደረግ የስጦታ ዉል፣ ከግለሰቦች በሚሰጥ ስጦታ ወይም በዉርስ ሲሆን ከእነዚህ ዉጪ በዘፈቀደ የይዞታ ባለመብት መሆን አይቻልም። በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ እንደተመለከተዉ አመልካች ያቀረበዉ ክስ መፋለምን የሚመለከት ሲሆን፣ በክሱ የይዞታ መብቱ ምንጭ ስጦታ መሆኑን የጠቀሰዉም በዚሁ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል። በሌላ በኩል ተጠሪዎች በህግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል አላቀረበም የሚል ከዉል ፎርም ጋር የተያያዘ ክርክር አቅርበዋል። እንደሚታወቀዉ ዉል አንድ የተወሰነ ፎርም ተከትሎ እንዲደረግ በህግ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ እንደሆነ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ በህግ የተወሰነዉን ፎርም ተከትሎ ሊደረግ ይገባል። የዉል ፎርም እንደየዉሉ እና የተጠየቀዉ ፎርም ዓይነት የተለያዩ ዓላማዎቹ ያሉት ሲሆን ከዚህ ዉስጥ አንዱ ዉሉ መደረጉን በተመለከተ ክርክር ሲኖር በማስረጃነት እንዲያገልግል ነዉ። የማይንቀሳቀስ ንብረትን በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በጽሑፍ ሆኖ ቢያንስ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበት የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2443 እና 881(1) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል። የከተማ ይዞታን በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ የስጦታ ዉል የሚደረግበትን ፎርም አስመልክቶ በልዩ ሁኔታ የተመለከተ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ከላይ በተመለከተዉ መልኩ በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለተያዘዉ ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል። ስለሆነም አመልካች በይዞታዉ ላይ መብት አግኝቻለሁ ላሉት ምንጩ ስጦታ መሆኑን በክሱ ከገለጸ በእርግጥም ይዞታዉን በስጦታ ያገኘ ስለመሆኑ በህግ አግባብ የተደረገ ዉል አቅርቦ የማስረዳት ግዴታ ያለበት በመሆኑ ተጠሪዎች ከዉሉ ህጋዊነት ወይም ተገቢዉን ፎርም አሟልቶ የተደረገ ዉል በአመልካች አልቀረበም በሚል ያነሱት ክርክር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 248 መሠረት ከግምት ዉስጥ ገብቶ በጭብጥነት ተይዞ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ነዉ። ክርክሩ መፋለምን የሚመለከት ወይም የዉል ይፈጸምልኝ ዳኝነትን የሚመለከት አለመሆኑ እንዲሁም ክሱ የቀረበዉ የስጦታ ዉሉ ተዋዋይ ባልሆነ ሦስተኛ ወገን ላይ መሆኑ ይህ ነጥብ በጭብጥነት እንዳይያዝ ምክንያት ሊሆን አይገባም።

ስለሆነም የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝን የክርክር ነጥብ መሠረት ባደረገ መልኩ አመልካች በህግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል ያቀረበ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ እና በመመርመር አመልካች በክሱ መሠረት ተገቢ የሆነ ማስረጃ አለማቅረቡን በማረጋገጥ ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ትክክለኛ የክርክር አመራር እና የጭብጥ

አመሠራረት ሥርዓትን የተከተለ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ይህ በመሆኑም በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎትም ሊጸና ይገባል የሚል ሃሳብ ስላለኝ ከሌሎች ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ን

የሰ/መ/ቁ. 216561

ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ወ/ሮ ማርታ ጎቤቦ፡- ጠበቃ መንክር ግርማ ቀርበዋል

ተጠሪዎች- 1. አቶ በቀለ አቤሮ፡- ተወካይ ታደሰ በቀለ ቀርበዋል

2. አቶ ዘለቀ ገ/ዮሐንስ፡- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት ሃዲያ ዞን የሴሞ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ እኔ እና 1ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ስንሆን የጋራ ንብረታችን የሆነውን በሸቻና ሮማ ቀበሌ በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ በቀለ አቤሮና ተካሽ፣ በምስራቅ ወዕሎሮ አቤሮ እንዲሁም በምዕራብ መንገድ ከሚያዋስኑት 2.8 ሄክታር የእርሻ መሬት ውስጥ 1000 ካሬ ሜትር የሚሆነውን 1ኛ ተጠሪ በቀን ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ውል በመሬቱ ላይ አራት ክፍል ቤት እንዳለው እና አመልካችም በሌለሁበት በውሉ ላይ እንደፈረምኩ በማስመሰል በብር 80,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠለት በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ሚስቱ ስትሆን ሳላማክራት በቀን ግንቦት ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ውል 530 ካ.ሜ መሬት በብር 80,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ ሸጬለታለሁ፤ በዚህም ምክያት ትዳሬ እና ቤተሰቤ ሰላም በማጣቱ 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲወስድና መሬቱን እንዲመልስ ብጠይቀው ፍቃደኛ አልሆነም፤ ስለሆነም አመልካች በጠየቀቸው መሠረት ህገ-ወጥ የሆነው የገጠር

መሬት ሽያጭ ውል ፈርሶና 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ወስዶ መሬቱን እንዲመልስ ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል። 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተደረገው የቤትና የቦታ ሽያጭ እንጂ የመሬት ሽያጭ ውል አይደለም፤ በውሉም ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት ሲሆን ቤቱን ከገዛሁ በኋላም ከፍተኛ ገንዘብና ጉልበት አውጥቼ በላሜራ ሱቅ እና ውሃ ልክ አሰርቼበታለሁ፤ አመልካች ሽያጩ የንብረት እንጂ የመሬት ባለመሆኑ ህገ-መንግስቱን የሚቃረን አይደለም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ 2ኛ ተጠሪ የገዙት በ530 ካ.ሜ መሬት ላይ ያረፈ አራት ክፍል ቤት እንጂ አመልካች እንደሚሉት 1000 ካ.ሜ የእርሻ መሬት አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል። በመቀጠል የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች በአከራካሪው ውል ላይ እንዳልፈረምኩ ክጄ ተከራክሬ እያለ ፍርድ ቤቱ በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ በፎረንሲክ ሳያረጋግጥ ውሳኔ መስጠቱ፤ አከራካሪው ይዞታ የእርሻ መሬት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ቦታው ድረስ በመሔድ አረጋግጦ እያለ ሽያጩ የቤት ነው በማለት 2ኛ ተጠሪ ያቀረበውን መከራከሪያ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ተፈፀመ በተባለው የሽያጭ ውል ላይ አልፈረምኩም፣ ፍቃዴንም አልሰጠሁም እያሉ ባለበት ሁኔታ ይዞታው የገጠር ነው? ወይስ የከተማ? የሚለው ሳይጣራ ክሳቸው ውድቅ የተደረገበት አግባብ ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ እና ከቤተሰብ ህጉ ጋር ተገናዝቦ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ አመልካች ባቀረበችው አቤቱታ መሠረት ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክርክር በውሉ ላይ ያለመፈረሟን ሳይሆን ተሳስታ የፈረመች መሆኑን በመግለጽ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ተሳስታለች ወይስ አልተሳሳተችም የሚለውን አጣርቶ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ፊርማውን በፎረንሲክ ማስርመር አይጠበቅበትም፤ ውሉ የተደረገውም በገጠር ክልል ውስጥ በተሰራ ቤት ላይ እንጂ በእርሻ መሬት ላይ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነዉ ዉሳኔ ላይ

በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት በተጠሪዎች መካከል በተደረገዉ ዉል የተሸጠዉ በ530 ካ/ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ አራት ክፍል ቤት ስለመሆኑ መረጋገጡን እና በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 2(6) አርሶ አደር በመሬት ላይ በጉልበቱ ያፈራዉን ንብረት መሸጥ እንደሚችል የደነገገ መሆኑን እንዲሁም አመልካች በዉሉ ላይ የፈረሙ ስለመሆኑ ተረጋጧል የሚል ምክንያት በመስጠት ስለመሆኑ የዉኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ፍርድ ቤቶች በዚህ መልኩ የሰጡትን ዉሳኔ በመቀበል የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ በትዕዛዝ ዉድቅ ማድረጉንም ተመልክተናል፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ

መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘዉ በክልሉ የሰማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 12592 ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ.መ.ቁ.216626

ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....ወ/ሮ አለምነሽ ከፈለኝ ፡- ጠበቃ ስጦታ ሽብሩ ቀርበዋል

ተጠሪ፡.....አቶ ዳዊት አበራ ፡- ጠበቃ ዘውዱ ተሾመ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የኑዛዜ ይሻርልኝ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነችዉ ዶ/ር ሜላት አበራ ገ/ሚካኤል የሥር 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274713 በ01/02/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ አባቴ አቶ አበራ ገ/ሚካኤል ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ በመሆኑ የሚች ልጅ መሆኔንና ወራሽነቴን በፍ/ቤት ያረጋገጥኩኝ ሲሆን፤ ከሳሽ ባደረብኝ ሕመም ምክንያት ሰርቼ ለማግኘት የማልችል በመሆኑ አባቴ ቀበል ሊሰጠኝ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሳለ፤ በ6/8/2008 ዓ.ም ባደረገዉ ግልጽ ኑዛዜ ከሳሽ በዝምታ ከዉርስ በመንቀል ተከሳሾች በቀር ሌላ ወራሽ የለኝም የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረቴን 1ኛ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከሳሽ እስከ ሕልፈተ ሕይወቷ ድረስ ለብቻዋ እንዲትጠቀምበት እና ከእርሷ እልፊት በኋላ ለ2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ሜላት አበራ ገ/ሚካኤል እንዲተላለፍ የተናዘዘዉ ከሕግና ከሞራል የሚቃረን በመሆኑ እንዲሻርልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት ክርክር ሟች ያደረገዉ ኑዛዜ በፍ/ቤት የጸደቀ በመሆኑ እስካልተሻረ ድረስ አስገዳጅነት አለዉ፤ ኑዛዜዉ በገደብ የተደረገ ነዉ እንጂ ከሳሽ ከዉርስ የነቀለ ስላልሆነ ከሕግና ከሞራል የሚቃረን አይደለም፤ ኑዛዜዉ ሊሻር አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ሟች አቶ አበራ ገ/ሚካኤል በሕይወት እያለ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበዉ ሚያዚያ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ወደታች የሚቆጠረዉን ተወላጅ የሆነዉን ከሳሽን በቂና አሳማኝ ምክንያት ሳያስቀምጥ በዝምታ ከዉርስ የነቀለ በመሆኑ ይህ ደግሞ የዉርስ ሕግ አንቀጽ 938 (1) እና የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ያሳለፋቸዉን አስገዳጅ ዉሳኔዎችን የሚቃረን በመሆኑ ኑዛዜዉ ተሽሯል/ዉድቅ ሆኗል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ህዳር 16 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ ሟች አቶ አበራ ገ/ሚካኤል ያደረጉትን ኑዛዜ እንዲሻርልኝ ብሎ ለመጠየቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነዉ፡፡ ሟች ሚያዚያ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ቤት የጸደቀ እና የሚሻርበትም ምክንያት የለም፡፡ አመልካች እና የሟች ልጆች ከዚህ ቀደም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ.107782 ላይ በተደረገዉ የኑዛዜ ይሻርልን ክርክር በ16/4/2012 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ሟች አመልካች እስከእልፊተ ሕይወቴ ድረስ እንዲጠቀምበት ያደረጉት የኑዛዜ ክፍል ሊሻር አይገባም በማለት ወስኖ እያለ፤ አሁን በዚህ ክርክር የሥር ፍ/ቤት ሟች ያደረጉትን ኑዛዜ ያለምንም የህግ ምክንያት እንዲሻር መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ተሽሮ ወይም ተሻሽሎ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም ተብሎ እንዲጸናልኝ፤ ይህ ካልሆነ አመልካችን የሚመለከተዉ የኑዛዜ ክፍል እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች እና በሌሎች ተወላጆች መካከል በነበረዉ ክርክር በመ.ቁ.107782 ላይ የሟች ኑዛዜ ላይ ሟች ለአመልካች ያደረጉት ኑዛዜ አይፈርስም ለ2ኛ ተከሳሽ የተደረገዉ የኑዛዜ ክፍል ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስኖ እያለ አሁን በዚህ ክርክር ኑዛዜዉ እንዲፈርስ፣ የመባሉን አግባብ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ በአህምሮ ሕመም ምክንያት በፍርድ ተከልክዬ በሞግዚት አስተዳደር ሥር የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጦ፣ ሟች አባቴ ለተጠሪ ቀለብ የመስጠት ግዴታዉን ወደ ጎን በመተዉ በዝምታ ከዉርስ የነቀለኝ መሆኑን በማረጋገጥ

ኑዛዜዉ ፊርሶ የሚች ወራሾች የዉርስ ሀብቱንና እዳዉን እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ እኔ አሁን ያቀረብኩኝ ክርክር እነ ጥሩወርቅ አበራ በመ.ቁ.107782 ላይ ካቀረቡት ክርክር ጭብጥና አዉድም የተለያየ ነዉ፡፡ ከተጠሪ አንጻር ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ከሕግና ከሞራል የሚቃረን መሆኑ ተረጋግጦ ኑዛዜዉ እንዲሻር መወሰናቸዉ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ሊሻር ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ የህግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ እንዲጸልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የመ.ቁ.107782 እና 114129 የሆኑት መዛግብት ከሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ሚች አባቴ አቶ አበራ ገ/ሚካኤል በሕይወት እያሉ ሚያዚያ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ያደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ያለምክንያት በዝምታ ከዉርስ የነቀለኝ ስለሆነ እንዲሻርልኝ የሚል ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በበኩሏ ቀደም ሲል ከሌሎች ወራሾች እነ ጥሩወርቅ አበራ ጋር በመ.ቁ.107782 ላይ በዚህ ጉዳይ ዉሳኔ የተሰጠ ስለሆነ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 መሰረት ቀርቦ እንዲታይልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡በዚህ መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.114129 በ2/7/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት አመልካች የመ.ቁ.107782የሆነዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 መሰረት ቀርቦ እንዲታይልኝ በማለት ባመለከተችዉ መሰረት ይህ መዝገብ ከቀጠሮ በፊት ቀርቦ መዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም መዝገቡ ቀርቦ መያያዙን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህም በላይ ፍ/ቤቱ በሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ላይ አመልካች ከመ.ቁ.107782 አንጻር ያነሳችዉን ክርክር በተመለከተ ያለዉ ነገር መኖሩን የዉሳኔዉ ግልባጭ የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ ከሌሎች ፍ/ቤቶች ወይም ከሌላ ክፍል እንዲቀርብ የሚጠየቀዉ ጽሑፍ፣ መዝገብ ወይም ሰነድ የሚጠየቅበትና የሚቀርብበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 ድንጋጌ ሥር ተመለክቶ እናገኛለን፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት በሌላ ፍ/ቤት ዘንድ የሚገኝ መዝገብ፣ ሰነድ፣ የጽሑፍ ማስረጃና ማንኛዉም ፍርድ የተሰጠበትን መዝገብ አስቀርቦ ለመመርመር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ.89494 ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ.ም (ቅጽ 15) በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ የፍ/ቤትን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻልበትን አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 (1፣ 2) ድንጋጌን በመተርጎም መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ፍ/ቤት አመልካች የመ.ቁ.107782 ቀርቦ እንዲታይልኝ በማለት ያመለከተችዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 አንጻር ሲታይ ተገቢ መሆኑን በመቀበል መዝገቡ ቀርቦ ከመ.ቁ.114129 ጋር እንዲያያዝ ካዘዘ በኋላ መዝገቡ በትዕዛዙ መሰረት ቀርቦ መያያዙ ሳይረጋገጥ፣ አመልካች ከዚህ አንጻር ያነሳችዉ ክርክር ምንም ሳይባል ዉሳኔ መሰጠቱ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ የሥር የይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ጉዳይ ማረም ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ማጽናቱ ተገቢ አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የመ.ቁ.107782 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145 መሰረት እንዲቀርብልኝ በማለት የጠየቀችዉ አስቀርቦ ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከዚህ መዝገብ አንጻር አመልካች ያነሳችዉን ክርክር በዝምታ በማለፍ ዉሳኔ መሰጠቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ማረም ሲገባዉ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.114129 በ20/8/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.274713 በ1/2/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.145 መሰረት ቀርቦ እንዲታይላት የጠየቀችዉን የመ.ቁ.107782 የሆነዉን በማስቀረብ ከዚህ አንጻር የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ይህ ችሎት ህዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. የመ.ቁ.107782 እና 114129 የሆኑት መዛግብት በመጡበት አግባብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት ይመለሱ ብለናል፡፡
7. ይህ ዉሳኔ ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁጥር 217051

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኦርጋኒክ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስ/አስኪያጅ ቀርበዋል

ተጠሪ ፡- ኦሮሚያ ብድር እና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር -- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ በብድር የተሰጠ ገንዘብ አመላለስን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ግንቦት 9 ቀን 2013 ዓ.ም በአጭር ስነ ስርዓት ባቀረበው ክስ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 9 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል አመልካች ከ13% ወለድ ጋር ለመክፈል ተስማምቶ ብር 500,000 የተበደረ ቢሆንም ብድሩን ሳይከፍል 32 ወራት ስለቆየ ዋናውን ገንዘብ ብር 500,000፣ ወለድ ብር 188,980.36፣ በውሉ መሰረት ብድሩን ባለመክፈሉ በየቀኑ የሚታሰብ 0.25% መቀጮ ብር 450,000 በድምሩ ብር 1,138,890.36 እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት አመልክቶ ተፈቅዶለት ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ የብድር መክፈያው ቀኑ መስከረም 9 ቀን 2014 ዓ.ም ስለሆነ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን አመልካች እራሱ መቃወሚያውን በስህተት ያነሳው መሆኑን በመግለፁ እና ፍርድ ቤቱም በፍሬ ጉዳይ የሚታይ ነው በሚል አልፎታል። በፍሬ ጉዳይ ላይ ብር 40,000 ከፍዬ እያለ ተቀናሽ አለመደረጉ አግባብ አይደለም፤ ክፍያውን ያልከፈልኩት በኮረና ወረርሽኝ እና በፀጥታ ችግር ምክንያት ገንዘቡን የተበደርኩበት ስራ ችግር ስለገጠመው ነው፤ 0.25% መቀጮም ከመስከረም 9 ቀን 2014 በኋላ ላለው ጊዜ እንጂ ከዚያ በፊት ላለው ሊታሰብ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

በክስ መስማት ጊዜም አመልካች ዋናውን ገንዘብ እና ወለዱን መክፈል ያለበት መሆኑን አምኖ መቀጮ ልከፍል አይገባም ብሎ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መስከረም 9 ቀን 2011 ዓ.ም ከተደረገው የብድር ውል ጋር አብሮ ከመረመረ በኋላ በውሉ መነሻነት አመልካች ብር 500,000 ከ13% ወለድ ጋር ለመክፈል ተስማምቶ ተበድሯል። በውሉ መሰረት የማይመለስ ከሆነም ብድሩን ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በቀን 0.25% ወለድ ለመክፈል ስለተስማማ መቀጮው ሊታሰብ የሚገባው የመክፈያ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ መሆን አለበት በማለት አመልካች ያነሳው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም። በመሆኑም ዋናውን የብድር ገንዘብ ብር 500,000፣ ወለድ ብር 188,890.36 እንዲሁም ብድሩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ባለመክፈል በ0.25% የሚታሰብ መቀጮ ብር 450,000 በድምሩ ብር 1,138,890.36 እና ወጪ እና ኪሳራ ብር 1,500 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል።

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል።

አመልካች ህዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው። የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ክስ ከመመስረቱ በፊት ብር 40,000፣ ክስ ከተመሰረተ በኋላ ብር 100,000 በድምሩ ብር 140,000 የከፈልኩ መሆኑን በፅሑፍም ሆነ በቃል ክርክር ጠቅሼ ተከራክሬ እያለው እንዲሁም አመልካችም ይህን ባልካደበት ገንዘቡን በድጋሜ እንድከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም። አመልካች በዋናው ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ብቻ እንድከፍል መወሰን ሲገባው መቀጮን ጨምሮ እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 12 በሰ/መ/ቁጥር 59882 ከወለድ በተጨማሪ ኪሳራ ለመክፍል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ነው በሚል የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም ግለሰቦችን ጨምሮ በብድር እና ቁጠባ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነውን የፍ/ሕ/ቁጥር 2489(2) የሚቃረን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ወለድ እና ቅጣትን አንድ ላይ እንዲከፍል የወሰኑበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁጥር 2489 አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል።

ተጠሪም ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በሁለት ዙር ብር 140,000 የከፈለው መሆኑን አምኖ ቅጣትን በሚመለከት በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል አመልካች ብድሩን በተባለው ጊዜ የማይከፍል ከሆነ በየቀኑ የሚታሰብ መቀጮ እንደሚከፈል ተስማምተናል፡፡ ይህም የፍ/ሕ/ቁ 1889ን መሰረት ያደረገ ነው፤ የፍ/ሕ/ቁ/ 2489(2) ድንጋጌም ወለድን እንጂ መቀጮን የሚመለከት ስላልሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያነሳው ክርክር እና የተጠቀሰው የሰበር ውሳኔ ለጉዳዩ ተገቢነት የለውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በበኩሉ ጥር 13 ቀን 2014 የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ከክርክር በፊት እና በክርክር ላይ እያለን የከፈልኩት በድምሩ ብር 140,000 ተቀናሽ አለመደረጉ እንዲሁም ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንድከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከብድር ገንዘቡ ብር 140,000 መክፈሉን አምኖ ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ አመልካች የብድር ገንዘቡን አለመክፈሉን መነሻ በማድረግ ክስ ከመመስረቱ በፊት አመልካች ብር 40,000 እንዲሁም በክርክር ላይ እያሉ ብር 100,000 በድምሩ ብር 140,000 የከፈለ መሆኑን እና ይህ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ተቀናሽ እንዲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በፅሁፍ እንዲሁም በቃል ባቀረበው ክርክር መግለፁን ጠቅሶ የሚያቀርበውን መከራከሪያ ተጠሪ በግልፅ ያመነ በመሆኑ ይህ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ተቀናሽ እንዲሆን አለመወሰኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 ድንጋጌን የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ሌላው መታየት ያለበት አመልካች ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 9 ቀን 2011 ዓም በተፈረመው የብድር ውል አመልካች ዋና የብድር ገንዘብ ብር 500,000 ከ13% ወለድ ጋር ለመመለስ ተስማምቶ መውሰዱ፤ ገንዘቡ በወቅቱ ባይመለስ በየቀኑ የሚታሰብ 0.25% መቀጮ ሊከፍል መስማማቱ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም ቢሆን የዚህን ውል ይዘት በመካድ የሚያቀርበው መከራከሪያ የለም፡፡ ይልቁንም አመልካች የሚከራከረው ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ ለመክፍል የሚደረግ ስምምነት ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚጠቅሰው የፍ/ሕ/ቁጥር 2489(2) ድንጋጌን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59882 የሰጠውን ውሳኔ ነው፡፡ የብድር ገንዘብ አመላለስን አስመልክቶ ተበዳሪው የብድር ገንዘቡን በውል በተጠቀሰው ጊዜ ሳይከፍል ካዘገየ አበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፍለው

ወለድ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2489(1) የተመላከተ ሲሆን በሕግ ከተገለፀው ወለድ መጠን በላይ ተበዳሪው መቀጫ እንዲከፍል የሚደረግ ስምምነት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በንኡስ አንቀፅ 2 ላይ ተመላክቷል፡፡ ከላይ በተገለፀው ሰበር መዝገብ ቁጥርም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህንኑ በማጠናከር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የተጠቀሰው ድንጋጌም ሆነ ውሳኔ በግለሰቦች መካከል በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ከወለድ በተጨማሪ መቀጮን ለመክፍል ስምምነት የተደረገ እንደሆነ ባለእዳው ከወለድ በተጨማሪ መቀጮን ሊከፍል የማይገባ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የብድር ውል ስምምነቱ የተደረገው በግለሰብ እና በአበዳሪ ተቋም መካከል እንጂ በሁለት ግለሰቦች መካከል አይደለም፡፡ እነኚህ አበዳሪ ተቋማት በብድር የሚሰጡት በዋናነት ከሕዝብ በቁጠባ መልክ የሚሰበስቡትን ገንዘብ እንዲሁም ከባለአክሲዮኖቻቸው የሚሰበስቡትን ገንዘብ በሕግ በተፈቀደላቸው የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት የሚያገኙትን ገንዘብ ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰበሰበው ገንዘብ የሕዝብ ጥቅም ያለበት በመሆኑ በግለሰቦች መካከል ብድርንና አመላለሱን አስመልክቶ ከሚደረጉ ስምምነቶች በተለየ ካልታየ የፋይናንስ ስርዓቱ ላይ ተፅእኖ በማሳድር የሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ በዚህ ጊዜ በፍ/ሕ/ቁጥር 1889 ላይ እንደተመለከተው ተዋዋዮች አስቀድመው በውላቸው መቀጫ እንደሚከፈል ከተስማሙ በስምምነታቸው መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም አመልካች የብድር ገንዘቡን ሳይከፍል የመክፈያ ጊዜው ማለፉ እስከታመነ ድረስ ከወለዱ በተጨማሪ በብድር ውሉ በተገለፀው አግባብ መቀጮ እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41925 ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 345509 ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ብር 1,138,890.36 ላይ መክፈሉ የተረጋገጠው ብር 140,000 ተቀናሽ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ይህ ገንዘብ ተቀንሶ የሚመጣው ቀሪ ገንዘብ ከነወለዱ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሁኖ መቀጮ እንዲሁም ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙን የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ.ቁ 216709

ቀን፡- 1/4/2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሱልጣን አባተማም

ምዕላል ኃይለ

ዋዚሞ ዋሲራ

አመልካች፡ቾች- እነ ኦሜጋ የወርቅ ግብይት ማህበር ጠበቃ አክሊሉ ኤርሚያስ

ተጠሪ፡/ዎች- እነ አቦቦ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት

መዝገቡ ከቀነ ቀጠሮ በፊት ሊቀርብ የቻለው አመልካች 30/3/2014 ዓ.ም በተፃፈ ቃለ መሃላ አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ለዚህ ችሎት 16/3/2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የጋምቤላ ብ/ክ/መ/ጠ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01080/2014 በ 16/3 /2014 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፆ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ መሰረት መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

ትዕዛዝ

ያሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ይሁን የምንሰራውን ፈቃዳችን ነጥቆ እንዳንሰራ አደረገን የሚል ሲሆን ፍ/ቤት ግራቀኝ በፍሬ ነገር ሣያከራክር የመክሰስ መብት የላችሁም በማለት የወሰነበት አግባብነት

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል፡፡

1.መጥሪያ ለተጠሪ/ዎች/ ይድረስ ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቀጠሮ ለ 25/4/2014 ዓ.ም ተቀጥሮአል፡፡ 5፡20 ሰዓት

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 216938

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች - አቶ ደረጀ ቢያዝን

ተጠሪ - ፋል ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል የስራ ቅጥር ዉልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በግንባታ መሃንዲስነት በወር ብር 40,000.00 ደሞዝ፣ ብር 17,000.00 አበል እና ብር 14,300.00 የትርፍ ሰዓት ዓበል እየተከፈለዉ ሲሰራ መቆየቱን ነገር ግን ተጠሪ መስከረም 12 ቀን 2013 በተፃፈ ደብዳቤ ከፕሮጀክቱ የስራ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የስራ ውሉ ተቋርጧል በማለት በህገ ወጥ መንገድ የስራ ዉሉን ያቋረጠ መሆኑን ጠቅሶ ወደ ስራዉ እንዲመለስ አሊያም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ይወሰኑለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬ ነገር ደረጃ ከደመወዝ ዉጪ ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ በፍሬ ነገሩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች ከስራ የተሰናበቱት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የስድስት ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ያስቀርባል ካለ በኋላ ግራ ቀኙን አከራክሮ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ብይን እና ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሲያፀና አመልካች እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸው አለመወሰኑን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሲያፀና ለአሁን አመልካች እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸው ሳይወስን ያለፈበት አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀፅ 43(5) አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መጋቢት 09 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳያቀርብ ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረብ ስለሌለበት ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተኝ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጠው መልስ ደግሞ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ በነበረን ክርክር የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ትክክል ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ብቻ የተከራከረ ሲሆን ውሳኔው የሚፀና ከሆነ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ክርክር ያላቀረበ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ወደ ስራዉ እንዲመለስ የተሰጠ ዉሳኔ እንደ ጸና ያለ ስለመሆኑ ግራ ቀኝን አላከራከረም፡፡ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ሠራተኛዉ ወደ ስራ ገበታዉ ሲመለስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የስራ ክርክር ችሎት ለሠራተኛዉ የስድስት ወር ዉዝፍ ደመወዝ እንደሚወስንለት፣ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሠራተኛዉ ወደ ስራ መመለስ ዉሳኔ ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ዉዝፍ ደመወዝ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሊወስን እንደሚገባ ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(5) ላይ ከተመለከቱት ግልጽ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀዉ አንድ ሠራተኛ በህገ ወጥ መልኩ ከስራ ተሰናብቶ ጉዳዩን በተለያዩ የዉሳኔ ሰጪ አካላት ፊት በማቅረብ ሲከራከር የተወሰኑ ጊዜያትን ማሳለፉ አይቀርም፡፡ የክርክሩ ዉጤትም የአሠሪዉ ሕገ ወጥ ድርጊት መረጋገጥና ሠራተኛዉም ወደ ስራዉ እንዲመለስ የሚታዘዝበት ከሆነ ጉዳዩ ለወሰደበት ወራት ስራ ሳይሰራ በመቆየቱ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ወጪዎችንም በማዉጣት ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡ ስለዚህ የዉዝፍ ደመወዝ እንዲህ ዓይነት ጉዳት ለመካስ የሚያገለግል ሲሆን አጠቃላይ ዓላማዉም አሠሪዉ ሠራተኛዉን በህገ ወጥ መልኩ ከስራዉ

አሰናብቶት በመቆየቱና ስራ ባለመስራቱ ምክንያት የሚያጣዉን ደመወዝ ለመተካት እንደሆነ ይታመናል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት በግራ ቀኝ መካከል የነበረዉ የስራ ዉል የተቋረጠዉ መስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ መዝገቡ ላይ አከራክሮ ዉሳኔ የሰጠዉ ከአንድ ዓመት በኋላ ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም ነዉ፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ወደ ስራ ገበታዉ እንዲመለስ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ካጸና የአንድ ዓመት ዉዝፍ ደመወዝ ለአመልካች እንዲከፈል የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ በአዋጁ በፍርድ ቤት ላይ የተጣለ ኃላፊነት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ይህን ለመወሰን ክርክሩ የግድ ከተጠሪ እንዲቀርብ አይጠበቅም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ወደ ስራ ገበታዉ እንዲመለስ የተሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቶ ነገር ግን የአንድ ዓመት ዉዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለዉ አለመወሰኑ ከላይ የተመለከተዉን የአዋጁን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን በተመለከተ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከስራ ክርክር ችሎት የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ የማይባልበት የመጨረሻ ዉሳኔ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 140(2) ላይ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነበረበት በማለት ተጠሪ የሚያቀርበዉ መከራከሪያ ተገቢነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 274880 ላይ ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የአንድ ዓመት ዉዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራ ገበታዉ እንዲመለስ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁጥር 217051

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኦርጋኒክ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስ/አስኪያጅ ቀርበዋል

ተጠሪ ፡- ኦሮሚያ ብድር እና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር -- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ በብድር የተሰጠ ገንዘብ አመላለስን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ግንቦት 9 ቀን 2013 ዓ.ም በአጭር ስነ ስርዓት ባቀረበው ክስ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 9 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል አመልካች ከ13% ወለድ ጋር ለመክፈል ተስማምቶ ብር 500,000 የተበደረ ቢሆንም ብድሩን ሳይከፍል 32 ወራት ስለቆየ ዋናውን ገንዘብ ብር 500,000፣ ወለድ ብር 188,980.36፣ በውሉ መሰረት ብድሩን ባለመክፈሉ በየቀኑ የሚታሰብ 0.25% መቀጮ ብር 450,000 በድምሩ ብር 1,138,890.36 እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት አመልክቶ ተፈቅዶለት ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ የብድር መክፈያው ቀኑ መስከረም 9 ቀን 2014 ዓ.ም ስለሆነ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን አመልካች እራሱ መቃወሚያውን በስህተት ያነሳው መሆኑን በመግለፁ እና ፍርድ ቤቱም በፍሬ ጉዳይ የሚታይ ነው በሚል አልፎታል። በፍሬ ጉዳይ ላይ ብር 40,000 ከፍዬ እያለ ተቀናሽ አለመደረጉ አግባብ አይደለም፤ ክፍያውን ያልከፈልኩት በኮረና ወረርሽኝ እና በፀጥታ ችግር ምክንያት ገንዘቡን የተበደርኩበት ስራ ችግር ስለገጠመው ነው፤ 0.25% መቀጮም ከመስከረም 9 ቀን 2014 በኋላ ላለው ጊዜ እንጂ ከዚያ በፊት ላለው ሊታሰብ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

በክስ መስማት ጊዜም አመልካች ዋናውን ገንዘብ እና ወለዱን መክፈል ያለበት መሆኑን አምኖ መቀጮ ልከፍል አይገባም ብሎ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መስከረም 9 ቀን 2011 ዓ.ም ከተደረገው የብድር ውል ጋር አብሮ ከመረመረ በኋላ በውሉ መነሻነት አመልካች ብር 500,000 ከ13% ወለድ ጋር ለመክፈል ተስማምቶ ተበድሯል። በውሉ መሰረት የማይመለስ ከሆነም ብድሩን ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በቀን 0.25% ወለድ ለመክፈል ስለተስማማ መቀጮው ሊታሰብ የሚገባው የመክፈያ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ መሆን አለበት በማለት አመልካች ያነሳው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም። በመሆኑም ዋናውን የብድር ገንዘብ ብር 500,000፣ ወለድ ብር 188,890.36 እንዲሁም ብድሩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ባለመክፈል በ0.25% የሚታሰብ መቀጮ ብር 450,000 በድምሩ ብር 1,138,890.36 እና ወጪ እና ኪሳራ ብር 1,500 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል።

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል።

አመልካች ህዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው። የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ክስ ከመመስረቱ በፊት ብር 40,000፣ ክስ ከተመሰረተ በኋላ ብር 100,000 በድምሩ ብር 140,000 የከፈልኩ መሆኑን በፅሑፍም ሆነ በቃል ክርክር ጠቅሼ ተከራክሬ እያለው እንዲሁም አመልካችም ይህን ባልካደበት ገንዘቡን በድጋሜ እንድከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም። አመልካች በዋናው ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ብቻ እንድከፍል መወሰን ሲገባው መቀጮን ጨምሮ እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 12 በሰ/መ/ቁጥር 59882 ከወለድ በተጨማሪ ኪሳራ ለመክፍል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ነው በሚል የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም ግለሰቦችን ጨምሮ በብድር እና ቁጠባ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነውን የፍ/ሕ/ቁጥር 2489(2) የሚቃረን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ወለድ እና ቅጣትን አንድ ላይ እንዲከፍል የወሰኑበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁጥር 2489 አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል።

ተጠሪም ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በሁለት ዙር ብር 140,000 የከፈለው መሆኑን አምኖ ቅጣትን በሚመለከት በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል አመልካች ብድሩን በተባለው ጊዜ የማይከፍል ከሆነ በየቀኑ የሚታሰብ መቀጮ እንደሚከፈል ተስማምተናል፡፡ ይህም የፍ/ሕ/ቁ 1889ን መሰረት ያደረገ ነው፤ የፍ/ሕ/ቁ/ 2489(2) ድንጋጌም ወለድን እንጂ መቀጮን የሚመለከት ስላልሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያነሳው ክርክር እና የተጠቀሰው የሰበር ውሳኔ ለጉዳዩ ተገቢነት የለውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በበኩሉ ጥር 13 ቀን 2014 የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ከክርክር በፊት እና በክርክር ላይ እያለን የከፈልኩት በድምሩ ብር 140,000 ተቀናሽ አለመደረጉ እንዲሁም ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንድከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከብድር ገንዘቡ ብር 140,000 መክፈሉን አምኖ ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ አመልካች የብድር ገንዘቡን አለመክፈሉን መነሻ በማድረግ ክስ ከመመስረቱ በፊት አመልካች ብር 40,000 እንዲሁም በክርክር ላይ እያሉ ብር 100,000 በድምሩ ብር 140,000 የከፈለ መሆኑን እና ይህ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ተቀናሽ እንዲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በፅሁፍ እንዲሁም በቃል ባቀረበው ክርክር መግለፁን ጠቅሶ የሚያቀርበውን መከራከሪያ ተጠሪ በግልፅ ያመነ በመሆኑ ይህ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ተቀናሽ እንዲሆን አለመወሰኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 ድንጋጌን የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ሌላው መታየት ያለበት አመልካች ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 9 ቀን 2011 ዓም በተፈረመው የብድር ውል አመልካች ዋና የብድር ገንዘብ ብር 500,000 ከ13% ወለድ ጋር ለመመለስ ተስማምቶ መውሰዱ፤ ገንዘቡ በወቅቱ ባይመለስ በየቀኑ የሚታሰብ 0.25% መቀጮ ሊከፍል መስማማቱ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም ቢሆን የዚህን ውል ይዘት በመካድ የሚያቀርበው መከራከሪያ የለም፡፡ ይልቁንም አመልካች የሚከራከረው ከወለድ በተጨማሪ መቀጮ ለመክፍል የሚደረግ ስምምነት ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚጠቅሰው የፍ/ሕ/ቁጥር 2489(2) ድንጋጌን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59882 የሰጠውን ውሳኔ ነው፡፡ የብድር ገንዘብ አመላለስን አስመልክቶ ተበዳሪው የብድር ገንዘቡን በውል በተጠቀሰው ጊዜ ሳይከፍል ካዘገየ አበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፍለው

ወለድ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2489(1) የተመላከተ ሲሆን በሕግ ከተገለፀው ወለድ መጠን በላይ ተበዳሪው መቀጫ እንዲከፍል የሚደረግ ስምምነት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በንኡስ አንቀፅ 2 ላይ ተመላክቷል፡፡ ከላይ በተገለፀው ሰበር መዝገብ ቁጥርም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህንኑ በማጠናከር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የተጠቀሰው ድንጋጌም ሆነ ውሳኔ በግለሰቦች መካከል በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ከወለድ በተጨማሪ መቀጮን ለመክፍል ስምምነት የተደረገ እንደሆነ ባለእዳው ከወለድ በተጨማሪ መቀጮን ሊከፍል የማይገባ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የብድር ውል ስምምነቱ የተደረገው በግለሰብ እና በአበዳሪ ተቋም መካከል እንጂ በሁለት ግለሰቦች መካከል አይደለም፡፡ እነኚህ አበዳሪ ተቋማት በብድር የሚሰጡት በዋናነት ከሕዝብ በቁጠባ መልክ የሚሰበስቡትን ገንዘብ እንዲሁም ከባለአክሲዮኖቻቸው የሚሰበስቡትን ገንዘብ በሕግ በተፈቀደላቸው የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት የሚያገኙትን ገንዘብ ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰበሰበው ገንዘብ የሕዝብ ጥቅም ያለበት በመሆኑ በግለሰቦች መካከል ብድርንና አመላለሱን አስመልክቶ ከሚደረጉ ስምምነቶች በተለየ ካልታየ የፋይናንስ ስርዓቱ ላይ ተፅእኖ በማሳድር የሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ በዚህ ጊዜ በፍ/ሕ/ቁጥር 1889 ላይ እንደተመለከተው ተዋዋዮች አስቀድመው በውላቸው መቀጫ እንደሚከፈል ከተስማሙ በስምምነታቸው መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም አመልካች የብድር ገንዘቡን ሳይከፍል የመክፈያ ጊዜው ማለፉ እስከታመነ ድረስ ከወለዱ በተጨማሪ በብድር ውሉ በተገለፀው አግባብ መቀጮ እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41925 ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 345509 ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ብር 1,138,890.36 ላይ መክፈሉ የተረጋገጠው ብር 140,000 ተቀናሽ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ይህ ገንዘብ ተቀንሶ የሚመጣው ቀሪ ገንዘብ ከነወለዱ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሁኖ መቀጮ እንዲሁም ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙን የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 217190

ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡-

1. አቶ ደጉ ማደቦ
2. አቶ አሸናፊ ማደቦ
3. ወ/ሮ አዳነች ማደቦ
4. ዶ/ር ተስፋዬ ማደቦ
5. ወ/ሮ ደመቀች ማደቦ
6. አቶ መኩሪ ማደቦ

ጠበቃ አሰፋ ካሣ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ውዴ ኡመር፡- ጠበቃ ማንጉዳይ ወንድሙ ቀርበዋል

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት ሚች የአመልካቾች አባት አቶ ማደቦ ሀይዴቦ ከአመልካች ወላጆች እናት ጋር ያፈሩትን የጋራ ንብረት ከአመልካቾች ስምምነት ውጪ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ በሚፃረር መልኩ " ጠቅላላ ንብረቱን ለተጠሪ ሰጥቻለሁኝ " በማለት የቀረበው የጋብቻ ማሻሻያ ውል ልጆቻቸው የሆኑ የአመልካቾችን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖእያለ በፍርድ ቤት መጽደቁ አግባብ አይደለም በማለት የጋብቻ ማሻሻያ ውሉን ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሻሩ ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው እና የሰበር ሰሚ ችሎቾችም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን መጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት በሰበር ለማሳረም ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስቀርባል ተብሎ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ ሚች የአመልካቾች አባት አቶ ማደሶ ሀይደሶ እና በተጠሪ መካከል ነሐሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም ተደርጎ በመዝገብ ቁጥር 01940 ላይ መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፀደቀውን የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመቃወም አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የተጀመረ ክርክር ሲሆን የሰበር ተጠሪም መቃወሚያው በቀረበበት የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት የመቃወሚያ ተጠሪ ነበሩ። አመልካቾች ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘት፡- የአመልካቾች አባት አቶ ማደሶ ሀይደሶ ሚያዝያ 15 ቀን 2012 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ተከትሎ የአባታቸው ወራሾች መሆናቸውን በማረጋገጥ ውርስ እንድጣራ ላቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ በሰጡት መልስ የሚችና የተጠሪ ጋብቻ ውል ተሻሽሎ ሚች አባታቸው በንብረት ድርሻ ላይ ያለውን መብት ሙሉ በሙሉ በመተው ያደረገው በፍርድ ቤት የፀደቀውን የጋብቻ ማሻሻያ ስምምነት በማስረጃነት ተያይዞ መቅረቡን ገልጸው ፤ የጋብቻ ውሉ መጽደቅ የለበትም የሚሉበትን ምክያት ስዘረዝሩ፡- ተጠሪ ሚች ድርሻውን ሙሉ በሙሉ ሰጥቶኛል የሚሉት ንብረት ሚች የአመልካቾች አባት አቶ ማደሶ ሀይደሶ ከሚች የአመልካቾች ወላጅ እናት ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ ጋር በትዳር እያሉ የተፈራ ሲሆን ፤ ይህንኑ ንብረት ለተጠሪ ስጦታ ማድረጋቸውን በመቃወም አቤቱታ አቀርበው የሀዋሳ ዙሪ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111/85 ላይ ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሚቹ ከአመልካቾች ስምምነት ውጭ ጠቅላላ ንብረቱን እንዳይሸጡ ፤ እንዳይለውጡ በስጦታ እንዳያስተላልፉ የተሰጠ ውሳኔ ፀንቶ መኖሩን ፤ አመልካቾች የእናታቸው ወራሽነት በማረጋገጥ የውርስ ሃበት ተጣርቶ የቀረበው ሪፖርት ጥቅምት 6 ቀን 1991 ዓ/ም በመዝገብ ቁጥር 96/87 መጽደቁን በመቃወም ሚች አቶ ማደሶ ሀይደሶ ያቀረቡት ይግባኝ ውድቅ ሆኖ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታህሳስ 7 ቀን 1991 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14/91 ፀንቶ በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 1060 መሠረት ሳይነጣጠል ሚች እና አመልካቾች የጋራ ባለሀብት የሆኑበትን ንብረት ለተጠሪ መተላለፉ አግባብነት የሌለው መሆኑን ፤ የጋብቻ ውሉም በሁለት የባል ወገን ምስክሮች መረጋገጥ ሲገባው በውሉ ላይ የፈረሙት አራቱም ምስክሮች የተጠሪ ወገኖች መሆናቸው ውሉን ፈረሽ የሚያደርገው መሆኑን ፤ ሚች ዕድሜውን ሙሉ ከአመልካቾች እናታ ጋር ያፈራውን ሙሉ ንብረቱን 2ኛ ሚስት ለሆነች ተጠሪ ከቀድሞ ሚስቱ የተወለዱ ልጆቹን ንብረት ለማሳጣት የተደረገው የጋብቻ ውል አመልካቾችን በእጅጉ ስለሚጎዳ መጽደቁ ተገቢ አለመሆኑን ፤ የጋብቻ ውሉ ከአፃፃፍ ፤ ከፎርም እና የሚቹ ችሎታ በሚመለከትም ውሉ ዋጋ አልባ ነው የሚሉበትን ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሉ እንዳይፀና ጠይቀዋል። በተጨማሪም ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጠ የተባለው የኑዛዜ ሥጦታም አስቀድሞ ንብረቱ ከአመልካቾች ስምምነት ውጪ እንዳይተላለፍ የሚለውን ውሳኔ የሚቃረን በመሆኑ ኑዛዜው ሕገ ወጥ ነው እንዲባል ጠይቀዋል።

ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን የታለፈ ሲሆን በፍሬ ነገር መልሳቸው፡- የአመልካቾች እናት ሚያዝያ 29 ቀን 1976 ዓ/ም ከተለዩ በኋላ ሚቹ ሐምሌ 26 ቀን 1977 ዓ/ም ተጠሪን አግብተው የንግድ ሥራው ሙሉ በሙሉ በሚባል በተጠሪ ኃላፊነት ሲሰራ ቆይቶ ሚች አስቀድሞ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት ተሰርቶ የነበረው የንግድ እና መኖሪያ ቤት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ፈርሶ በተጠሪ ጉልበትና ላብ እንደገና መሰራቱን ፤ በመንግስት የተወረሱ ሶስት ክፍል ቤቶች በተጠሪ ጥረት መመለሳቸውን

፣ ተጨማሪ 19 ክፍል በርጎዎች የተሰሩ በመሆኑና ሌሎች በአዲስ መልክ ተሠሩ የሚሉትና ዕድሳቶችን በመዘርዘር ሟቹ ይህንን የተጠሪን ትጋት ግምት ውስጥ በማስገባት የራሳቸውን ንብረት ድርሻ በስጦታ ለተጠሪ ያስተላለፉ መሆኑን ፤ ሟች እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ የተስማሙት የአመልካቾች እናት ድርሻ እንጅ በራሳቸው ድርሻ ላይ አለመሆኑን ፣ ድርሻቸውን ላለመሸጥ ስምምነት ቢያደርጉም እንኳን የሲቪል መብታቸውን ለመተው ያደረገሁት ስምምነት በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 195 ድንጋጌ መሠረት ዋጋ የሌለው መሆኑን ፤ ንግድ ቤቱም ሆነ መኖሪያ ቤቱ በሟች እና ተጠሪ ጋብቻ ውስጥ በአዲስ መልክ የተሠራ የጋራ ንብረት በመሆኑ ሟች ድርሻቸውን ለተጠሪ በጋብቻ ውል ማስተላለፋቸው አግባብ መሆኑን ፣ በተሻሻለው የጋብቻ ውል መሠረት ቤቱም ሆነ መኪናው የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑን ፤ የተሸሻለው የጋብቻ ውልም ለቤተሰብ ጥቅም መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ በመሆኑ ፣ ሟች ውሉን ሲያደርጉ በመልካም ጤንነት ላይ የነበሩ መሆኑ ፣ ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ/ም የተደረገው የስጦታ ውል መቃወሚያ ከቀረበበት የተሸሻለው የጋብቻ ውል ጋር ተያያዥነት የሌለው መሆኑንና በተሻሻለው የጋብቻ ውል የተተካ በመሆኑ አቤቱታው ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑን ገልፃው በዝርዝር ያቀረቡት መከራከሪያ ታይቶ ተቃውሞ የቀረበበት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት ለክርክሩ እልባት ለመስጠት ያስችለኛል ያለውን ጭብጥ ይዞ የግራቀኙ ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡ እንደመረመረው፡- ነሃሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም ተደርጎ መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ/ም በፍርድ ቤት የፀደቀው የተሻሻለው የጋብቻ ውል ይዘት የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 02-011 A 43288 ቶዮታ የቤት አውቶሞቢል በተጠሪ የግል ገንዘብ የተገዛ የግል ንብረቷ መሆኑንና የአቶ ማዴቦ ሀይዴቦ እና ተጠሪ የጋራ ንብረት የሆነው በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ቀበሌ 750 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኙት የመኖሪያና ንግድ ቤቶች ሟች ድርሻውን ለተጠሪ ሙሉ በሙሉ የለቀቀ መሆኑን የሚገልጽ መሆኑን ፤ ይህ 750 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው የመኖሪያና የድርጅት ቤት ሟቹ ከአመልካቾች እናት ጋር ያፈሩት የጋራ ሀብት ከመቃወሚያ አመልካቾች ስምምነት ውጭ ሟች አቶ ማዴቦ ሀይዴቦ እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ በስጦታም እንዳይሰጡ በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111/85 ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠ የፀና ውሳኔ እያለ ንብረቱ ሳይከፋፈልና ሳይነጣጠል የሟች ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ የአመልካቾች እናት ድርሻን እንኳን ከግምት ሳያስገባ ሟች የአመልካቾች አባት አጠቃለይ ንብረቱን ለተጠሪ በመስጠት የተደረገው የጋብቻ ማሻሻያ ውል በመዝገብ ቁጥር 111/85 ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚፃረር ፣ የጋብቻ ማሻሻያው ለቤተሰብ ጥቅም የተደረገ ለመሆኑ አመልካቾች ሃሳባቸውን ባልሰጡበት ውሉ ለቤተሰብ ጥቅም የተደረገ መሆኑ አለመረጋገጡን ፣ ሟች ውሉን ሲያደርጉ በተለያዩ በሽታዎች ተይዘው በህመም ሲሰቃዩና በእርጅና ጃጅተው እያሉ የተደረገ መሆኑ በአመልካቾች የሰውና የሰነድ ማስረጃ በተሸለ መልኩ ተረጋግጧል በማለት አጽድቆ የነበረውን የጋብቻ ማሻሻያ ውል በመሰረዝ ወስኗል፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ጉዳዩን ያየው የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሟቹ በሕጋዊ መንገድ እማኞች ባሉበት የእድሜም ሆነ የጤና ችግር እንደሌለባቸው በዳኛ ተጣርቶ በራሳቸው 50 % ድርሻ ብቻ ላይ በፍርድ ቤት ቀርበው ያደረጉት የተሻሻለው የጋብቻ ውል

ሊፈርስ አይገባም በማለት የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳሽ ምድብ ችሎት ውሳኔን ሽሯል፡፡

አመልካቾች የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሚች አቶ ማደቦ ሀይዴቦ እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ በስጦታም እንዳይሰጡ የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111/85 የሰጠው ውሳኔ አጠቃላይ ንብረቱን እንጅ 50 % የሚቹን ድርሻ ባለመሆኑ ፤ የሚቻ የአመልካቾች እናት ድርሻን አስቀርቶ የሌላ 3ኛ ወገን መብት ሳይነካ የመጠቀም ፣ ለሌላ ሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ያለው በመሆኑና ሚቹ የሚያደርገውን እያወቀና በነፃ አእምሮ ውሉን ማድረጉ ተረጋግጦ ፣ ሚቹ ውሉን ያደረገው ለቤተሰብ ጥቅም መሆኑን በጽሁፍ ከመግለጹም በላይ በአካል አስረድቶ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ ሰበር ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሚች አቶ ማደቦ ሀይዴቦ የአመልካቾች እናት ድርሻን ጨምሮ የገቡት ውል ፈርሶ የአመልካቾች እናት ድርሻ እንዳይሸጥ ፣ እንዳይለወጥ ፣ በስጦታም እንዳይተላለፍ የተሰጠ ትዕዛዝ መሆኑን ግራቀኙ ያልተካካዱ በመሆኑ ሚች አሻሽለው የገቡት ውል በፊት ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የሚጋጭ ባለመሆኑና የአመልካቾች ክርክርም የእናታቸውን ድርሻ አሳልፎ ሰጥቷል የሚል ባለመሆኑ ሚች የራሱን ድርሻ ብቻ አሳልፎ መስጠቱ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመበት አይደለም በማለት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካቾች የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በየደረጃው ያሉት ጉዳዩን ያዩት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም ያቀረቡት አቤቱቱ ይዘት በአጭሩ፡- በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ቀበሌ 750 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኙት የመኖሪያና ንግድ ቤቶች ሚች አቶ ማደቦ ሀይዴቦ የአመልካቾች እናት ከሆኑት ከሚች ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ ጋር በጋራ የተፈራ ሆኖ ፤ አመልካቾች ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ውርስ ተጣርቶ በጋራ ተይዞ ያለ ንብረት ሚቹ አባታቸው ግማሽ ድርሻቸውን ለተጠሪ ለማስተላለፍ አድርገውት የነበረውን የሥጦታ ውል የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111/85 ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመሻር ከአመልካቾች ስምምነት ውጪ ጠቅላላ ንብረቱን ሚቹ እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ በስጦታም እንዳይሰጡ የሰጠው የፀና ውሳኔ እያለ ሚች ድርሻውን ሊያስተላልፍ ይችላል መባሉ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38041 እና ሌሎች መዛግብት ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚፃር በመሆኑ ሊታረም የሚገባ መሆኑን ፣ ሚች የጋብቻ ማሻሻያ ውሉን በጤነኛ አዕምሮ ወደ ፊቅዶ ያላደረገው መሆኑ በአመልካች ምስክሮች የተረጋገጠው ፍሬ ነገርታልፎ የተወሰነ ከመሆኑም በላይ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ መሆኑን ፤ የጋብቻ ማሻሻያ ውሉ የቤተሰብ ጥቅምን የጎዳ ሆኖእያለ ውሉ ሊፀና ይገባል መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት ውሳኔ ፀንቶ የቀሪዎቹ በየደረጃው ያሉት ጉዳዩን ያዩት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በክርክሩ የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆላቸው ውሳኔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡

ከሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት ውሳኔ ውጪ ያለው የቀሪዎቹ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በየደረጃው ያሉ ጉዳዩን ያዩት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ የአመልካቾች አባት ነሓሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም አድርጎታል የተባለው የጋብቻ ማሻሻያ ውል ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በሥር የሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01940 ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር አግባብነቱ መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- ሟቹ በ1985 ዓ/ም ፣ በ2005 ዓ/ም እና 2011 ዓ/ም በንብረቱ መፈራትም ሆነ ለሟቹ በህይወት መቆየት ያደረጉትን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የንብረት ድርሻቸውን ለተጠሪ መተዋቸው አመልካቾች ሟቹ በተጽኖ ሥር ሆነው ነው የተሻሻለውን የጋብቻ ውል ያደረጉት የሚለውን የአመልካቾችን ክርክር ዋጋ የሚያሳጠ መሆኑንና ሟቹ ንብረቱ ለተጠሪ ለመስጠት ከመነሻው ያላቸውን ፍላጎት የሚያመለክት መሆኑን ፣ በ1985 ዓ/ም ሟች እንዳይሸጡ እና እንዳይለውጡ በፍርድ ቤት እገዳ የተጣለባቸው የሟቿ የአመልካቾች እናት ድርሻን እንጅ አቶ ማዴቦ ሀይዴቦን ድርሻን አለመሆኑን ፣ አሁን ያለው ንብረት ከበፊቱ በእጅጉ የተለየና በሟቹና በተጠሪ ስም የሚገኝ መሆኑን እንዳይሸጡ ፣ እንዳይለውጡ የሚለው በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 195 መሠረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ በፍርድ ቤት የፀደቀው የተሻሻለው የጋብቻ ውል ሊያስለውጥ የሚችል ምክንያት አለመኖሩን ፣ የተጠሪ ምክሮች በተጠሪ የቀረበውን ክርክር በሚገባ ያስረዱ ስለሆነ ከማስረጃ ምዘና አንፃርም የተፈፀመ ስህተት በለመኖሩና ማስረጃ መመዘን የሰበር ሰሚ ችሎቱ ሥልጣን ባለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን ፣ የተሻሻለው የጋብቻ ውል ለቤተሰብ ጥቅም የተደረገ መሆኑ ተረጋግጦ የፀደቀ በመሆኑ ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ፀንቶ ተጠሪ ለክርክሩ ያወጡትን ወጪ አመልካቾች እንዲተኩ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም በተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ በሰበር አቤቱታቸው ላይ የተጠቀሱትን የሕግ ስህተቶች የሚመለከት ሳይሆን በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ ያተኮረ ነው በማለት የሰበር አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ሟች አቶ ማዴቦ ሀይዴቦ የአመልካቾች እናት ከሆኑት ከሟች ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ ጋር በጋራ በተፈራ ፤ አመልካቾች ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ውርስ ተጣርቶ ከሟቹ ጋር የጋራ ባለሀብት ሆኑበትን ንብረት ከአመልካቾች ፈቃድ ውጪ ነሃሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም ተደርጎ መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ/ም በፍርድ ቤት በፀደቀው የተሻሻለው የጋብቻ ውል ለተጠሪ የማስተላለፋቸውን አግባብነት ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1266 እና ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እንዲሁም የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111/85 ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት ከሰጠው ውሳኔ አንፃር የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስመጣት ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የንብረት መብት ለዜጎች የተከበረ መሰረታዊ መብት ሆኖ ንብረትን የመያዝ ፣ በንብረቱ የመጠቀም ፣ የሌሎች ዜጎችን መብት እስካልተቃረነ ድረስ ንብረቱን የመሸጥ የማውረስ እና በሌላ መንገድ ማስተላለፍን

የሚያካትት ሆኖ ይህ መብት ***በሕግ ልገደብ የሚችል*** መሆኑን የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 40(1) ይደነግጋል። የባለሃብትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት ሆኖ በሕግ ከተቀመጠው ሥርዓት ውጪ ልገድብ የማይችል መሆኑንና የመብቱ ይዘት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1204 እና 1205 ሥር ተመላክቷል። ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች የሚተላለፍ ሲሆን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሀብትነት ስተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 ያስገነዝበናል። በዚህ መልክ ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል።

የአንድ ንብረት ባለሀብትነት የብዙ ሰዎች ሊሆን እንደሚችል ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1257 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የጋራ ባለሀብትነት በፍትሐ ብሔር ሕጉ ትርጉም አልተሰጠው። co-ownership (joint ownership is asituation where a single object of ownership (movable or immovable) right is made to fall under two or more individual. In such a situation though the right of ownership is divided the object of ownership remains undivided. In the case of co-ownes the title of the one is rendered consistent with that of the other by the *existence of reciprocal obligation of restricted use and enjoyment.* የጋራ ባለሀብትነት በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1257 — 1308 ድንጋጌዎች የሚመራ ሲሆን ፤ እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በቁጥር 1260(1) መሠረት ድርሻውን ለመሸጥ ፣ ለማስተላለፍ ፣ ለመያዝ እንዲሁም ከሌሎች የጋራ ባለሀብቶች ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ መጠቀም(መገልገል) እንደሚችል ቁጥር 1263 የሚደነግግ ቢሆንም ፤ የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ ፣ ለማስተላለፍ ወይንም ዋስትና ለማስያዝ ወይንም የተመደበለትን አገልግሎት ለመለወጥ ስሆን ***የጋራ ባለንብረቶቹ ስምምነት አስፈራጊ*** መሆኑን ቁጥር 1266 የሚያመለክት ሲሆን ፤ የጋራ ባለሀብቶች ያልተካፈለውን የጋራ ንብረት ከሌሎች 3ኛ ወገኖች በቅድሚያ የማስቀረት መብት ያላቸው መሆኑን የቁጥር 1261 ድንጋጌ ያመለክታል። ውል ለመመስረት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ የስምምነት መኖር መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1678(ሀ) የሚያመለክት በመሆኑ የሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ፈቃድ ሳይኖር እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በቁጥር 1260(1) መሠረት ድርሻውን ለመሸጥ ፣ ለማስተላለፍ ፣ ስለማይችል *የጋራ ባለንብረቶቹ ስምምነት* ሳይኖር የሚያደረገው ስምምነት ፈራሽ ነው።

በተያዘው ጉዳይ ሟች አቶ ማደቦ ሀይዴቦ ነሃሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም ተደርጎ መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ/ም በፍርድ ቤት የፀደቀው የተሻሻለው የጋብቻ ውል ሙሉ መመሉ ለተጠሪ ያስተላለፉት ንብረት የአመልካቾች አባት አቶ ማደቦ ሀይዴቦ ከሟች የአመልካቾች ወላጅ እናት ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ ጋር በትዳር እያሉ የተፈራ መሆኑ ፤ አመልካቾች የእናታቸው ወራሽነት በማረጋገጥ የውርስ ሃበት ተጣርቶ ሟች እና አመልካቾች በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 1257 የጋራ ባለሀብት የሆኑበት ንብረት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከመረጋገጡም በላይ ፤ የአመልካቾች የውርስ ድርሻ ሳይለይ የጋራ የሆነውን ንብረት ሟች አቶ ማደቦ ሀይዴቦ በስጦታ ማሰተላለፋቸው አግባብ አይደለም ተብሎ ሟቹ ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ ፈርሶ ንብረቱ ከአመልካቾች ፈቃድ ውጭ እንዳይሸጡ ፤ እንዳይለውጡና በስጦታ እንዳያስተላልፉ የሀዋሳ ዙሪ ወረዳ ፍርድ

ቤት በመዝገብ ቁጥር 111/85 ላይ ሰኔ 21 ቀን 1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስቀድሞ ውሳኔ መስጠቱን ችሎቱ ከሥር ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ካስመጣው መዝገብ ግንዛቤ ወስዷል። ተጠሪ የተሻሻለው የጋብቻ ውል መፍረስ የለበትም የሚሉበት ዋናው ምክንያት ሟች አቶ ማዴቦ ሀይዴቦ በተሻሻለው የጋብቻ ውል ያስተላለፉት ድርሻቸውን እንጅ የአመልካቾች ወላጅ እናት ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ ድርሻን የማይጨምር በመሆኑ በድርሻው ላይ ገደብ ሊኖር አይገባም በሚል እንጅ የሟቹ ድርሻ በክፍፍል ተለይቶ ታውቆ የግል ንብረታቸውን አስተላልፏል በሚል አይደለም። የሥር ፍርድ ቤቶችም ሟቹ በንብረቱ ላይ የጋራ ባለሀብት በመሆኑ ድርሻውን የማስተላለፍ መብት አለው በማለት ሲወስኑ የጋራ የሆነው ንብረት በጋራ ባለሀብቶች መካከል ከፍፍል ተደርጎ የሟች ድርሻ ተለይቶ የግሉ የሆነውን ንብረት አስተላልፏል በሚል ካለመሆኑን በላይ ከጋራ ንብረቱ ድርሻውን ያስተላለፈው የአመልካቾች ስምምነት መኖሩ ተረጋግጧል በሚል አይደለም።

ሲጠቃለል ያለአመልካቾች ፈቃድ ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ በህግ የተከለከለውንና የህግ ክልከላውን መሠረት አድርጎ አስቀድሞ የተሰጠ የፀና ውሳኔ እያለ ሟች ደርሻውን በተሸሻለው የጋብቻ ውል ማስተላለፉ አግባብ ነው በማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት እና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፤ እንዲሁም የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1266 ፣ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 212 ድንጋጌዎችንና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል።።

ውሳኔ

1. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01553 ህዳር 1 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 00896 ሰኔ 25 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ ፤ እንዲሁም የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29868 መጋቢት 9 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ተሽሯል***።
2. የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የባህል አዳራሽ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01940 ታህሳስ 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምጽ ***ፀንቷል***
3. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ።
4. በዚህ መዝገብ ላይ ታህሳስ 25 ቀን 2014 ዓ/ም የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል።
5. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኋን ወደ መጣበት ይለመስ ተብሏል።
6. ውሳኔው ግንቦት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በችሎት ተነቧል።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሠ/ኃ

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው በአሁን ተጠሪ ወ/ሮ ውዴ ኡመር እና ባለቤታቸው በሚች አቶ ማዴቦ አይዴቦ መካከል በ29/12/2011 ዓ/ም በሀዋሳ ከተማ ባህል አደራሽ ክ/ከተማ አዳሬ ቀበሌ ክልል በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤትና ንግድ ቤት እና የቤት መኪና የሰሌዳ ቁጥር2-A43288 አአ ላይ ያደረጉት የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በተመለከተ ነው፡፡ በ29/12/2011 ዓ/ም በሁለቱ መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01940 መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት ቀርቦ ጸድቋል፡፡ የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ፣ ይህ በ29/12/2011 ዓ/ም የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል፣ ሚች አባታችን አቶ ማዴቦ አይዴቦ ከሚች እናታችን ወ/ሮ በላይነሽ መርፎ በውርስ ያገኘነውን የጋራ ንብረታችን በሆነው በሀዋሳ ከተማ ባህል አደራሽ ክ/ከተማ አዳሬ ቀበሌ ክልል በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤትና ንግድ ቤት እና የቤት መኪና የሰሌዳ ቁጥር 2-A43288 አአ ላይ ያደረጉት የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል ህግ፣ ውሳኔ እና ከሞራል ተቃራኒ ሆኖ የተደረገ ውል በመሆኑ ይሻርልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ይሄውም ሚች አባታችን ይህን ቤት ከኛ አመልካቾች ስምምነት ውጪ መሸጥ ማስተላለፍ እንደማይችል በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም ትእዛዝ ሰጥቶ እያለ፣ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውላቸው የኛን የቤተሰብ ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ እያለ፣ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውሉ ሁለት ሁለት ምስክሮች ባሉበት ያልተደረገ እና በሷ ወገን ብቻ በቀረቡ ምስክሮች የተደረገ ሆኖ እያለ ሚች አባታችን እድሜው 100 የሞላውና በህመም ላይ እያለ እራሱን በማያውቅ ሁኔታ የተደረገ ውል በመሆኑ በውሉ ላይ ያለው ፊርማ በጣት አሻራ በመሆኑ የሚች አባታችን ፊርማ ባለመሆኑ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ እና የፍርድ ቤት ውሳኔ በመጣስ የተደረገ የጋብቻ መሻሻያ ውል በመሆኑ እና ፍ/ቤቱም ተቀብሎ ማጽደቁ ተገብ ባለመሆኑ የሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ከሚች ባለቤቴ አቶ ማዴቦ አይዴቦ ጋር በ29/12/2011 ዓ/ም በሀዋሳ ከተማ ባህል አደራሽ ክ/ከተማ አዳሬ ቀበሌ ክልል በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤትና ንግድ ቤት ላይ ያደረግነው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል አዲስ ሳይሆን በ1985 ዓ/ም በ2005 ዓ/ም እና አሁን በ2011 ዓ/ም የተደረገ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመሆኑ እና ቀድሞም ለ27 ዓመት ያክል የነበረውን ነጻ ፍላጎቱንና ፈቃዱን በድጋሚ በ29/12/2011 ዓ/ም የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል አደረግን እንጂ እንደ አዲስ ጫና ተፈጥሮበታል፣ እድሜው ገፍቷል እና የጤና እክል አለበት በሚል መከራከሪያ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ ይህ ለመሆኑ የአሁን አመልካቾችም ከ1985 ዓ/ም ጀምሮ የሚያውቁት ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ትእዛዝ ጠቅላላ ንብረቱን ማለት የአሁን አመልካቾች ከእናታቸው የወረሱትን ንብረት ጨምሮ ለመሸጥ ለማስተላለፍ የአሁን አመልካቾችን ስምምነት መጠየቅ አንዳለበት የሚገልጽ እንጂ የራሱን ድርሻ ለመሸጥ ለማስተላለፍ የሚከለክለው ትእዛዝ አይደለም፡፡ ነው ቢባል እንኳ የንብረት ማፍራት ህገ መንግስታዊ መብቱን የሚጋፋ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የቤተሰብ ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን በፍ/ቤት ተረጋግጦ የጸደቀ በመሆኑ፣ ሁለት ሁለት ምስክሮች ባሉበት የተደረገ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመሆኑ፣ እድሜው በ84 ዓመቱ ጤነኛ እና መንቀሳቀስ በሚችል ሁኔታ ፍ/ቤት ቀርቦ በፍ/ቤት ተረጋግጦ የጸደቀ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመሆኑ የሚፈርመውም በጣት አሻራ አንደሆነ ተከራክራለች፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ እና በሚች ማዴቦ አይደቦ መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል ቀደም ብሎ የመጀመሪያ ደረጃ በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ የሚቃረን ነው፡፡ ሚች አቶ ማዴቦ አይደቦ ነሐሴ 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በደፊናው ለቤተሰብ ጥቅም

ተደርጓል መባሉና እድሜው 100 ዓመት ከሞላውና በጤንነት ችግር እራሱን በማያውቅበት ሁኔታ የተደረገ ውል በመሆኑና በፍ/ቤቱም መጽደቁ ተገቢ ባለመሆኑ ተሽሯል ሲል ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበረ ሰሚ ችሎት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጡት ውሳኔ ደግሞ ቀደም ብሎ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ሚች በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት ካለ አሁን ተጠሪዎች ስምምነት ጠቅላላውን የአሁን ተጠሪዎችን ድርሻ ጨምሮ እንዳይሸጥ እንዳያስተላልፍ የሚል በመሆኑ የራሱን ድርሻ ለማስተላለፍ የሚከለክለው አይደለም፡፡ በሚች እና የአሁን ተጠሪ መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውሉም ከሚች እና ከአሁን ተጠሪ ጋር በቤተሰብ አባልነት የሚኖር ልጅ ባለመኖሩ የቤተሰብ ጥቅም የሚጎዳ አይደለም፡፡ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውሉ ሁለት ሁለት የግራ ቀኙ ምስክሮች በተገኙበት፣ ምስክሮቹም ሚችም በውሉ ላይ የፊረሙ ስለመሆኑ ተረጋግጦ፣ በ84 ዓመት እድሜው በጤነኛ አእምሮ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ ይህንኑ አረጋግጦ ነጻ ፍላጎቱንና ፍቃዱን ጠይቆ ውሉን ያጸደቀው መሆኑ በቀረቡት ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በ29/12/2011 ዓ/ም በሚችና የአሁን ተጠሪ መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውሉ እና ይህን ውል ያጸደቀው የፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር አይገባም ሲሉ ወስነዋል፡፡ የአሁን አመልካቾችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡

የአሁን ተጠሪና ሚች አቶ ማዴቦ አይዴቦ ከ27 ዓመት በላይ በጋብቻ መቆየታቸው ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሳኔ በሚች እና የአሁን ተጠሪ መካከል በ29/12/2011 ዓ/ም የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል የሚች አቶ ማዴቦ አይዴቦ እድሜ ሁኔታ፣ ፊርማ እና ምስክሮች እና በነጻ ፍላጎቱ እና ፍቃዱ ያደረው ውል ስለመሆን አለመሆኑን በተመለከተ ሚች ከ1985 ዓ/ም ጀምሮ ለ3ኛ ጊዜ የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል እያደረገ የቆየ መሆኑ ሲታይ በ29/12/2011 ዓ/ም ያደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በአዲስ ያልመጣ፣ በስተእርጅና እና የጤና ችግር ባለበት ጊዜ በጫና የተደረገ ነው ሊያስብል የማያስችል ነው፡፡ ቀድሞም የነበረውን ፍቃድና ነጻ ፍላጎቱን በ29/12/2011 ዓ/ም ውል ማድረጉን የሚያረጋግጥ በመሆኑ በአዲስ ጫና ተደርጎበታል የሚል ክርክር ተቀባይነት ያለው አይሆነም፡፡ እንዲሁም እድሜ ሁኔታ፣ የሚች ፊርማ፣ ምስክሮች እና በነጻ ፍላጎቱ እና ፍቃዱ ያደረው ውል ስለመሆን አለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በቀረበው የሰነድና የሰው ማስረጃ ተረጋግጦ የተወሰነ ጉዳይ በመሆኑ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ልቀርብ የሚችልም አይደለም፡፡

የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ሚች አቶ ማዴቦ አይዴቦ በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት ካለ አሁን ተጠሪዎች ስምምነት ጠቅላላውን የአሁን አመልካቾች ድርሻ ጨምሮ እንዳይሸጥ እንዳያስተላልፍ የሚል ነው፡፡ ይህ በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከእናታቸው የወረሱት ድርሻ ስላለበት ሚች ጠቅላላውን የአሁን አመልካቾችን ድርሻ ጨምሮ ለመሸጥ ለማስተላለፍ የአሁን አመልካቾችን ስምምነት ጠይቅ ተብሎ መታዘዙ ህጉም የሚለው በመሆኑ የተለየ ግዴታ አይደለም፡፡ ትእዛዙም ድርሻህን ለማስተላለፍ የአሁን አመልካቾችን ፈቃድ ወይም ስምምነት ጠይቅ የሚል አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1266 የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አግልግሎት ለመለወጥ ሲሆን የጋራ ባለንብረቶቹን ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የጋራ ንብረቱን (ጠቅላላውን) ለመሸጥ ለማስተላለፍ እንደሆነ የሌላውን የጋራ ባለሀብት ስምምነት መጠየቅ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሚች በራሱ ድርሻ ላይ ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመ/ቁጥር 111/85 በ21/10/1985 ዓ/ም የተሰጠውን ትእዛዝ የሚቃረን አይደለም፡፡ እንዲሁም በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት ከሚች ድርሻ ወደ የአሁን ተጠሪ መተላለፉ የጋራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ንብረትነቱ የግድ በአባታችን መቆየት አለበት የሚል ክርክር ካልሆነ በቀር የጋራ ቤትነቱን ወይም ንብረትነቱን የሚያሳጣውም አይደለም፡፡ አንድ ባለንብረት ንብረቱን የመጠቀም የመሸጥ የማስተላለፍ ህገ መንግስታዊ መብት አለው፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፡፡ ይህ መብት የህዝብ ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረቱ የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶች እንዳሉት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በግል ንብረቱ ላይ የሚያደርገው ውል መብት እንጂ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም፡፡ ይህ ጉዳይ የባልና ሚስት የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውል በመሆኑም የሚዳኘው በቤተሰብ ህጉ እንጂ የኑዛዜ ጉዳይ የሚመለከት አይደለም፡፡ የኑዛዜ ጉዳይ ባለመሆኑም ውሉ ከወራሽነት ነቅሎናል የሚል ክርክርም አይነሳም፡፡ ሌላው የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1260(1) እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት የራሱን ድርሻ ለመሸጥ ለማስተላለፍ ለማስያዝ ይችላል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጋራ ባለሀብት የራሱን ድርሻ ለማስተላለፍ የሚከለከልም አይደለም፡፡ የሌላውን የጋራ ባለሀብት ፈቃድም የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ሌላው የጋራ ባለሀብት ያለው መብት ንብረቱ የሚሸጥ ከሆነ የቅድሚያ መብት ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1261(2) ይህ በቀደምትነት የማስቀረት መብት በስራ ላይ ስለሚውልበት አኳኋን በዚህ አንቀጽ በምዕራፍ 4 በተነገረው ድንጋጌ ውስጥ የተመለከተው ደንብ ጸንቶ እንደሚሰራ ይገልጻል፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1388 በቀዳሚነት ግዥ ይገባኛል የማለት መብት ከጋራው ንብረት ውስጥ ለሚሸጠው አንድ ክፍል ለጋራ ባለሀብቶቹ በህግ መሰረት አላቸው ሲል ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ይህ ያከራከረው በ750 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት ሟች የሸጠው ባለመሆኑ የቀደምትነት መብትም የሚነሳ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሌላው የቤተሰብ ጥቅም በተመለከተ የደቡብ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 56 ትርጉም እና የቤተሰብ ህጉ ዓላማ አንጻር የአሁን አመልካቾች እራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ከአሁን ተጠሪ እና ከሟች ባለቤቷ ጋር የማይኖሩ መሆኑ እና በሁለቱ መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውሉ የቤተሰብ ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ ተረጋግጦ የጸደቀ እና አሁንም በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክርም የጸደቀው ውል የቤተሰብ ጥቅም እንደማይጎዳ ተረጋግጦ ሊሻር አይገባም በሚል ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን አመልካቾችም ጥቅማችንን ይጎዳል የሚሉት የአባታችንን ንብረት እንዳንወርስ ያደርገናል የሚል የውርስ ንብረት ጥያቄ አይነት ክርክር በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ደግሞ የባልና ሚስት የጋብቻ ውል ማሻሻያ ውልን በተመለከተ የሚደረግ ክርክር በመሆኑ በተገቢው ቦታ የተነሳ ክርክር የሚሆን አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ሲገባ በቂ ባልሆነ ምክንያት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ካለአግባብ በመሆኑ የተለየ ሀሳቤን አስቀምጫለሁለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ.መ.ቁ 217195
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍርኑስ ፈንቴ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የደብረማዊ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት -- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩን የማየት የሥረ -ነገር ስልጣን የላቸውም በሚል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳየ የሥረ-ነገር ስልጣን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በቀን ሕዳር 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የክስ አቤቱታ በይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የነበራቸውን መሬት ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ ቦታ ሳይሰጥና በቀሪው ይዞታ ላይ ካሳ ሳይከፈላቸው ተጠሪ ይዞታውን ለሌሎች ግለሰቦች የሰጠባቸው በመሆኑ ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ እንዲሰጣቸው፣ በቀሪው ይዞታ ደግሞ ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ተጠሪ ታሕሳስ 5/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገር መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የካሳ ጥያቄ የሚያቀርቡት በአስተዳደራዊ መንገድ ሆኖ በይግባኝ በከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑን፣ ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት ክስ እንዲያቀርቡ የወሰነላቸው የቦታ ጥያቄ እንጅ የካሳ ጉዳይ ጭምር አለመሆኑን፣ ለአመልካች እና ለ1ኛ ልጃቸው 750 ካ.ሜ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ሌሎቹ ልጆች ግን መስፈርቱን የማያሟሉ መሆኑን፣ ቀሪውን ይዞታ ተጠሪ የማይፈልገው መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች በማቅረብ የሰማ ሲሆን አመልካች 500 ካ.ሜ፣ 1ኛው የአመልካች ልጅ 250 ካ.ሜ ይዞታ ያገኙ መሆኑን ቀሪ ልጆች መመሪያ ቁጥር 26/2008 ን መስፈርት ማለትም በወቅቱ ከአመልካች ጋር በስፍራው የማይኖሩ በመሆኑ ምክንያት መሬት ያልተሰጣቸው መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል በሚል አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ያልተቀበለው ሲሆን፣ ካሳን በተመለከተ አመልካች ካሳ ያልወሰደች መሆኑ በተጠሪ የታመነና ተጠሪ ትውሰድ በማለት በችሎት የገለጸ በመሆኑ ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ከወሰደው መሬት ተመጣጣኝ ካሳ ለአመልካች እንዲሰጥ በሚል ወስኗል፡፡

በአመልካች በኩል ይግባኙ የቀረበለት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በትዕዛዝ ያጸናው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለህዝብ ጥቅም ለማዋል በሚወሰድ ንብረት አስመልክቶ የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የቀረበውን ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ሳይኖረው መወሰኑና ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ማረም ሲገባው ይግባኙን መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው በማለት የአመልካችን ሥልጣን ባለው አካል ክስ የማቅረብ መብቷን ጠብቆ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የስር ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍል በሰጠው ውሳኔ ላይ ክርክር ባልተነሳበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ ባሉበት መዝገብ አመልካችን በሚጎዳ መልኩ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የገጠር መሬት የሚነሳባቸው አርሶ አደሮች ቦታ አሰጣጥና ካሳ አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 36 እና የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንቀጽ 60 ላይ በተጠቀሰው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሰረት አመልካች ጉዳዩን ወደ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡበት አግባብ ተገቢ ሆኖ ሳለ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 በመጥቀስ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለጠየቁት ዳኝነት የወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም የመባሉን አግባብ አርሶ አደር ካሳ አከፋፈል እና ቦታ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 7/2010 እና

የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንጻር ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን መጋቢት 22/2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች ጉዳዩን ለስር ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡት መመሪያ ቁጥር 7/2010 ም ሆነ 44/2013 ከመውጣቱ በፊት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በወቅቱ በነበረው መመሪያ ቁጥር 26/2008 እና በአዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 11 እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 ላይ የተቀመጠውን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን፣ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች አግባብ ባለው አካል መብታቸውን የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት ወሰነ እንጅ አመልጃች ያቀረቡትን መብት በመመርምር ያሳጣቸው መብትም ሆነ የተጣለባቸው ግዴታ የሌለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ሊባል የማይችል መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ በቀረበው መልስ ላይ ሚያዚያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አመልካች ያቀረቡት የካሳ አነሰኝ ጉዳይ ሳይሆን ለአመልካችና ለ3 ልጆቻቸው ትክ መሬት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በመግለጽ ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ስልጣነ አለው በማለት ቀድመው ያቀረቡትን መከራከሪያ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ይዘት በግልጽ መገንዘብ የቻልነው ሕጋዊ መብታቸው ሳይጠበቅ የገጠር መሬታቸው የተወሰደባቸው መሆኑን በመግለጽ መብታቸው እንዲጠበቅ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም አመልካች በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ ክስ ያቀረቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52/2 ድንጋጌ ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት በገጠር መሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብት ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ በመሆኑ ከላይ በተገለጸው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክቶ የፍሬነገር ክርክሩን መርምሮ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ ድንጋጌን በመጥቀስ የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን

የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ. 217202
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ
ዐሐይ መንክር
ኑረዲን አድር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ብርሃን አለም ጠ/አለባቸው ጊዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ክልል
የቀጠና ሁለት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ----አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 122512 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 275468 ሕዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የጻፈው የዕግድ ደብዳቤ አመልካች በምፈልገው የእምነት ቦታ በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል አጥቢያ ውስጥ አምልኮ የማምለክ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መብቱን የሚጋፋ በመሆኑ በኢ.ፌ.ድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 27(3) መሰረት ፅግዱ ህገወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን መመዝን ውስጥ ገብቶ ይኸኛው አገልጋይ ይቀጥል ይኸኛው አይቀጥል ብሎ በፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠት ማለት ሶስተኛው ክንፍ የሆነው ፍርድ ቤት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃገብነት ማለት በመሆኑ፤ የግራ ቀኙ ጉዳይ ሀይማኖታዊ በሆነ ጉዳይ ተጠሪ የሆኑትን ቤተክርስቲያን በፍርድ ቤት ልትከሰስ እና ልትገደድ የሚገባ ባለመሆኑ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ ተጠሪ ልትከሰስ አይገባም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 231(1)(ሀ)ን መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል።

አመልካች ይህንኑ ብይን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተሰርሟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ትዕዛዝ ላይ ሲሆን አመልካች የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ብይን እና ውሣኔ በመቃወም ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ቤተክሰርስቲያን በአመልካች ላይ የፈጸመችውን ክልከላ የእምነት ነፃነት መብቱን የሚጋፋ እና ኢ-ህገመንግስታዊ ነው፤ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11ን የሚቃረን ነው፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከጠየቀው ዳኝነት ውጪ በራሱ አነሳሽነት የሰጠው ብይን ስህተት ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በቀረበባት ክስ ላይ መልስ ሳትሰጥበት አያስከስስም ማለቱ ተገቢ አይደለም፤ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ዳኝነት ጥያቄ የማምለክ መብቱ ይጠበቅልኝ የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤት የሚ,ታይ አይደልም በማለት የሰጠው ብይን አግባብነት ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 27 እና 37 አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠችው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ ከአባላቶቿ የኮሚቴ አባል የመምረጥ የመረጠችውን የመሻር መብት የቤተክርስቲያን የውስጥ ጉዳይ እንጂ በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ አይደለም፤ የአመልካች ክስ ከህገመንግስቱ አንቀጽ 13፣27(1) እና 37 ጋር ግንኙነት የለውም፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን መዘጋቱ ህግ እና ስርዓትን የተከተለ ነው፤በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ ከተመለከተውን ሲመለል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ከተሰጠው ብይን እና ተዕዛዝ እንዲሁም መዝገቡ ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማረናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ከላይ እንደተገለጸው የማምለክ ህገ መንግሥታዊ ነፃነቴን ተጠሪ አግዳብኖለች የሚል ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ሃይማኖታዊ ጉዳይ በመሆኑ በፍርድ ቤት ተጠሪ ልትከሰስ አይገባም በሚል ክሱን ውድቅ አድርጐታል።

ከአጠቃላይ ክርክሩ እና ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠችው የዕግድ ትዕዛዝ የሀይማኖት ነፃነትን የሚነካ መሆን አለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በአግባቡ ተመርምሮ ብይን የመሰጠቱን አግባብነት ከህገመግሥቱ አንቀጸ 11 እና 27 ድንጋጌዎች ጋር በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 11 መንግሥትና ሀይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፣ መንግሥታዊ ሀይማኖት ያለመኖሩን፣ መንግሥት በሀይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ ስለመሆኑ ይደነግጋል።

እንዲሁም በህገመንግስቱ የሀማይማኖት የእምነት እና የአመለካከት ነፃነትን የሚደነግገው አንቀጽ 27 የሚያመለክተው ማንም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሀይማኖት ነፃነት ያለው መሆኑን፣ የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል የማይቻል መሆኑን የሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብ ደህንነት ሰላምን ጤናን ትምህርትን የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶችን ነፃነቶች እና መንግሥት ከሀይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች እንደሆነ እና ሌሎችንም ደንግጐ እናገኛለን።

ከላይ ከተገለፁት የህገመንግሥቱ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ሰዎች የማምለክ ነፃነት ያላቸው መሆኑን፣ ይህ ነፃነታቸው ሊገደብ የሚችለው በህግ ብቻ መሆኑን እና መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በተጠሪ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ እንደሆኑ እና በዚህ የአገልግሎት ጊዜያቸው ውስጥ ቤተክርስቲያኗ ፈፀሙት ያለችውን ችግር በመዘርዘር ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. በተፃፈ ከአገልግሎት ያገደቻቸው መሆኑን ነው።

አንድ ቤተክስርቲያን በስሯ ያለውን አማኝ አገልጋይ ማድረግ እና ግለሰቡ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ችግር አግኝቼበታለሁ ስትል ደግሞ ከአገልግሎት የማገድ መብት የምታገኘው በቤተክርስቲያኗ በሚኖር ሥርዓት መሠረት ነው።

ከላይ የህገመንግሥቱ ድንጋጌዎች የሚያሳዩት በእምነት ተቋማት ውስጥ በሚፈጠር አለመግባባት መንግሥት ጣልቃ መግባት የማይችል መሆኑን የዚህ የቤተክርስቲያኒቱ አሰራር ሊፈተሽ የሚገባውም በዚሁ በእምነት ተቋም ውስጥ በተዘረጋው መስመር እንጂ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አምልኮትን በተመለከተ ህገመንግሥቱ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው በህግ እግድ ካልተጣለ በቀር ማንም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት የመከተል እና የማምለክ መብት ያለው በመሆኑ አመልካችም የዚህ መብት ተጠቃሚ ናቸው። ከተሰጠው እግድ ላይ የምንገነዘበውም አመልካች በተሰጠው እግድ መሰረት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የታገዱ መሆኑን ነው። ይህ የእግድ ትዕዛዝ ደግሞ በቤተክርስቲያኒቱ አጥቢያ ውስጥ የማምለክ ህገ መንግሥታዊ መብትን የሚነካ መሆኑን የእግዱ ትዕዛዝ ዝርዝር አያሳይም። የቀረበው ጉዳይም ቢሆንም አመልካች እንደሚሉት ከእምነት ነፃነት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሃይማኖት ተቋማት የውስጥ አሰራር ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት ይሆናል።

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ከተሰጠው የእግድ ትዕዘዝ አንፃር አመልካች ያቀረቡት ክስ በፍ/ቤት የሚስተናገድ አይደለም በሚል የደረሱበት ድምዳሜ ህግን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል።

<u>ውሣኔ</u>

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 275468 ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 122518 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል።
2) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።
3) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

መዝገቡ ውሣኔ ሰላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ.መ.ቁ. 217202
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ
ዐሐይ መንክር
ኑረዲን አድር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ብርሃን አለም ጠ/አለባቸው ጊዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- በኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ክልል
የቀጠና ሁለት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ----አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 122512 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 275468 ሕዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የጻፈው የዕግድ ደብዳቤ አመልካች በምፈልገው የእምነት ቦታ በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል አጥቢያ ውስጥ አምልኮ የማምለክ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መብቱን የሚጋፋ በመሆኑ በኢ.ፌ.ድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 27(3) መሰረት ፅግዱ ህገወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን መመዝን ውስጥ ገብቶ ይኸኛው አገልጋይ ይቀጥል ይኸኛው አይቀጥል ብሎ በፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠት ማለት ሶስተኛው ክንፍ የሆነው ፍርድ ቤት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃገብነት ማለት በመሆኑ፤ የግራ ቀኙ ጉዳይ ሀይማኖታዊ በሆነ ጉዳይ ተጠሪ የሆኑትን ቤተክርስቲያን በፍርድ ቤት ልትከሰስ እና ልትገደድ የሚገባ ባለመሆኑ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ ተጠሪ ልትከሰስ አይገባም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 231(1)(ሀ)ን መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል።

አመልካች ይህንኑ ብይን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተሰርሟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ትዕዛዝ ላይ ሲሆን አመልካች የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ብይን እና ውሣኔ በመቃወም ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ቤተክሰርስቲያን በአመልካች ላይ የፈጸመችውን ክልከላ የእምነት ነፃነት መብቱን የሚጋፋ እና ኢ-ህገመንግስታዊ ነው፤ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11ን የሚቃረን ነው፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከጠየቀው ዳኝነት ውጪ በራሱ አነሳሽነት የሰጠው ብይን ስህተት ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በቀረበባት ክስ ላይ መልስ ሳትሰጥበት አያስከስስም ማለቱ ተገቢ አይደለም፤ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ዳኝነት ጥያቄ የማምለክ መብቱ ይጠበቅልኝ የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤት የሚ,ታይ አይደልም በማለት የሰጠው ብይን አግባብነት ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 27 እና 37 አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠችው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ ከአባላቶቿ የኮሚቴ አባል የመምረጥ የመረጠችውን የመሻር መብት የቤተክርስቲያን የውስጥ ጉዳይ እንጂ በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ አይደለም፤ የአመልካች ክስ ከህገመንግስቱ አንቀጽ 13፣27(1) እና 37 ጋር ግንኙነት የለውም፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን መዘጋቱ ህግ እና ስርዓትን የተከተለ ነው፤በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ ከተመለከተውን ሲመለል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ከተሰጠው ብይን እና ተዕዛዝ እንዲሁም መዝገቡ ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማረናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ከላይ እንደተገለጸው የማምለክ ህገ መንግሥታዊ ነፃነቴን ተጠሪ አግዳብኖለች የሚል ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ሃይማኖታዊ ጉዳይ በመሆኑ በፍርድ ቤት ተጠሪ ልትከሰስ አይገባም በሚል ክሱን ውድቅ አድርጐታል።

ከአጠቃላይ ክርክሩ እና ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠችው የዕግድ ትዕዛዝ የሀይማኖት ነፃነትን የሚነካ መሆን አለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በአግባቡ ተመርምሮ ብይን የመሰጠቱን አግባብነት ከህገመግሥቱ አንቀጸ 11 እና 27 ድንጋጌዎች ጋር በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 11 መንግሥትና ሀይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፣ መንግሥታዊ ሀይማኖት ያለመኖሩን፣ መንግሥት በሀይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ ስለመሆኑ ይደነግጋል።

እንዲሁም በህገመንግስቱ የሀማይማኖት የእምነት እና የአመለካከት ነፃነትን የሚደነግገው አንቀጽ 27 የሚያመለክተው ማንም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሀይማኖት ነፃነት ያለው መሆኑን፣ የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል የማይቻል መሆኑን የሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብ ደህንነት ሰላምን ጤናን ትምህርትን የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶችን ነፃነቶች እና መንግሥት ከሀይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች እንደሆነ እና ሌሎችንም ደንግጐ እናገኛለን።

ከላይ ከተገለፁት የህገመንግሥቱ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ሰዎች የማምለክ ነፃነት ያላቸው መሆኑን፣ ይህ ነፃነታቸው ሊገደብ የሚችለው በህግ ብቻ መሆኑን እና መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በተጠሪ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ እንደሆኑ እና በዚህ የአገልግሎት ጊዜያቸው ውስጥ ቤተክርስቲያኗ ፈፀሙት ያለችውን ችግር በመዘርዘር ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. በተፃፈ ከአገልግሎት ያገደቻቸው መሆኑን ነው።

አንድ ቤተክስርቲያን በስሯ ያለውን አማኝ አገልጋይ ማድረግ እና ግለሰቡ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ችግር አግኝቼበታለሁ ስትል ደግሞ ከአገልግሎት የማገድ መብት የምታገኘው በቤተክርስቲያኗ በሚኖር ሥርዓት መሠረት ነው።

ከላይ የህገመንግሥቱ ድንጋጌዎች የሚያሳዩት በእምነት ተቋማት ውስጥ በሚፈጠር አለመግባባት መንግሥት ጣልቃ መግባት የማይችል መሆኑን የዚህ የቤተክርስቲያኒቱ አሰራር ሊፈተሽ የሚገባውም በዚሁ በእምነት ተቋም ውስጥ በተዘረጋው መስመር እንጂ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አምልኮትን በተመለከተ ህገመንግሥቱ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው በህግ እግድ ካልተጣለ በቀር ማንም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት የመከተል እና የማምለክ መብት ያለው በመሆኑ አመልካችም የዚህ መብት ተጠቃሚ ናቸው። ከተሰጠው እግድ ላይ የምንገነዘበውም አመልካች በተሰጠው እግድ መሰረት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የታገዱ መሆኑን ነው። ይህ የእግድ ትዕዛዝ ደግሞ በቤተክርስቲያኒቱ አጥቢያ ውስጥ የማምለክ ህገ መንግሥታዊ መብትን የሚነካ መሆኑን የእግዱ ትዕዛዝ ዝርዝር አያሳይም። የቀረበው ጉዳይም ቢሆንም አመልካች እንደሚሉት ከእምነት ነፃነት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሃይማኖት ተቋማት የውስጥ አሰራር ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት ይሆናል።

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ከተሰጠው የእግድ ትዕዘዝ አንፃር አመልካች ያቀረቡት ክስ በፍ/ቤት የሚስተናገድ አይደለም በሚል የደረሱበት ድምዳሜ ህግን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል።

<u>ውሣኔ</u>

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 275468 ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 122518 ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል።
2) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።
3) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

መዝገቡ ውሣኔ ሰላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 217220

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡ ሲ/ር ፈለገሽ ዳርጌ፡- ተወካይ ሳሙኤል ዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክር ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች መልስ ሰጪ ተጠሪ ደግሞ ይግባኝ ባይ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በአመልካች ዩኒቨርሲቲ ክሊኒክ ክፍል ኃላፊ በመሆን እየሰራሁ እያለ በ2006 ዓ.ም ነጻ የትምህርት እድል አግኝቼ ተምሬ ከጨረስኩ በኋላ በ2009 ዓ.ም ወደ ሥራ ተመልሰሼ አመልካችን ምደባ ስጠይቅ በሥነ-ምግባ የሥራ መደብ ላይ እንድሰራ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ የምደባ ደብዳቤ ተሰጥቶኛል፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር የሥራ መደቡ ስለሌለ ሊያሠራኝ እንደማይችል ሲገልጽልኝ ይህንኑ ለሰው ሀብት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አስተዳደር ክፍል ወዲያውኑ ያሳወኩ ቢሆንም በህዳር 03 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ የጥሪ ማስታወቂያ በሥራ ላይ ላልተገኘሁበት ማስረጃ አቅርቢ ተብያለሁ፡፡ እኔም ሥራ መስራት ያልቻልኩት የሥራ ምደባ ስላልተሰጠኝ መሆኑን ብገልጽም ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዜ እንዳይከፈለኝ ታግዷል፡፡ በመሆኑም የሥራ ምደባ እንዲሰጠኝ እና ደመወዜ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ ያቀረበ ሲሆን አንዱ የአመልካች መቃወሚያ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ በበላይ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠበትም የሚል ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ተጠሪ ያቀረቡትን የምደባ ጥያቄ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በአማራጭ በሰጠው መልስ ተጠሪ ምንም አይነት የሥራ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት የገለጹት ሀሰት ነው፡፡ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሥነ-ምግብ የሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ተጠሪ የሥራ መደቡ የለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ ተጠሪ ሥራውን ያልሰሩት የሥራ መደቡ አይመጥነኝም በሚል እንጂ መደቡ ስለሌለ ወይም ሥራው ስለሌለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሥራ ሳይሰሩ ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለማይችል ደመወዝ እንዲከፈላቸው መጠየቅ አይችሉም በሚል ተከራክሯል፡፡

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ተጠሪ ለሶስት አመት ተኩል በሥራ ገበታቸው ላይ አለመገኘታቸውን ገልጾ የሚከፈላቸውን ደመወዝ አግዷል፡፡ የተጠሪ ስም በአመልካች መስሪያ ቤት የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ የለም፡፡ አመልካች ሠራተኛን የመቆጣጠር ግዴታውን ሳይወጣ በደፈናው ተጠሪ ሥራ ላይ አልተገኙም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባነት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪን በሥራ ላይ አልተገኙም ካለ ስማቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ አስገብቶ ሥራ ላይ እንዳልተገኙ የሚገልጽ ምልክት በማድረግ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አልተገኙም ብሎ ቢከራከርም አለመኖራቸውን በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ በመሆኑ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተገቢውን ተቀናሽ በማድረግ ለተጠሪ ደመወዝ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካች በህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው በአስተዳደር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱን በመቃወም ተፈጽሟል የሚለውን የህግ ስህተት ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ለበላይ ሀላፊ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ነው በሚል በብይን ውድቅ ከተደረገ በኋላ ይህንን ብይን በሚቃረን መልኩ ተጠሪ ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ፤ ተጠሪ ሥራ መስራት አለመስራታቸው አከራካሪ ባልሆነበት አመልካች ተጠሪ ሥራ ላለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረበም መባሉ እና የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈላቸው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ ተጠሪ ከትምህርት ከተመለሱ በኋላ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሥራ ምደባ ተሰጥቷቸው አለመሥራታቸው ባልተካደበት እና በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እንዳይሰሩ ስለመደረጉ ማስረጃ ባልቀረበበት ከሥራ መታገዳቸው አግባብ አይደለም በማለት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1064/2010 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ክስር ጀምሮ የነበረው ክርክር የደመወዝ መታገድን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከሥራ ስለመሰናበቱ ያነሳው ክርክር ሳይኖር ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ አመልካች የምደባ ደብዳቤ የሰጠኝ ቢሆንም በተማሪዎች አገልግሎት ስር የሥነ-ምግብ የሥራ መደብ አለመኖሩን በዳይሬክቶሬቱ ተገልጾልኛል፡፡ አሁንም ድረስ ይህ የሥራ መደብ የለም፡፡ አመልካች ምደባ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ የጻፍኩት ደብዳቤ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ አመልካች ምደባን በተመለከተ ገና በመስሪያቤቱ ኃላፊ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው በሚል የተከራከረ በመሆኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ምደባ ተሰጥቷት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የሚያጣራበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በየካቲት 06 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ለተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ በአመልካች ምደባ የተሰጠኝ ቢሆንም በሌለ የሥራ መደብ ላይ የምደባ ደብዳቤ የተሰጠኝ በመሆኑ ሥራ መስራት ባልቻልኩበት ሥራ ላይ አልተገኘሽም በሚል ደመወዜ መታገዱ ተገቢ አይደለም የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም ማለታቸው ተገቢ አይደለም፤ ምደባ ተሰጥቷቸው ሥራ ላይ ባለመገኘታቸው ደመወዛቸው መታገዱ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ክርክር መረዳት የሚቻለው ተጠሪ የማስተርስ ትምህርት ጨርሰው ሲመለሱ አመልካች ለተጠሪ የሥራ ምደባ ደብዳቤ እንደተሰጣቸው በግራ ቀኙ የታመነ መሆኑን ነው፡፡ ግራ ቀኙ የተካካዱበት ፍሬ ነገር ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2/2/6 የሥራ መደብ ትርጉም እንደተመለከተው የሥራ መደብ ማለት በአንድ የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ጊዜ እንዲሰራ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥ የሥራ ኃላፊነት እና ተግባር ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የስራ ምደባ ማለት ምደባውን

በሚሰጠው የመንግስት መስሪያቤት ውስጥ ሠራተኛው ባለው እውቀት፣ የሥራ ልምድ እና ክህሎት መሰረት በሥራ ሰአት እንዲያከናውን የሚሰጠው የሥራ ድርሻ ወይም ኃላፊነት ማለት ነው። ሠራተኛው እንዲሰራ በተመደበበት የሥራ መደብ ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ አሠሪው መሥሪያቤት ለሥራው ምቹ የሆነ እና የሠራተኛውን ደህንንነት የሚያስጠብቅ የሥራ ቦታ እና የሥራ መሳሪያ ማቅረብ እንዳለበት፤ ተገቢውን ሥልጠና መስጠት እንዳለበት እና ሌሎች ሁኔታዎችን የማሟላት ግዴታ እንዳለበት በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 65 ላይ ተመልክቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሠራተኛውም በሥራ ሰአት በሥራ መደቡ ላይ ተገኝቶ የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት እና ሌሎች ግዴታዎች ያሉበት መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 66 ላይ ተመልክቷል። ከእነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መረዳት የሚቻለው የመንግሰት መስሪያቤት ለሠራተኛው ተገቢውን የሥራ መደብ እና ለሥራ መደቡ የሚያስፈልጉ አቅርቦቶችን ማሟላት እና ሠራተኛውም በስራ ሰአት በሥራ ቦታ ላይ በመገኘት ተገቢውን ሥነ-ምግባር ጠብቆ ሥራውን የማከናወን ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። እነዚህ ከአሠሪውም ሆነ ከሠራተኛው የሚጠበቁ ግዴታዎች ከተጣሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 68 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ደመወዛቸውን የማገድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደው ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አልተገኙም በሚል ነው። ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ በሥራ ቦታቸው መገኘት ያልቻሉት በአመልካች የተሰጣቸው የሥራ መደብ በተግባር ባለመኖሩ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል። ከላይ እንደተመለከተው የተጠሪ አሠሪ ሆነው አመልካች የሥራ መደብ ለተጠሪ የመሥጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባውም በደብዳቤ ከመገለጹ በተጨማሪ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ሊሆን እንደሚገባ ግልጽ ነው። አመልካች በደብዳቤ ተጠሪን የመደበ ቢሆንም በደብዳቤ የተገለጸውን የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤት ውስጥ የሌለ ከሆነ አመልካች በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 65 ላይ የተመለከተውን ሥራ እና ሥራ ቦታ አመቻችቶ የመስጠት ግዴታውን ስላልተወጣ የተጠሪን ደመወዝ ማገዱ ህጋዊ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ተጠሪ በደብዳቤ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ በተግባር አለ ወይስ የለም የሚለው የግራ ቀኙ የክርክር ጭብጥ ተደርጎ በተገቢው ማስረጃ ከተጣራ በኋላ የተጠሪ ደመወዝ መታገዱ ተገቢ ነው አይደለም ለሚለው ምላሽ የሚያገኝ በመሆኑ በመጀመሪያ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለው ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ ሊጣራ ይገባ ነበር።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ለሶስት አመት ተኩል ተጠሪ በሥራ ቦታ ስለመገኘት አለመገኘታቸው ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ ግዴታውን አልተወጣም እንዲሁም አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አለመገኘታቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ በማቅረብ አላስረዳም በሚል የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል። በእርግጥ አመልካች ለተጠሪ በሰኔ ወር 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ምደባ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እየሰሩ መቆየት አለመቆየታቸውን የመቆጣጥር ኃላፊነት እንዳለበት አከራካሪ አይደለም። ይሁን እንጂ ላለፉት ሶስት

አመታት ተቆጣጥሮ እርምጃ አለመውሰዱ ከሶስት አመት ተኩል በኋላ ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ እስካልተገኙ እና ድርጊቱ እስከቀጠለ ድረስ እርምጃ ከመውሰድ የሚያግደው ወይም እርምጃ የመውሰድ መብቱን የሚያስቀረው አይሆንም፡፡ ተጠሪ ሥራ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ ያልተገኙበትን ምክንያት በመግለጽ የሚከራከሩ ከመሆኑ አንጻር ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በተመለከተ የታመነ ፍሬ ነገር ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 መሰረት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡

ሌላው አመልካች በሰበር ቅሬታው የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት ተጠሪ ለስር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሥራ ስንብትን በተመለከተ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የለም፡፡ አመልካችም ለተጠሪ ቅሬታ በሰጠው መልስ የተጠሪ ደመወዝ ያልተከፈለው ከሥራ በመሰናበታቸው ነው በሚል ያቀረበው ክርክር ያለም፡፡ ከስር ጅምሮ የነበረው ክርክር ከደመወዝ መታገድ ጋር ብቻ የተያያዘ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ከሥራ ስንብት ጋር ተያይዞ የተነሳው ክርክር የሚታይበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አመልካችን አሰናብቻለው የሚል ከሆነ እራሱን ችሎ ክርክር የሚደረግበት በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 246 መሰረት ግራ ቀኙ በተካካዱበት ፍሬ ነገር ማለትም ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤቱ ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰርት እንዲሁም ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ አመልካች ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ምክንያት የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ግድፈት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማረም ሲገባው አለማረሙ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176/2013 በግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209017 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ በታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 217557

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አክስዬን ማህበር- ጠበቃ ፕ/ር ጥላሁን ተሾመ እና ነ/ፈጅ አበራ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የኢትዬጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ-ነ/ፈጅ ሰለሞን ነጋሽ ቀረቡ

2ኛ. የኢትዬጵያ ብሔራዊ ባንክ- ነ/ፈጅ ታፈሰ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 28/03/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀን 01/02/2014 ዓ.ም ለባለጉዳዮች ተነቧል የተባለው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው። ክርክሩ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጣ/ገብቶ ተከራክሯል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ከሳሽ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ/ም እና በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ በማለት ጠይቋል።

ተከሳሽ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ነገር ክርክሩን አቅርቧል። ባቀረበው መቃወሚያ ተከሳሽ ለጣ/ገብ በ04/02/2013 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ቋሚ መመሪያ እስኪወጣ ድረስ በማለት የሰጠውን መመሪያ ለማብራራት የተጻፈ ደብዳቤ እንጂ አስተዳደራዊ ውሳኔ አይደለም። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከመውጣቱ በፊት የወጣ ስለሆነ አዋጁ በመመሪያው ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም። በተጨማሪም ከሳሽ ተከሳሽ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 51 መሰረት ለተከሳሽ ተቋም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ያላቀረበ ስለሆነ ከሳሽ የተከሳሽን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ተከራክሯል።

ጣ/ገብ በበኩሉ ወደክርክሩ ገብቶ ባቀረበው መቃወሚያ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ ጣ/ገብ ለተከሳሽ ለጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ሲሆን በግልባጭ ከሳሽ እንዲያውቀው ተደርጓል። ሆኖም ከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መሰረት ለተከሳሽ ምንም ቅሬታ ያላቀረበ ስለሆነ በአዋጁ መሰረት አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ከሳሽ በአዋጁ መሰረት የአስተዳደር ውሳኔው በተወሰነ 30 ቀናት ውስጥ ክስ ማቅረብ ሲኖርበት ግዜው ካለፈ በኋላ በማቅረቡ በይርጋ ይታገዳል። እንዲሁም በራሱ 22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ በ23ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተሻረ ስለሆነ ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት ተከራክሯል።

ለመቃወሚያ ክርክሩ ከሳሽ በሰጠው መልስ መቃወሚያዎቹ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2) መሰረት የቀረቡ አይደሉም፤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ እንደሚለው ቋሚም ሆነ ግዜያዊ መመሪያ አይደለም፤ የቦርድ ሰብሳቢ መመሪያም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፤

ስልጣን ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤ እነዚህ ደብዳቤዎች የአስተዳደር መመሪያዎች እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም። መብታችን በመነካቱ ነው ፍ/ቤት የመጣነው። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ በተጻፈው ደብዳቤ መነሻ ላቀረብነው ቅሬታ ምላሽ የተሰጠን አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከወጣ በኋላ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም ስለሆነ ይህንኑ መሰረት አድርገን ነው ክስ ያቀረብነው። በአስተዳደር ተቋም ውስጥ ያለውን መፍትሄ አሟጦ መጨረስን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በቦርድ ሰብሳቢ የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን በመግለጽ ለቦርዱ ሰብሳቢ ለራሳቸው አመልክተናል፤ በግልባጭም ለጣ/ገብ አሳውቀናል። ጣ/ገብም በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቋል። ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለ በግልባጭ አሳውቆናል፤ ደብዳቤው በአድራሻ የተጻፈ ለጣ/ገብ ነው። ተከሳሽ ቅሬታ ስናቀርብ ወደ ቅሬታ ሰሚ ሂዱ ብሎ አልመራንም፤ አሁንም ቢሆን ተከሳሽ ቅሬታ ሰሚ አካል ያቋቋመ ስለመሆኑ ይፋ አላደረገም። በመሆኑም መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን አቅርበን ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለው በመግለጽ ይርጋ ጊዜውን አቋርጦታል። መብትና ጥቅም የለውም የተባለውን በተመለከተም በክሱ መሰረት ከተወሰነልን በ22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ ደግሞ ለመወሰን የሚያስችለን ስለሆነ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም አለን በማለት ተከራክሯል።

የመቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ደብዳቤዎቹ የአስተዳደር መመሪያዎች አይደሉም እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም፤ መብታችን ስለተነካ ነው ፍ/ቤት የመጣነው በማለት ለመቃወሚያው ክርክር ቢያቀርብም ከሳሽ ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም ባቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም እና 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ የጠየቀ ስለሆነ ክርክሩ ከክሱ አንጻር ተገቢነት የለውም። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ

በቀረበው ቅሬታ ላይ የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ ስለመሆኑ አላከራከረም። በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ነው። አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም ከመሆኑ አንጻር በአስተዳደር ውሳኔው ላይ ቅሬታው ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን ሆኖ አልተገኘም። በዚህ መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 51 ማንኛውም የክለሳ አቤቱታ ፍ/ቤት የሚቀርበው የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ብቻ መሆኑ የተደነገገ ስለሆነ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም። በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 56(2) መሰረት ፍ/ቤት የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር ውሳኔ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ የአስተዳደር ውሳኔው እና ቅሬታው በአዋጁ በማይሸፈኑበት ሁኔታ ፍ/ቤት በቅሬታው ላይ የተሰጠውን ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ የአስተዳደር ውሳኔውን ማጽናት ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር አይችልም። በመሆኑም ሌሎች መቃወሚያዎችን መመርመር ሳያስፈልግ የቀረበውን የክለሳ አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 ስር የማይሸፈን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።.....

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 28/03/2013 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ በተሰጠው ብይን ተፈፀሙ የሚላቸውን የህግ ስህተቶች ዘርዝሮ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ፍሬ ነገር ክርክር አላግባብ አዛብቶ በመረዳት እና የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጁን ተፈጻሚነት በተመለከተ የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ብይኑ እንዲሻርና ስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬነገሩ በመግባት ክርክሩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ እንዲወሰንልን በማለት ቅሬታውን አቅርቧል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ስር አይሸፈንም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

1ኛ ተጠሪ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ክርክሩን አጠናክሮ የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከ11 ወራት በኋላ በወጣ ህግ ስለማይዳኝ እና ከአዋጁ መውጣት በፊት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል።

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታው በአዋጁ የማይሸፈን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይን ትክክለኛና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል። ይህ ታልፎ ብይኑ የሚሻር ከሆነ ግን የስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመታዘዙ በፊት በተጠሪዎች በኩል በተነሱት ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን እንዲሰጥባቸው እንዲታዘዝ በማለት ጠይቋል። አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል። እንደመረመርነው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አይሸፈንም ፍርድ ቤቱም የክለሳ አቤቱታውን ለመመልከት ስልጣን የለውም በማለት ብይን የሰጠው በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለቀረበው ቅሬታ የተሰጠ ምላሽ መሆኑን ተገንዝበ፤ ነገር ግን በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ በመሆኑና በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም በመሆኑ ለቦርዱ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን

አይደለም፤ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም በሚል ነው።

በመሰረቱ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከወጣበት ምክንያት አንዱ የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን እና ሥነ ሥርዓት በመደንገግ እንዲሁም በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

"የአስተዳደር ውሳኔ" ማለት ደግሞ የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2(3) ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል። በእንዲህ አይነት የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 48(2) እና 49(1) ስር ተመልክቷል። ስለሆነም ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአስተዳደር ተቋሙ በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ በሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው የክለሳ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል መደንገጉን ሲሆን ከዚህ በቀር የአስተዳደር ውሳኔው የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከተሰጠ ውሳኔ ጋር በተያያዘ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም እንዲሁም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስልጣን አይኖረውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም።

በ1952 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለ አስተዳደር ክፍሎች በሚደነግገው አንቀጽ ሶስት ምዕራፍ አንድ ቁጥር 401(1) እና 402(1) ሥር ከተመለከተው ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የአስተዳደር አካላት በህግ የታወቀላቸው የተግባር ስልጣን ከሚዘረጋበት ውጭ ወይም በህጉ የተገደዱትን ሁኔታዎች ወይም ፎርም ባለመከተል የሚፈጽሟቸው ሥራዎች ፈራሾች ሲሆኑ ይህን ፈራሽነት ማንኛውም ባለጉዳይ ሁሉ ሊጠይቅ ይችላል። ስለሆነም አስተዳደሩ በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ ሲወስን ወይም በህግ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ወይም የተዘረጋውን ስርዓት ባለመከተል ወስኖ

ሲገኝ በአስተዳደሩ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔው በፍርድ ፈራሽ እንዲሆን ሊወሰን እንደሚችል አስቀድሞም ቢሆን በፍትሐ ብሔር ህጉ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው።

ከዚህም ሌላ አመልካች በፅሁፍ ባቀረበው የክለሳ የዳኝነት ጥያቄ ላይ እንዲሁም በተጠሪዎች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተከትሎ ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ወጥነት አለመኖሩን በማንሳት የስር ፍርድ ቤት የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎችም ይህን በመከራከሪያነት አያይዘው ማንሳታቸውን ተመልክተናል። ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ስርዓት በተመለከተ የክለሳ ስነ ስርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 58 ተደንግጓል። ስሆነም ለክለሳ ለክርክሩ በአዋጁ የተመለከቱ ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች የሚፈፀሙበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚመራው በፍትሐ ብሐር ሥነ ሥርዓት ህጉ አግባብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ከሳሽ በህጉ የተፈቀደን መፍትሄ ከፍርድ ቤቱ ለማግኘት በፅሁፍ በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ ይገባዋል። በዚህ መልኩ በጽሁፍ ግልጽ የዳኝነት ጥያቄውን ካቀረበ በኃላ መቃወሚያን ለመወሰንም ይሁን በፍሬ ነገር ላይ በችሎት የሚያቀርብ ክርክር መሰረታዊ አላማው በጽሁፍ ያቀረበውን ክርክር ለማብራራት እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ለማስተናገድ አይደለም። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 83፣ 222፣ 224፣ 234፣ 235፣ 236፣ 241፣ 244፣ 245 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ የኢትዬጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥቅሙን የሚነካና የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ ለመጠየቅ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ክርክሩ ሊመራና ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባውም ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው።

ስለሆነም ግራቀኙ የየበኩላቸውን ክርክር ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበው ቅሬታ ላይ

የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል በሚል ለያይቶ መወሰኑ በግልፅ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እና ከፍሲል የጠቀስናቸውን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘት የተከተለ አይደለም።

በአጠቃላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በግልጽ በጽሁፍ የቀረበውን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽን ብቻ መሰረት በማድረግ የቀረበ አቤቱታ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ፤ ይህን ተከትሎም መሰል የክለሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፤ አመልካች ያቀረበው የክለሳ አቤቱታ በአዋጁ የሚሸፈን አይደለም፤ እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ብይን የሚነቀፍ ነው። የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከእነሙሉ ይዘቱ በአግባቡ ሳይጤን፤ ከፍሲል ከተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከክርክሩ ውጪ በመውጣት የተሰጠ ብይን በመሆኑም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ቀሪ ክርክር ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 341/1/ መሰረት መልሰናል። የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው።
3. ከስር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት አግባብ ይመለስ።
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 217836

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመካው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ስንታየሁ የግል 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ጠበቃ ንጉሴ አበበ ቀርበዋል

ተጠሪዎች-

1. አቶ ይርጋ ባይችሉ
2. ወ/ሪት ትሪንጎ ካሳሁን
3. ወ/ሪት ሙሉሰዉ ጌታነህ
4. አቶ ዳኛቸዉ አብጥ
5. አቶ ዘማርያም ጋርዶ
6. አቶ ተሾመ ሽመልስ
7. አቶ ልጃለም አለህኝ
8. ወ/ሮ አለምጸሐይ በየነ

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በአመልካች ትምህርት ቤት በመምህርነት ተቀጥረዉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመስራት ላይ እያሉ ከነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ወደ ትምህርት ቤቱ ግቢ እንዳይገቡ በመከልከልና ወደ ፖሊስ ሄዳችሁ ከሳችሁኛል በሚል ምክንያትም ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸዉ ከስራ እንዲሰናበቱ ያደረገበት አግባብ ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰዉ አመልካች ወደ ስራ እንዲመልሳቸዉ፣ ወደ ስራ የማይመለሱበት ምክንያት ካለም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸዉ እንዲሁም ለስራ ግብርና ለጡረታ በሚል ከደመወዛቸዉ ሲቀንስ የነበረዉን ለሚመለከታቸዉ አካላት ገቢ እንዲያደርግ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገ የቅጥር ዉል ከመስከረም እስከ ሰኔ የሚቆይ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ፡፡ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ በወጣዉ አስቸኳይ አዋጅ ምክንያት ከመጋቢት 2012 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸዉ ለመምህራን የሚከፈል ደመወዝ ባለመኖሩ ትምህርት ቢሮ ባወጣዉ መመሪያ መሠረት አመልካች 75 ከመቶ ከወላጆች ሰብስቦ ለመምህራንና ሠራተኞች እንዲከፈል ጥረት ያደረገ ቢሆንም ከአመልካች ድርጅት የግል ገንዘብ ተጨምሮበት እስከ ሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ለተጠሪዎች ሙሉ ደመወዝ የከፈለ ሲሆን በአቅም ችግር ምክንያት አመልካች የሐምሌ እና ነሐሴ ወር ደመወዝ ግን ለመክፈል አልቻለም፡፡ የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ዉሉን ማቋረጡ አዋጁን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ የስንብት፣ ዉዝፍ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን አስመልክቶ የቀረበ የክፍያ ጥያቄ ያላግባብ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተጠሪዎች አዲስ ዉል እንዲያደርጉ ከአመልካች የቀረበላቸዉን ጥያቄ ባለመቀበል ስራ ለመጀመር ፍቃደኛ ባለመሆናቸዉ ምክንያት መሆኑን እና አመልካች ለተጠሪዎች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ደመወዝ መክፈል ያልቻለዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በመረጋገጡ ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ደመወዝ ባለመክፈሉ መሆኑን ጠቅሰዉ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በህገ ወጥ መንገድ ነዉ በማለት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች ደመወዝ በወቅቱ መክፈል ያልቻለዉ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤት በመዘጋቱ እና የተማሪዎች ወላጆችም ክፍያ በማቋረጣቸዉ ባጋጠመዉ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል የመዘግየት ቅጣትን አስመልክቶ የተጠየቀዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ የትራንስፖርት እና የቤት አበልን ጨምሮ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤትም መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ከአመልካች ድርጅት የስራ ባህርይ አንፃር ሲታይ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የስራ ዉል በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 10 እና 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር በመሆኑ የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ በማለት አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ የስራ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ እያለ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር

ደመወዝ አለመክፈሉ እና ተጠሪዎች ዉል በአዲስ መልክ ያዙ በማለት አመልካች ለዉሉ መቋረጥ ምክንያት ሆኖ እያለ ዉሉ የተቋረጠዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ የስራ ዉሉ ለመቋረጡ መነሻ ምክንያቱ የአመልካች አነሳሽነት ብቻ ሳይሆን የተጠሪዎችም አነሳሽነት እንዳለበት ጠቅሶ አመልካች የስራ ስንብት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ካለ በኋላ አመልካች ለተጠሪዎች ካሳ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ለእያንዳቸዉ የአንድ ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ተጠሪዎች የ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ዉል እንዲይዙ ተጠይቀዉ የሐምሌ እና የነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ደመወዝ ካልተከፈለን ዉል አንይዘም፤ አናስተምርም በማለት ዉሉን በእራሳቸዉ አነሳሽነት አቋርጠዉ እያለ ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች የሁለት ወር ደመወዝ አመልካች አልከፍልም እንዳለ በማስመሰል የስራ ዉሉ በአመልካች ጉድለት ተቋርጧል በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ እንዲሁም የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ እያለ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ በሚል አመልካች ካሳ እንዲከፍል በማለት መወሰኑ እንዲሁም ካሳዉ ያልተጣራ ደመወዝ መነሻ ማድረግ ሲገባዉ የቤት ኪራይ፣ አበል እና ትራንስፖርትን ጨምሮ በማስላት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የስራ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንደሆነ ወስዶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጋራ ባቀረቡት መልስ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሁለት ወር ደመወዝ በተጨማሪ አመልካች ካሳ እና የደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት የአንድ ወር ደመወዝ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ሲወስን መሠረት ያደረገዉ በግራ ቀኝ መካከል የነበረዉ የስራ ቅጥር ዉል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ ሳለ አመልካች ዉሉ የሚቆየዉ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነዉ በሚል ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ ባለመክፈሉ እና ተጠሪዎች የስራ ዉል በአዲስ መልኩ ያዙ በማለት ለስራ ዉሉ መቋረጥ ምክንያት መሆኑን እና ይህም ድርጊቱ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ተከትሎ የወጣዉን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ጭምር ያላገናዘበ በመሆኑ ዉሉ

የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስለመሆኑ የወሳኔው ግልባጭ ያሳያል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን በመቃወም የሰረበለትን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ትዕዛዝ የሰጠው ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። ይህ ከሆነ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በትዕዛዝ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል።

እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ውሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነው። መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው? ወይም አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው መቼ ነው? የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠው ውሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠውም ነበር። ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ማድረግን አንዱ ዓላማው ያደረገው ይህ አዋጅ ካካተታቸው አዳዲስ ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነው። በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነው።

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበው ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ

ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ውሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘዉ በክልሉ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0149107 ላይ ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 108073 ላይ ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. የሰበር አጣሪ ችሎት ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 212603

ሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የኢትዮጵያ አየር መንገድ

ተጠሪ- አቶ ተከስተ ካሴ

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ እ.አ.አ. ከቀን 22/04/2020 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 42,863.37 እየተከፈለኝ በአውሮፕላን ጥገና አሰልጣኝነት ሳገለግል ቆይቻለሁ፡፡ ከመስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ በተቋቋመው የሰራተኛ ማህበር ውስጥ ምክትል ፀኃፊ በመሆን እያለገልኩ ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ስለእኔ እውነት ያልሆነ መረጃ በማስተላለፍ ስም እና ዝናዬን አጥፍተሃል፣ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በስራ ቦታ መተባበር እና ሰላማዊ የስራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት የስራ ውሌን አቋርጦታል፡፡ ከስራ ስሰናበት በህብረት ስምምነቱ መሠረት በተቋቋመው ኮሚቴው ውስጥ የሰራተኛ ማህበር ተወካይ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ያልተከፈለኝ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ፤ ወደ ስራ ልመለስ የማልችልበት አግባብ ካለ ደግሞ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዝያ ወር ሙሉ ደሞዝ፣ እ.አ.አ. የ2020 ዓ.ም የዓመት እረፍት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክፍያ እንዲከፍለኝ እና የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ።

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪን ከስራ ያሰናበትናቸው የሰራተኛ ማህበር አባል በመሆናቸው ሳይሆን የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም በድርጅታችን መልካም ስም እና ዝና ላይ የስም ማጥፋ ዘመቻ በማካሄዳቸውና በስራ ቦታ ላይ ሊኖር የሚገባውን መልካም የስራ ግንኙነት እና መግባባት የሚያበላሽ ተግባር በመፈፀማቸው ነው፤ ለአብነት ያህል የኛ ቲዩብ ከተባለ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ አመልካች ድርጅት ሰራተኛ ሲቀጥርም ሆነ ሲያሰናብት መርህ የለውም፣ የድርጅት ሰራተኞች ለድርጅቱ አመራሮች ብቻ ተገዢ እንዲሆኑ ነው የሚሰራው፤ ድርጅቱም ሆነ አመራሩ የሚያስበው ለውጪ ሃገር ዜጎች እንጂ ኢትዮጵያዊ ለሆነው ሰራተኛ አይደለም፤ የኮቪድ 19 ስርጭትን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ሰራተኞችን በመቅጣት በፍርሃትና በመርበትበት እንዲኖር እያደረገ ነው ሲሉ ስም አጥፍተዋል፤ ይህ የተጠሪ ድርጊት ከስራ የሚያስናብት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው እንኳን ቢባል በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው መተማመን በእጅጉ የሻከረ በመሆኑ ተጠሪ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የሰጡት ቃለ-ምልልስ የአመልካች ድርጅትን ስም የሚያጠፋ፣ መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ወይም የሚያጥላላ ሳይሆን ያላቸውን የመናገር ነፃነት ተጠቅመው ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ተችሏል፤ አመልካች በዚህ ምክንያት ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሆነ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደሞዝ ብር 257,174.22 ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 377 መሠረት ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 07/12/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 08 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ማህበር ጣልቃ መግባትን የሚመለከተውን ክስ ከተጠሪ ስንብት ጥያቄ ጋር አጣምረው ማቅረባቸው ተገቢ ነው ማለቱ፤ ተጠሪ ቃለ-ምልልስ ያደረጉት በግላቸው ሳይሆን ማህበሩን ወክለው ነው መባሉ፤ ቃለ-ምልልሱ የተጋነነ ቢሆንም ካለው ሁኔታ አንፃር እውነት መሆኑን መረዳት ይቻልል ሲል የስር ፍርድ ቤት በደፈናው ድምዳሜ ላይ መድረሱ፤ እንዲሁም ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካች እና የተጠሪን የሻከረ የስራ ግንኙነት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገበዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ተጠሪ ወደ ስራ ይመለሱ በማለት የተወሰነበት አግባብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት አመልካች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 15/02/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ንግግሩን ያደረጉት ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና እንጂ በራሳቸው አይደለም፤ አመልካችም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011

አንቀጽ 26 በመተላለፍ የሰጠው ስንብት አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ሲል ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፤ ተጠሪ በቃለ-ምልልስ ወቅት ያነሳኋቸው ጉዳዮች እውነት መሆናቸውን በማስረጃ ጭምር በስር ፍርድ ቤት አረጋግጫለሁ፤ ተጠሪ ያደረጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከማህበሩ በተሰጣቸው ውክልና ላይ የተመሠረተ ሲሆን በግላቸው ከአመልካች ጋር ምንም አይነት የሻከረ ግንኙነትም ሆነ መቃቃር በሌለበት አመልካች የተበላሸ የስራ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀው ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢነቱን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ አመልካች ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደሥራ እንዲመለስላቸው፤ ይህ ካልሆነም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የአመልካች ተግባር ያልሆነውን ሀሰተኛ መረጃ በመገናኛ ብዙኃን በመግለጽ መልካም ስምና ዝናውን የሚያጎድፍ ተግባር በመፈጸማቸውና ንብረት ጥቅሙ ላይ ጉዳት በማድረሳቸው ምክንያት የሥራ ውላቸው የተቋረጠ ስለሆነ የሥራ ሥንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል። በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል። የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል። የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል። ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል።

ሠራተኛ የአሠሪው ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር ከፈጸመ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአሠሪውን ሥም ማጥፋትም ሥራው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ድርጊት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በሠራተኛ ማሕበር አመራርነታቸው ሳይሆን በመገናኛ ብዙኃን በመቀጠም የአመልካች ደርጅት መልካም ስምና ዝና ላይ ሀሰተኛ የሥም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂድ ቡድን ላይ ዋና ተዋናይ ሆነው አመልካች የሠራተኛውን ክብር የማይጠበቅ፣ ሕገ-ወጥ ፖሊሲ ተቀርጾ ሠራተኛ ላይ በደል እንደሚፈጸም፣ አመራሩ ከሕግ በላይ ነን የሚሉና በማን አለበኝነት መንፈስ የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው፣ ሕግን ያልተከተለ የውጭ ምደባ እንደሚደረግ፣ ምደባ በሥራ አፈጻጸም ሳይሆን ከአመራር ጋር ባለ ቀረቤታና ቁርኝት እንደሚፈጸም፣ የበረራ አስተናጋጆች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ያልተገባ ድጋሜ ክፍያ እንደሚፈጸም በማለት ሀሰተኛ እና ስም የሚያጠፋ መረጃ ሰጥቷል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸውበሠራተኞች ማሕበር ውስጥ በምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ እየሰራሁ እያለ ማሕበሩን በመወከል የተገለጸ ነው፣ የአመልካችን ስም የሚያጎድፍ ሆነ የሠራተኛውን ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠፋ ተግባር ባልተፈጸመበት የተሳሳተ መረጃ ሰጥተሃል፣ ሰላማዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዳይኖር አድርገሃል በማለት ከግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ማሰናበቱ ሕገ-ወጥ ስንብት ነው የሚል ነው፡፡

የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመለየት፣ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ኃላፊነት የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተጠሪ የሰጡትን ቃለምልልስ ሲዲውን አስቀርቦ በመመልከት ተጠሪ ቃለ ምልልሱን ያደረጉት በሠራተኛ ማሕበሩ ተዋካይ በመሆናቸዉ እንጂ በግል ያደረጉት አይደለም፣ በተጨማሪም በሰዓቱ ተጠሪ ሲናገሩ የነበሩት በግላቸዉ ስለደረሰባቸዉ በደል ሳይሆን ሠራተኛዉ በአጠቃላይ ችግሮች አሉበት የሚል ይዘት ያለዉ መሆኑን እና ተተሪ በቃለ ምልልሱ የገለፃቸዉ ጉዳዮች አለመከሰታቸዉን አመልካች ያስረዳበት ሁኔታ አለመኖሩን፣ ተጠሪ በቃለ ምልልሱ የተናገሩት የግል አስተያየታቸዉ ነዉ ቢባ እንኳን የአመልካችን ድርጅት ስም የሚጠፋ እና የሚያጥላላ ሳይሆን ተጠሪ ያላቸዉን የመናገር ነፃነት ተጠቅመዉ ያደረጉት እንደሆነ ከይዘቱ መረዳቱን ጠቅሶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የፈጸመ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገው የሕብረት ሥምምነት አባሪ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል ሀ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ስምና ዝና የሚያጎድፍ፣

መልካም ግንኙነት የሚሻክር ከባድ ጥፋት መፈጸሙ ሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ድንጋጌ መጣሱን የሚያስረዳ ሳይሆን ተጠሪ የማሕበሩ ተወካይ በመሆናቸዉ በማሕበሩ አባላት ላይ ደርሰዋል ያሉትን የመብት ጥሰቶችና ግድፈቶች በመግለጻቸው ከሥራ መሰናበታቸው ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ነው በማለት መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

ወደሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ ተጠሪ ወደሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን የሠበር አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(1)(2) የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ በአሠሪው የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደሥራው እንዲመለስ ሊወሰን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ወደሥራ ሊመለስ የማይችለው ከሥራው ጠባይ ግንኙነት የተነሳ ወይም ከክርክር ሂደት ከወሰደው ግንዛቤ በሥራ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲታመን እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ከፍተኛ ችግር የሚለው የሕጉ አነጋገር ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት ሠራተኛውን ወደሥራው እንዳይመለስ ማድረግ የማይችል መሆኑን እና የሚያስከትለው ጉዳት ጉልህ የሆነ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህም ሕግ አውጭው በአንድ በኩል የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ ለሠራተኛው ሆነ ለሀገር መሠረት የሆነውን የሠራተኛውን ቤተሰብ መጠበቅ እንዳለበት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል የሥራ ሁኔታውን እና የኢንዱስትሪውን ሠላም ማስጠበቅ ለምርታማነት መሠረት መሆኑን በመገንዘብ በሁለቱ አሳቤዎች መካከል ጉዳዩ እንዲገዛ የፖሊሲ ውሳኔ ላይ መድረሱን እና ጉዳዩም የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ምክንያታዊ በሆነ አግባብ እንዲጠቀም ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ግራቀኙ ተከራካሪዎችም በተለይም አሠሪው ፍርድ ቤቱን ለማሳመን ሠራተኛው ወደሥራ ቢመለስ የሚስከትለውን ጉልህ የሆነ ጉዳት ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የአውሮፕላን ጥገና ባለሙያ ሲሆኑ ከአመልካች አስተዳደር ጋር አለመግባባት መኖሩ ከሥራ ድርሻቸው አንጻር ወደሥራ መመለሳቸው አመልካች ላይ ጉልሕ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37454 የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ሠራተኛው የጥበቃ ሠራተኛ መሆኑ እንዲሁም ከአለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር መሆኑና በእጁም ትጥቅ ያለ መሆኑ የሥራ ውሉን ለማስቀጠል የማይቻል መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የአሠሪው ሠላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅትን ጠቅላላ ንብረት ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሠው መሆኑን ግምት ወስጥ በማስገባት ወደሥራ ሊመለስ እንደማይገባ የተወሰነበት ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ. 64079 የተወሰነውም ገንዘብ ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ መሆኑን በመገንዘብና ጥፋት ፈጽሟል የተባው ከሥራ ኃለፊነቱ ጋር በተያያዘ በመሆኑ፤ ከአሠሪው ጋር ያለው መተማመን ከቀነስ ባለበት ኃላፊነት ወደሥራ መመለስ መልካም የሥራ ግንኙነት አይፈጥርም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር የተያያዘ ጥፋት ፈጽሟል ያልተባለ በመሆኑና ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ከተወሰኑት ጉዳዮች ጋር የፍሬ ነገር ልዩነት ያለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ወደሥራ ቢመለሱ ሥራው ላይ ያለው ከፍተኛ ጉዳትን አመልካች ያላሳየ ስለሆነ

በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደሥራ እንዲመለሱ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል። በሌላ በኩል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(5) መሠረት ተጠሪ ወደሥራው እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ታይቶ የጸና በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል ብለናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117180 ላይ ህዳር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ነበዋለዉ ችሎት እንዲሁም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 274582 ላይ ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል።
3. የሰበር አጣሪ ችሎት ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል።
4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 217220

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡ ሲ/ር ፈለገሽ ዳርጌ፡- ተወካይ ሳሙኤል ዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክር ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች መልስ ሰጪ ተጠሪ ደግሞ ይግባኝ ባይ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በአመልካች ዩኒቨርሲቲ ክሊኒክ ክፍል ኃላፊ በመሆን እየሰራሁ እያለ በ2006 ዓ.ም ነጻ የትምህርት እድል አግኝቼ ተምሬ ከጨረስኩ በኋላ በ2009 ዓ.ም ወደ ሥራ ተመልሰሼ አመልካችን ምደባ ስጠይቅ በሥነ-ምግባ የሥራ መደብ ላይ እንድሰራ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ የምደባ ደብዳቤ ተሰጥቶኛል፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር የሥራ መደቡ ስለሌለ ሊያሠራኝ እንደማይችል ሲገልጽልኝ ይህንኑ ለሰው ሀብት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አስተዳደር ክፍል ወዲያውኑ ያሳወኩ ቢሆንም በህዳር 03 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ የጥሪ ማስታወቂያ በሥራ ላይ ላልተገኘሁበት ማስረጃ አቅርቢ ተብያለሁ፡፡ እኔም ሥራ መስራት ያልቻልኩት የሥራ ምደባ ስላልተሰጠኝ መሆኑን ብገልጽም ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዜ እንዳይከፈለኝ ታግዷል፡፡ በመሆኑም የሥራ ምደባ እንዲሰጠኝ እና ደመወዜ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ ያቀረበ ሲሆን አንዱ የአመልካች መቃወሚያ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ በበላይ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠበትም የሚል ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ተጠሪ ያቀረቡትን የምደባ ጥያቄ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በአማራጭ በሰጠው መልስ ተጠሪ ምንም አይነት የሥራ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት የገለጹት ሀሰት ነው፡፡ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሥነ-ምግብ የሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ተጠሪ የሥራ መደቡ የለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ ተጠሪ ሥራውን ያልሰሩት የሥራ መደቡ አይመጥነኝም በሚል እንጂ መደቡ ስለሌለ ወይም ሥራው ስለሌለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሥራ ሳይሰሩ ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለማይችል ደመወዝ እንዲከፈላቸው መጠየቅ አይችሉም በሚል ተከራክሯል፡፡

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ተጠሪ ለሶስት አመት ተኩል በሥራ ገበታቸው ላይ አለመገኘታቸውን ገልጾ የሚከፈላቸውን ደመወዝ አግዷል፡፡ የተጠሪ ስም በአመልካች መስሪያ ቤት የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ የለም፡፡ አመልካች ሠራተኛን የመቆጣጠር ግዴታውን ሳይወጣ በደፈናው ተጠሪ ሥራ ላይ አልተገኙም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባነት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪን በሥራ ላይ አልተገኙም ካለ ስማቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ አስገብቶ ሥራ ላይ እንዳልተገኙ የሚገልጽ ምልክት በማድረግ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አልተገኙም ብሎ ቢከራከርም አለመኖራቸውን በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ በመሆኑ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተገቢውን ተቀናሽ በማድረግ ለተጠሪ ደመወዝ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካች በህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው በአስተዳደር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱን በመቃወም ተፈጽሟል የሚለውን የህግ ስህተት ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ለበላይ ሀላፊ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ነው በሚል በብይን ውድቅ ከተደረገ በኋላ ይህንን ብይን በሚቃረን መልኩ ተጠሪ ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ፤ ተጠሪ ሥራ መስራት አለመስራታቸው አከራካሪ ባልሆነበት አመልካች ተጠሪ ሥራ ላለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረበም መባሉ እና የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈላቸው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ ተጠሪ ከትምህርት ከተመለሱ በኋላ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሥራ ምደባ ተሰጥቷቸው አለመሥራታቸው ባልተካደበት እና በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እንዳይሰሩ ስለመደረጉ ማስረጃ ባልቀረበበት ከሥራ መታገዳቸው አግባብ አይደለም በማለት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1064/2010 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ክስር ጀምሮ የነበረው ክርክር የደመወዝ መታገድን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከሥራ ስለመሰናበቱ ያነሳው ክርክር ሳይኖር ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ አመልካች የምደባ ደብዳቤ የሰጠኝ ቢሆንም በተማሪዎች አገልግሎት ስር የሥነ-ምግብ የሥራ መደብ አለመኖሩን በዳይሬክቶሬቱ ተገልጾልኛል፡፡ አሁንም ድረስ ይህ የሥራ መደብ የለም፡፡ አመልካች ምደባ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ የጻፍኩት ደብዳቤ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ አመልካች ምደባን በተመለከተ ገና በመስሪያቤቱ ኃላፊ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው በሚል የተከራከረ በመሆኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ምደባ ተሰጥቷት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የሚያጣራበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በየካቲት 06 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ለተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ በአመልካች ምደባ የተሰጠኝ ቢሆንም በሌለ የሥራ መደብ ላይ የምደባ ደብዳቤ የተሰጠኝ በመሆኑ ሥራ መስራት ባልቻልኩበት ሥራ ላይ አልተገኘሽም በሚል ደመወዜ መታገዱ ተገቢ አይደለም የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም ማለታቸው ተገቢ አይደለም፤ ምደባ ተሰጥቷቸው ሥራ ላይ ባለመገኘታቸው ደመወዛቸው መታገዱ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ክርክር መረዳት የሚቻለው ተጠሪ የማስተርስ ትምህርት ጨርሰው ሲመለሱ አመልካች ለተጠሪ የሥራ ምደባ ደብዳቤ እንደተሰጣቸው በግራ ቀኙ የታመነ መሆኑን ነው፡፡ ግራ ቀኙ የተካካዱበት ፍሬ ነገር ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2/2/6 የሥራ መደብ ትርጉም እንደተመለከተው የሥራ መደብ ማለት በአንድ የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ጊዜ እንዲሰራ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥ የሥራ ኃላፊነት እና ተግባር ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የስራ ምደባ ማለት ምደባውን

በሚሰጠው የመንግስት መስሪያቤት ውስጥ ሠራተኛው ባለው እውቀት፣ የሥራ ልምድ እና ክህሎት መሰረት በሥራ ሰአት እንዲያከናውን የሚሰጠው የሥራ ድርሻ ወይም ኃላፊነት ማለት ነው። ሠራተኛው እንዲሰራ በተመደበበት የሥራ መደብ ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ አሠሪው መሥሪያቤት ለሥራው ምቹ የሆነ እና የሠራተኛውን ደህንንነት የሚያስጠብቅ የሥራ ቦታ እና የሥራ መሳሪያ ማቅረብ እንዳለበት፤ ተገቢውን ሥልጠና መስጠት እንዳለበት እና ሌሎች ሁኔታዎችን የማሟላት ግዴታ እንዳለበት በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 65 ላይ ተመልክቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሠራተኛውም በሥራ ሰአት በሥራ መደቡ ላይ ተገኝቶ የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት እና ሌሎች ግዴታዎች ያሉበት መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 66 ላይ ተመልክቷል። ከእነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መረዳት የሚቻለው የመንግሰት መስሪያቤት ለሠራተኛው ተገቢውን የሥራ መደብ እና ለሥራ መደቡ የሚያስፈልጉ አቅርቦቶችን ማሟላት እና ሠራተኛውም በስራ ሰአት በሥራ ቦታ ላይ በመገኘት ተገቢውን ሥነ-ምግባር ጠብቆ ሥራውን የማከናወን ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። እነዚህ ከአሠሪውም ሆነ ከሠራተኛው የሚጠበቁ ግዴታዎች ከተጣሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 68 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ደመወዛቸውን የማገድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደው ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አልተገኙም በሚል ነው። ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ በሥራ ቦታቸው መገኘት ያልቻሉት በአመልካች የተሰጣቸው የሥራ መደብ በተግባር ባለመኖሩ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል። ከላይ እንደተመለከተው የተጠሪ አሠሪ ሆነው አመልካች የሥራ መደብ ለተጠሪ የመሥጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባውም በደብዳቤ ከመገለጹ በተጨማሪ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ሊሆን እንደሚገባ ግልጽ ነው። አመልካች በደብዳቤ ተጠሪን የመደበ ቢሆንም በደብዳቤ የተገለጸውን የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤት ውስጥ የሌለ ከሆነ አመልካች በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 65 ላይ የተመለከተውን ሥራ እና ሥራ ቦታ አመቻችቶ የመስጠት ግዴታውን ስላልተወጣ የተጠሪን ደመወዝ ማገዱ ህጋዊ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ተጠሪ በደብዳቤ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ በተግባር አለ ወይስ የለም የሚለው የግራ ቀኙ የክርክር ጭብጥ ተደርጎ በተገቢው ማስረጃ ከተጣራ በኋላ የተጠሪ ደመወዝ መታገዱ ተገቢ ነው አይደለም ለሚለው ምላሽ የሚያገኝ በመሆኑ በመጀመሪያ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለው ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ ሊጣራ ይገባ ነበር።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ለሶስት አመት ተኩል ተጠሪ በሥራ ቦታ ስለመገኘት አለመገኘታቸው ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ ግዴታውን አልተወጣም እንዲሁም አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አለመገኘታቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ በማቅረብ አላስረዳም በሚል የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል። በእርግጥ አመልካች ለተጠሪ በሰኔ ወር 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ምደባ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እየሰሩ መቆየት አለመቆየታቸውን የመቆጣጥር ኃላፊነት እንዳለበት አከራካሪ አይደለም። ይሁን እንጂ ላለፉት ሶስት

አመታት ተቆጣጥሮ እርምጃ አለመውሰዱ ከሶስት አመት ተኩል በኋላ ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ እስካልተገኙ እና ድርጊቱ እስከቀጠለ ድረስ እርምጃ ከመውሰድ የሚያግደው ወይም እርምጃ የመውሰድ መብቱን የሚያስቀረው አይሆንም፡፡ ተጠሪ ሥራ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ ያልተገኙበትን ምክንያት በመግለጽ የሚከራከሩ ከመሆኑ አንጻር ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በተመለከተ የታመነ ፍሬ ነገር ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 መሰረት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡

ሌላው አመልካች በሰበር ቅሬታው የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት ተጠሪ ለስር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሥራ ስንብትን በተመለከተ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የለም፡፡ አመልካችም ለተጠሪ ቅሬታ በሰጠው መልስ የተጠሪ ደመወዝ ያልተከፈለው ከሥራ በመሰናበታቸው ነው በሚል ያቀረበው ክርክር ያለም፡፡ ከስር ጅምሮ የነበረው ክርክር ከደመወዝ መታገድ ጋር ብቻ የተያያዘ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ከሥራ ስንብት ጋር ተያይዞ የተነሳው ክርክር የሚታይበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አመልካችን አሰናብቻለው የሚል ከሆነ እራሱን ችሎ ክርክር የሚደረግበት በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 246 መሰረት ግራ ቀኙ በተካካዱበት ፍሬ ነገር ማለትም ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤቱ ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰርት እንዲሁም ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ አመልካች ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ምክንያት የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ግድፈት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማረም ሲገባው አለማረሙ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176/2013 በግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209017 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ በታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 217557

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አክስዬን ማህበር- ጠበቃ ፕ/ር ጥላሁን ተሾመ እና ነ/ፈጅ አበራ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የኢትዬጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ-ነ/ፈጅ ሰለሞን ነጋሽ ቀረቡ

2ኛ. የኢትዬጵያ ብሔራዊ ባንክ- ነ/ፈጅ ታፈሰ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 28/03/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀን 01/02/2014 ዓ.ም ለባለጉዳዮች ተነቧል የተባለው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው። ክርክሩ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጣ/ገብቶ ተከራክሯል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ከሳሽ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ/ም እና በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ በማለት ጠይቋል።

ተከሳሽ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ነገር ክርክሩን አቅርቧል። ባቀረበው መቃወሚያ ተከሳሽ ለጣ/ገብ በ04/02/2013 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ቋሚ መመሪያ እስኪወጣ ድረስ በማለት የሰጠውን መመሪያ ለማብራራት የተጻፈ ደብዳቤ እንጂ አስተዳደራዊ ውሳኔ አይደለም። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከመውጣቱ በፊት የወጣ ስለሆነ አዋጁ በመመሪያው ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም። በተጨማሪም ከሳሽ ተከሳሽ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 51 መሰረት ለተከሳሽ ተቋም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ያላቀረበ ስለሆነ ከሳሽ የተከሳሽን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ተከራክሯል።

ጣ/ገብ በበኩሉ ወደክርክሩ ገብቶ ባቀረበው መቃወሚያ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ ጣ/ገብ ለተከሳሽ ለጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ሲሆን በግልባጭ ከሳሽ እንዲያውቀው ተደርጓል። ሆኖም ከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መሰረት ለተከሳሽ ምንም ቅሬታ ያላቀረበ ስለሆነ በአዋጁ መሰረት አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን አሟጦ ያልጨረሰ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ከሳሽ በአዋጁ መሰረት የአስተዳደር ውሳኔው በተወሰነ 30 ቀናት ውስጥ ክስ ማቅረብ ሲኖርበት ግዜው ካለፈ በኋላ በማቅረቡ በይርጋ ይታገዳል። እንዲሁም በራሱ 22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ በ23ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተሻረ ስለሆነ ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት ተከራክሯል።

ለመቃወሚያ ክርክሩ ከሳሽ በሰጠው መልስ መቃወሚያዎቹ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2) መሰረት የቀረቡ አይደሉም፤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ እንደሚለው ቋሚም ሆነ ግዜያዊ መመሪያ አይደለም፤ የቦርድ ሰብሳቢ መመሪያም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፤

ስልጣን ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤ እነዚህ ደብዳቤዎች የአስተዳደር መመሪያዎች እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም። መብታችን በመነካቱ ነው ፍ/ቤት የመጣነው። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ በተጻፈው ደብዳቤ መነሻ ላቀረብነው ቅሬታ ምላሽ የተሰጠን አዋጅ ቁጥር 1183/12 ከወጣ በኋላ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም ስለሆነ ይህንኑ መሰረት አድርገን ነው ክስ ያቀረብነው። በአስተዳደር ተቋም ውስጥ ያለውን መፍትሄ አሟጦ መጨረስን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በቦርድ ሰብሳቢ የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን በመግለጽ ለቦርዱ ሰብሳቢ ለራሳቸው አመልክተናል፤ በግልባጭም ለጣ/ገብ አሳውቀናል። ጣ/ገብም በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጠይቋል። ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለ በግልባጭ አሳውቆናል፤ ደብዳቤው በአድራሻ የተጻፈ ለጣ/ገብ ነው። ተከሳሽ ቅሬታ ስናቀርብ ወደ ቅሬታ ሰሚ ሂዱ ብሎ አልመራንም፤ አሁንም ቢሆን ተከሳሽ ቅሬታ ሰሚ አካል ያቋቋመ ስለመሆኑ ይፋ አላደረገም። በመሆኑም መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ እንደደረሰን በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በውሳኔው ላይ ቅሬታችንን አቅርበን ቦርዱ በቀን 04/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታችንን እንዳልተቀበለው በመግለጽ ይርጋ ጊዜውን አቋርጦታል። መብትና ጥቅም የለውም የተባለውን በተመለከተም በክሱ መሰረት ከተወሰነልን በ22ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ ደግሞ ለመወሰን የሚያስችለን ስለሆነ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም አለን በማለት ተከራክሯል።

የመቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ደብዳቤዎቹ የአስተዳደር መመሪያዎች አይደሉም እንዲሁም የአስተዳደር ውሳኔዎች አይደሉም፤ መብታችን ስለተነካ ነው ፍ/ቤት የመጣነው በማለት ለመቃወሚያው ክርክር ቢያቀርብም ከሳሽ ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም ባቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም እና 04/02/2013 ዓ.ም የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ የጠየቀ ስለሆነ ክርክሩ ከክሱ አንጻር ተገቢነት የለውም። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ

በቀረበው ቅሬታ ላይ የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል። በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተከሳሽ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ ስለመሆኑ አላከራከረም። በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ነው። አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም ከመሆኑ አንጻር በአስተዳደር ውሳኔው ላይ ቅሬታው ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ለተከሳሽ ቦርድ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን ሆኖ አልተገኘም። በዚህ መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 51 ማንኛውም የክለሳ አቤቱታ ፍ/ቤት የሚቀርበው የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ብቻ መሆኑ የተደነገገ ስለሆነ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም። በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 56(2) መሰረት ፍ/ቤት የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን የአስተዳደር ውሳኔ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ የአስተዳደር ውሳኔው እና ቅሬታው በአዋጁ በማይሸፈኑበት ሁኔታ ፍ/ቤት በቅሬታው ላይ የተሰጠውን ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ የአስተዳደር ውሳኔውን ማጽናት ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር አይችልም። በመሆኑም ሌሎች መቃወሚያዎችን መመርመር ሳያስፈልግ የቀረበውን የክለሳ አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 ስር የማይሸፈን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።.....

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 28/03/2013 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ በተሰጠው ብይን ተፈፀሙ የሚላቸውን የህግ ስህተቶች ዘርዝሮ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ፍሬ ነገር ክርክር አላግባብ አዛብቶ በመረዳት እና የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጁን ተፈጻሚነት በተመለከተ የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ብይኑ እንዲሻርና ስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬነገሩ በመግባት ክርክሩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ እንዲወሰንልን በማለት ቅሬታውን አቅርቧል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ስር አይሸፈንም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

1ኛ ተጠሪ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ክርክሩን አጠናክሮ የአስተዳደር ሥነ ሥርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከ11 ወራት በኋላ በወጣ ህግ ስለማይዳኝ እና ከአዋጁ መውጣት በፊት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል።

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በቀን 29/07/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የስር ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታው በአዋጁ የማይሸፈን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይን ትክክለኛና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል። ይህ ታልፎ ብይኑ የሚሻር ከሆነ ግን የስር ፍ/ቤት ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመታዘዙ በፊት በተጠሪዎች በኩል በተነሱት ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን እንዲሰጥባቸው እንዲታዘዝ በማለት ጠይቋል። አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል። እንደመረመርነው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አይሸፈንም ፍርድ ቤቱም የክለሳ አቤቱታውን ለመመልከት ስልጣን የለውም በማለት ብይን የሰጠው በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለቀረበው ቅሬታ የተሰጠ ምላሽ መሆኑን ተገንዝበ፤ ነገር ግን በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተጻፈ በመሆኑና በዚህ ደብዳቤ ቅር በመሰኘት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ቦርድ ሰብሳቢ ቅሬታ ያቀረበው በ26/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1183/12 የወጣው ደግሞ መጋቢት 29/2012 ዓ.ም በመሆኑ ለቦርዱ ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 የሚሸፈን

አይደለም፤ የአስተዳደር ውሳኔውና በአስተዳደር ውሳኔው ላይ የቀረበው ቅሬታ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 በማይሸፈንበት ሁኔታ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽ ብቻ መሰረት በማድረግ ክለሳ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም በሚል ነው።

በመሰረቱ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ከወጣበት ምክንያት አንዱ የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን እና ሥነ ሥርዓት በመደንገግ እንዲሁም በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

"የአስተዳደር ውሳኔ" ማለት ደግሞ የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2(3) ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል። በእንዲህ አይነት የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው ውሳኔው በከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 48(2) እና 49(1) ስር ተመልክቷል። ስለሆነም ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአስተዳደር ተቋሙ በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ በሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ጥቅሙ የተነካበት ሰው የክለሳ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል መደንገጉን ሲሆን ከዚህ በቀር የአስተዳደር ውሳኔው የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከተሰጠ ውሳኔ ጋር በተያያዘ በመሆኑ የክለሳ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም እንዲሁም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስልጣን አይኖረውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም።

በ1952 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለ አስተዳደር ክፍሎች በሚደነግገው አንቀጽ ሶስት ምዕራፍ አንድ ቁጥር 401(1) እና 402(1) ሥር ከተመለከተው ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የአስተዳደር አካላት በህግ የታወቀላቸው የተግባር ስልጣን ከሚዘረጋበት ውጭ ወይም በህጉ የተገደዱትን ሁኔታዎች ወይም ፎርም ባለመከተል የሚፈጽሟቸው ሥራዎች ፈራሾች ሲሆኑ ይህን ፈራሽነት ማንኛውም ባለጉዳይ ሁሉ ሊጠይቅ ይችላል። ስለሆነም አስተዳደሩ በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ ሲወስን ወይም በህግ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ወይም የተዘረጋውን ስርዓት ባለመከተል ወስኖ

ሲገኝ በአስተዳደሩ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔው በፍርድ ፈራሽ እንዲሆን ሊወሰን እንደሚችል አስቀድሞም ቢሆን በፍትሐ ብሔር ህጉ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው።

ከዚህም ሌላ አመልካች በፅሁፍ ባቀረበው የክለሳ የዳኝነት ጥያቄ ላይ እንዲሁም በተጠሪዎች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተከትሎ ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ወጥነት አለመኖሩን በማንሳት የስር ፍርድ ቤት የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎችም ይህን በመከራከሪያነት አያይዘው ማንሳታቸውን ተመልክተናል። ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ስርዓት በተመለከተ የክለሳ ስነ ስርዓት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 58 ተደንግጓል። ስሆነም ለክለሳ ለክርክሩ በአዋጁ የተመለከቱ ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች የሚፈፀሙበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚመራው በፍትሐ ብሐር ሥነ ሥርዓት ህጉ አግባብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ከሳሽ በህጉ የተፈቀደን መፍትሄ ከፍርድ ቤቱ ለማግኘት በፅሁፍ በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ ይገባዋል። በዚህ መልኩ በጽሁፍ ግልጽ የዳኝነት ጥያቄውን ካቀረበ በኃላ መቃወሚያን ለመወሰንም ይሁን በፍሬ ነገር ላይ በችሎት የሚያቀርብ ክርክር መሰረታዊ አላማው በጽሁፍ ያቀረበውን ክርክር ለማብራራት እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ለማስተናገድ አይደለም። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 83፣ 222፣ 224፣ 234፣ 235፣ 236፣ 241፣ 244፣ 245 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ የኢትዬጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥቅሙን የሚነካና የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 48 መሰረት ውሳኔው እንዲከለስ ለመጠየቅ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ክርክሩ ሊመራና ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባውም ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው።

ስለሆነም ግራቀኙ የየበኩላቸውን ክርክር ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ የተጻፈው ደብዳቤ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን እንዲሁም በቀን 04/02/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ በቀን 19/02/2012 ዓ.ም በተወሰነው የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበው ቅሬታ ላይ

የሰጠው ምላሽ መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል በሚል ለያይቶ መወሰኑ በግልፅ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እና ከፍሲል የጠቀስናቸውን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘት የተከተለ አይደለም።

በአጠቃላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በግልጽ በጽሁፍ የቀረበውን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ በቀረበ ቅሬታ ላይ የተሰጠ ምላሽን ብቻ መሰረት በማድረግ የቀረበ አቤቱታ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ፤ ይህን ተከትሎም መሰል የክለሳ አቤቱታ ማቅረብ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፤ አመልካች ያቀረበው የክለሳ አቤቱታ በአዋጁ የሚሸፈን አይደለም፤ እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ብይን የሚነቀፍ ነው። የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከእነሙሉ ይዘቱ በአግባቡ ሳይጤን፤ ከፍሲል ከተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከክርክሩ ውጪ በመውጣት የተሰጠ ብይን በመሆኑም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 262067 በቀን 05/01/2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ቀሪ ክርክር ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 341/1/ መሰረት መልሰናል። የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው።
3. ከስር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት አግባብ ይመለስ።
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 217836

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመካው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ስንታየሁ የግል 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ጠበቃ ንጉሴ አበበ ቀርበዋል

ተጠሪዎች-

1. አቶ ይርጋ ባይችሉ
2. ወ/ሪት ትሪንጎ ካሳሁን
3. ወ/ሪት ሙሉሰዉ ጌታነህ
4. አቶ ዳኛቸዉ አብጥ
5. አቶ ዘማርያም ጋርዶ
6. አቶ ተሾመ ሽመልስ
7. አቶ ልጃለም አለህኝ
8. ወ/ሮ አለምጸሐይ በየነ

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በአመልካች ትምህርት ቤት በመምህርነት ተቀጥረዉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመስራት ላይ እያሉ ከነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ወደ ትምህርት ቤቱ ግቢ እንዳይገቡ በመከልከልና ወደ ፖሊስ ሄዳችሁ ከሳችሁኛል በሚል ምክንያትም ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸዉ ከስራ እንዲሰናበቱ ያደረገበት አግባብ ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰዉ አመልካች ወደ ስራ እንዲመልሳቸዉ፣ ወደ ስራ የማይመለሱበት ምክንያት ካለም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸዉ እንዲሁም ለስራ ግብርና ለጡረታ በሚል ከደመወዛቸዉ ሲቀንስ የነበረዉን ለሚመለከታቸዉ አካላት ገቢ እንዲያደርግ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገ የቅጥር ዉል ከመስከረም እስከ ሰኔ የሚቆይ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ፡፡ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ በወጣዉ አስቸኳይ አዋጅ ምክንያት ከመጋቢት 2012 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸዉ ለመምህራን የሚከፈል ደመወዝ ባለመኖሩ ትምህርት ቢሮ ባወጣዉ መመሪያ መሠረት አመልካች 75 ከመቶ ከወላጆች ሰብስቦ ለመምህራንና ሠራተኞች እንዲከፈል ጥረት ያደረገ ቢሆንም ከአመልካች ድርጅት የግል ገንዘብ ተጨምሮበት እስከ ሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ለተጠሪዎች ሙሉ ደመወዝ የከፈለ ሲሆን በአቅም ችግር ምክንያት አመልካች የሐምሌ እና ነሐሴ ወር ደመወዝ ግን ለመክፈል አልቻለም፡፡ የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ዉሉን ማቋረጡ አዋጁን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ የስንብት፣ ዉዝፍ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን አስመልክቶ የቀረበ የክፍያ ጥያቄ ያላግባብ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተጠሪዎች አዲስ ዉል እንዲያደርጉ ከአመልካች የቀረበላቸዉን ጥያቄ ባለመቀበል ስራ ለመጀመር ፍቃደኛ ባለመሆናቸዉ ምክንያት መሆኑን እና አመልካች ለተጠሪዎች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ደመወዝ መክፈል ያልቻለዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በመረጋገጡ ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ደመወዝ ባለመክፈሉ መሆኑን ጠቅሰዉ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በህገ ወጥ መንገድ ነዉ በማለት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች ደመወዝ በወቅቱ መክፈል ያልቻለዉ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤት በመዘጋቱ እና የተማሪዎች ወላጆችም ክፍያ በማቋረጣቸዉ ባጋጠመዉ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል የመዘግየት ቅጣትን አስመልክቶ የተጠየቀዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ የትራንስፖርት እና የቤት አበልን ጨምሮ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤትም መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ከአመልካች ድርጅት የስራ ባህርይ አንፃር ሲታይ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የስራ ዉል በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 10 እና 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር በመሆኑ የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ በማለት አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ የስራ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ እያለ አመልካች የሐምሌ እና የነሐሴ ወር

ደመወዝ አለመክፈሉ እና ተጠሪዎች ዉል በአዲስ መልክ ያዙ በማለት አመልካች ለዉሉ መቋረጥ ምክንያት ሆኖ እያለ ዉሉ የተቋረጠዉ በህጋዊ መንገድ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ የስራ ዉሉ ለመቋረጡ መነሻ ምክንያቱ የአመልካች አነሳሽነት ብቻ ሳይሆን የተጠሪዎችም አነሳሽነት እንዳለበት ጠቅሶ አመልካች የስራ ስንብት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ካለ በኋላ አመልካች ለተጠሪዎች ካሳ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ለእያንዳቸዉ የአንድ ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ተጠሪዎች የ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ዉል እንዲይዙ ተጠይቀዉ የሐምሌ እና የነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ደመወዝ ካልተከፈለን ዉል አንይዘም፤ አናስተምርም በማለት ዉሉን በእራሳቸዉ አነሳሽነት አቋርጠዉ እያለ ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች የሁለት ወር ደመወዝ አመልካች አልከፍልም እንዳለ በማስመሰል የስራ ዉሉ በአመልካች ጉድለት ተቋርጧል በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ እንዲሁም የስራ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ እያለ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነዉ በሚል አመልካች ካሳ እንዲከፍል በማለት መወሰኑ እንዲሁም ካሳዉ ያልተጣራ ደመወዝ መነሻ ማድረግ ሲገባዉ የቤት ኪራይ፣ አበል እና ትራንስፖርትን ጨምሮ በማስላት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የስራ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንደሆነ ወስዶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጋራ ባቀረቡት መልስ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሁለት ወር ደመወዝ በተጨማሪ አመልካች ካሳ እና የደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት የአንድ ወር ደመወዝ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ሲወስን መሠረት ያደረገዉ በግራ ቀኝ መካከል የነበረዉ የስራ ቅጥር ዉል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሆኖ ሳለ አመልካች ዉሉ የሚቆየዉ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነዉ በሚል ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ ባለመክፈሉ እና ተጠሪዎች የስራ ዉል በአዲስ መልኩ ያዙ በማለት ለስራ ዉሉ መቋረጥ ምክንያት መሆኑን እና ይህም ድርጊቱ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ተከትሎ የወጣዉን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ጭምር ያላገናዘበ በመሆኑ ዉሉ

የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስለመሆኑ የወሳኔው ግልባጭ ያሳያል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን በመቃወም የሰረበለትን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ትዕዛዝ የሰጠው ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። ይህ ከሆነ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በትዕዛዝ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል።

እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ውሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነው። መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው? ወይም አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው መቼ ነው? የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠው ውሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠውም ነበር። ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ማድረግን አንዱ ዓላማው ያደረገው ይህ አዋጅ ካካተታቸው አዳዲስ ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነው። በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነው።

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበው ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ

ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ውሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘዉ በክልሉ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0149107 ላይ ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 108073 ላይ ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. የሰበር አጣሪ ችሎት ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ.መ.ቁ. 217855
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ዐሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ሥልጣን ወ/ሚካኤል

2. ወ/ሮ ጠጅቱ ሁንዴ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኡሜጋ ተረዳ

2. አቶ ሸዋንግዛው ኡሜጋ

3. አቶ በለጠ ኡሜጋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 223936 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 193612 ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ይዘታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች በቅደም ተከተል 1ኛ

፣2ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉት ወ/ሪት ሙሉ ወርቅ ኡሜጋ እና ወ/ሮ ሸዋዬ ሰይድ በቅደም ተከተል ደግሞ 3ኛ እና 5ኛ ተከሻሾች በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ አስኮ ተብሎ ለሚጠራው ሰፈር የተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ይዞታ የሚያሳየው 275 ካ.ሜ ሲሆን የአመልካቾች ደግሞ 152 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ ነው፤ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች በቤት ቁጥር 378 ካርታ ላይ ካለው 275 ካ.ሜ ይዞታ ተጨማሪ ከአመልካቾች ይዞታ ስር የሚገኝ 35 ካ.ሜ አላግባብ የያዙ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ከካርታቸው ውጪ የያዙትን ቦታ በመሃንዲስ ተለክቶ አለግባብ የወሰዱት ተረጋግጦ እንዲለቁ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁን ተጠሪዎች እና የስር 3ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ 35 ካ.ሜ በመግባት አለመያዛቸውን በመግለጽ የአመልካቾች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎችን በብይን ውድቅ ያደረገ ሲሆን በፍሬ ነገር ላይ ደግሞ የኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊዜ አገልግሎት ኘሮጀክት ዴስክ ስለጉዳዩ አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥበት አድርጐ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ጽ/ቤት በሴሪ.ቁ.048821 በካርታ ቁጥር 014/ወዝ01/924/1757/1 ለ1ኛ አመልካች 152 ካ.ሜ በሆነው ይዞታ ላይ የሰጠው ካርታ ላይ ተቃራኒ ማስረጃ አልቀረበም፤ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ወደ አመልካቾች ይዞታ በስተደቡብ አቅጣጫ 26 ካ.ሜ የሚሆን ቦታ አጥረው እንደያዙ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፤ አመልካቾች ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት ከተጠሪዎች እና ከስር ተከሳሾች በግዥ ስለማግኘታቸው አልተካደም፤ ግራ ቀኙ የያዙት ይዞታ በካርታ ላይ ካለው ያነሰ እንደሆነ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፤ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ከይዞታቸው ላይ 82 ካ.ሜ ያህል እንደተቀነሰ የሚመለከው አካል ያመነ በመሆኑ በምን አግባብ ወደማን ይዞታ ተቀላቅሎ ተቀነሰብን የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ክስ መስርቶ ከማስወሰን በቀር ይህንን መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለው መሆኑን፣ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች በስተደቡብ በኩል አጥረው የያዙትን 26 ካ.ሜ አጥሩን አንስተው ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ በማለት ተወስኗል።

ተጠሪዎች በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማለታቸውን እና አመልካቾች ደግሞ በወጪና ኪሣራ ላይ መስቀልኛ ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም መዝገቡን አጣምሮ ተመልክቶ ስለጉዳዩ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የመሬት የይዞታ አስተዳደር ጉዳዩን አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥ ካደገ በኋላ ተጠሪዎች በተጨባጭ የያዙት ይዞታ በካርታ ከተሰጣቸው ይዞታ ያነሰ መሆኑ ተረጋግጧል፤ በተጠሪዎች ታጥረው የሚገኘው ይዞታ በካርታ ለአመልካቾች የተሰጠ እና የካርታ መደራረብ መኖሩ ተረጋግጦ ባለበት ተጠሪዎች የአመልካቾችን ይዞታ ገፍተው ይዘዋል የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በስተደቡብ በኩል አጥረው የያዙት 26 ካ.ሜ ቦታ ለአመልካቾች ለቀው እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሰረት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያላደረገ እና ተጠሪዎች የአመልካቾችን ቦታ ገፍተው መያዝ አለመያዛቸው በአግባቡ ሳያጣራ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሸሮ ተጠሪዎች ለቀው የሚያስረክቡት ይዞታ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የተሻረ በመሆኑ የአመልካቾች በወጪና ኪሣራ ላይ አቅርበውት የነበረው መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

አመልካቾች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሣኔውን አጽንቶታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካቾች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክፍለ ከተማው ከሰጠው ማስረጃ ውጪ የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 22 መ.ቁ. 122595 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስ ነው፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ ከተደረገው ክርክር ማስረጃ ምንም አንኳን በግራ ቀኙ ካርታ ላይ መደራረብ የሚታይ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ባጣሩት መሰረት የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርቶ ያልያዘውን ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ አልፈው በመግባት መያዛቸው ተረጋግጦ ባለበት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካቾች ሊለቅ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሲሸር ይህ ውሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተቀባይነት ያገኘበት አግባብ ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪዎች መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፦ የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ተጠሪዎች ወሰን ገፍተው የአመልካቾችን ይዞታ ይዘዋል የሚል ምላሽ አልሰጠም፤ ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ በስተደቡብ በኩል 26 ካ.ሜ አልፈን አለመያዛችን ተረጋግጧል፤ አመልካቾች በተጠሪዎች እጅ እና ይዞታ ስር በሚገኘው መሬት ከህግ እና ደንብ ውጪ የተሰራ ካርታ ይዘው መገኘታቸው ብቻ የንብረቱ ባለቤት እንደማያደርጋቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 9 መ.ቁ. 36320 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ የተጠሪዎች ካርታ ከአመልካቾች ካርታ ቀድሞ የተሰጠ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት የተጠሪዎች ካርታ በአመልካቾች ካርታ ላይ የበላይነት አለው፤ ተጠሪዎች አሁን በተጨባጭ ከያዝነው የይዞታ ስፋት በካርታ ላይ ከተመዘገበው የይዞታ ስፋት ያነሰ ስለመሆኑ በባለሙያ ተረጋግጧል፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ከተጠረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጡ ውሣኔዎች እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ቀርቦ የነበረው ክርክር ተጠሪዎች ከይዞታችን ያለአግባብ 35 ካ.ሜ. ገፍተው የያዙ በመሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልን የሚል ነው። ተጠሪዎች በበኩላቸው ገፍተው የያዙት ይዞታ እንደሌለ በመግለጽ ክሱ ውድቅ ይደረግልን ሲሉ መከራከራቸውን ተመልክተናል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አስተዳደሩን ጠይቆ ባገኘው መረጃ መሠረት የካርታ መደራረብ ያለ መሆኑ ተገልጸለታል።

ከአጠቃላይ ክርክሩ ይዘት የሚዋሰኑ ይዞታዎች መካከል ባለ ይዞታ ክርክር ምክንያት የካርታ መደራረብ መኖሩ ከተረጋገጠ ከካርታ መደራረብ አኳያ ጉዳዩ ተመርምሮ ሊወሰን የሚችልበትን አግባብ በስር ፍ/ቤቶች በአግባቡ ተመርምሮ የመወሰኑን አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ነው።

አንድ የፍትሐብሄር ክርክር የሚመራው እና ጭብጡም የሚመሰረተው ከሣሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን በክስ አቤቱታው ላይ የገለፃቸውን ፍሬ ነገሮች እና ተከሣሽ የሆነው ወገን በመከላከያ መልሱ ላይ የገለፃቸውን ፍሬ ነገሮች ክሱን ለመከላከል ያስችለኛል በማለት በማለት ያቀረበውን ማስረጃዎችን እንዲሁም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 241መሠረት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሲሰማ ያገኘውን ፍሬ ጉዳዮችን በማገናዘብ ስለመሆኑ ስለጭብጥ አመሠራረት የሚደነግጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁ. 246-248 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ከይዞታችን ውስጥ 35 ካ.ሜ. የሆነውን ተጠሪዎች ገፍተው ይዘውብናል በሚል የሚከራከሩ ሲሆን በስር ፍ/ቤት በተደረገ ማጣራት በደቡብ በኩል ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ 26 ካ.ሜ. ገፍተው ይዘዋል በሚል ተረጋግጧል። ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ባደረገው ማጣራት ደግሞ የካርታ መደራረብ መኖሩ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል። በሁለቱም ፍ/ቤቶች በተደረገው ማጣራት ግራ ቀኙ ይዘው የሚገኙት ይዞታ ጥርት ባለመልኩ በያዙት ካርታ ይዞታ መጠን ይዞታውን ይዘው የሚገኙ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አይደለም።

የካርታ መደራረብ ያለ በሆነ ጊዜ ካርታው እንዴት አንዱ በአንዱ ይዞታ ላይ ተደርቦ እንደተሰጠ፣ ለምን መደራረቡ እንደተፈጠረ፣ በይዞታው ተፈጥሮ አኳያ የማን ካርታ የማንኛው ይዞታ ላይ እንደተደረበ እና እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል ተጣርቶ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ካርታ መደራረብ ስላለ ብቻ አንዱ አንዱን ገፍቶ ይዟል ሊባል የማይቻል ነው በሚል

ውሣኔውን መሻሩና ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ሊሻር የሚገባው ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች የፈፀሙበትን ስህተት ማረም ሲገባው ማጽናቱ ተገቢ አይደለም ብለን ተከታዩን በአብላጫ ድምፅ ወስነናል።

<u>ውሣኔ</u>

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 193612 ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 223936 በ24/06/12 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 78580 በ22/02/2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሸሯል።

2) የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሣኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ክላይ በፍርድ ሃተታው ተገለንው መሠረት የካርታ መደራረቡን ምክንያት ካርታ በመደረቡ ሊሰጥ የሚችለውን ውሣኔ የሚመለከተው አካል ተገቢ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ እና ግራ ቀኙ አስቀድሞ ያቀረቡትን ማስረጃ አብሮ በመመርመርና በማጣራት ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲወስን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል።

3) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

4) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

<u>መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።</u>

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>የሃሣብ ልዩነት</u>

እኛ በሶስተኛ እና አራተኛው ተራ ቁጥር ስማችን የተጠቀሰው የችሎቱ ዳኞች አብላጫው ድምፅ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለስ በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማን በመሆኑ ያለንን የልዩነት ሀሳብ እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኽው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍስ/ስ/ህ/ቁ 136፤ 137.272 እና 345 ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲያቀርብ መታዘዝ አለበት፡፡ / በሰበር መዝገብ ቁጥር 72980 እና 22603 በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይመለከታል፡፡/ በዚህ አግባብ አከራካሪው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ሊመለስ የሚችለው ከላይ እንደተመለከተው ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር የተያዙና ሊያዙ የሚገባቸው ጭብጦች በአግባቡ ተጣርተው ያልተወሰኑ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ግራቀኙ ከሚከራከሩበት ይዞታ አንፃር የግራ ቀኙን ካርታ በተመለከተ መደራረብ መኖር አለመኖሩ በአግባቡ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሲሆን የኮ/ቀ/ክ/ከ/መሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት በ 05/05/2012 ዓ.ም ጉዳዩን በይግባኝ ለተመለከተው ሌፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላከው ማብራሪያ የግራቀኙ ካርታ መደራረብ ያለው መሆኑን የተደራረበውም 68 ካሜ መሆኑን ማረጋገጡን የገለፀ ሲሆን መደረቡ የተፈጠረውም የአመልካች ካርታ ሲሰራ በ 1997 ዓ.ም አየር ካርታ ላይ የሚታየውን ቤት መሰረት በማድረግ በሽንሻኖ ማስተካከያ በመሆኑና በመስክ ልኬት ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማረጋገጫ ባለመኖሩ መሆኑን በዚህ ምክንያትም በተጠሪዎችም ታጥሮ የሚገኘው ይዞታ በአመልካቾች ካርታ ውስጥ ተካትቶ ሊሰጥ መቻሉን የገለፀ ሲሆን የኮ/ቀ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አ/ፕ/ዴስክ በ22/09/2010 ዓ.ም ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ምላሽ መደራረብ የተፈጠረው የመስክ ልኬት ሳይደረግ በጂአይ ኤስ አየር ካርታን መሰረት በማድረግ ካርታው በመዘጋጀቱ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ የካርታ መደራረቡ የተፈጠረው ካርታው የተሰጠው መሬቱን በአግባቡ ለመያዙ ሳያረጋግጥ ሂደቱ በመፈፀሙ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ፅ/ቤት በተጨማሪም በሰጠው ምላሽ የተጠሪዎች ካርታ በ 18/12/08 ዓ.ም የአመልካቾች ካርታ በ 11/06/2008 ዓ.ም ከመዘጋጀቱ 6 ወር ያህል በፊት የተዘጋጀ መሆኑን በማመልከት ቅድሚያ የሚሰጠው ቀድሞ መብት ለተፈጠረለት ሰው መሆኑን በሚያመለክት መልኩ መልስ መስጠቱን የስር ፍርድቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

በመሠረቱ የካርታ መደራረብ ሲፈጠር ክፍተቱን የሚሞላ ህግ ባለመኖሩ በአሰራር የዳበረው መሬቱን ለያዘው ሰው ወይም ቀድሞ መብት ለተፈጠረለት ሰው ቅድሚያ መስጠት ተቋማቱ በአማራጭነት የሚከተሏቸው ምርጫዎች ሲሆኑ አሁን በያዝነው ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተው ካርታው ሲዘጋጅ አከራካሪው ይዞታ በተጠሪዎች እጅ መኖሩ እንዲሁም አስቀድሞ መብት የተፈጠረውም ለተጠሪዎች

መሆኑ በአሰራር በዳበሩት ሁለቱም አማራጮች ቢሆን ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዘታ ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ከላይ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱን በመውሰድ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ለአመልከቻ ካቾች ለቀው የሚያስረክቡት ይዞታ የለም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ከውጤት አንፃር ሊፀና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቻችን በሃሳብ ተለይተናል።

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 217928
ግንቦት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. *መምህርት ትዕግስት ተቀጸል*

2. *መምህርት መሬም አሚን*

3. *መምህርት ሻይማ ሞሃመድ*

4. *መምህር አብዱላዚዝ አህመድ*

5. *መምህር ፋሲካ ዘውዱ*

ተጠሪ ፡- የመን ኮሚኒቲ ትምሕርት ቤት፡- ጠበቃ መባረክ አብዱሰላም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሥራ ውል መቋረጡ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ትምሕርት ቤት ተቀጥረን ስንሰራ ደመወዝ በማቋረጡ በመዝገብ ቁጥር 113179 ክስ አቅርበን ደመወዝ እንዲከፈለ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተወስኗል፡፡ በ2013 ዓም ስራ እንጀምራለን ብለን ስንጠብቅ ትምሕርት ቤቱን በመዝጋት በሕገ-ወጥ መልኩ ያሰናበተን በመሆኑ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ያልተከፈለ የስድስት ወር ደመወዝ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ በቂ ተማሪዎች ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ ትምሕርት ቤቱ ስለተዘጋ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ በሌለበት ደመወዝ አስወሰኑ እንጂ በክሱ የተጠቀሰው የደመወዝ መጠን ያህል አይከፈላቸውም ነበር፤ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ አይደሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116531 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት መርካቶ የሚገኘው የተጠሪ ትምሕርት ቤት ቅርንጫፍ መዘጋቱ በግራቀኙ ምስክሮች የተረጋገጠ ነው፡፡ ትምሕርት ሚኒስቴርም ትምሕርት ቤቱ አገልገሎት ማቆሙን ገልጿል፡፡ አመልካቾች የሰሩት እስከ የካቲት ወር 2012 ዓ/ም ድረስ ነው፡፡ ተጠሪ በፋይናንስ ችግር፣ በኮቪድ ወረሽኝ ምክንያትና ግንቡ በመፍረሱ ምክንያት መርካቶ የሚገኘው ቅርንጫፍ የሚገኘውን ትምሕርት ቤት መዝጋቱን አስረድቷል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24(4) መሠረት ሕጋዊ ነው፡፡ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ አይደሉም፡፡ አመልካቾች ላልተሰራ ሥራ ደመወዝ መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ከገቢዎች ጽ/ቤት በቀረበው የደመወዝ መጠን መሠረት ተሰልቶ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በማከራከር ትምሕርት ቤቱ መዘጋት ስለታመነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው መባሉ ተገቢ ነው፡፡ 3ኛ አመልካች ሠራተኛ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ክፍያዎች ይገባቸዋል፡፡ የደመወዝ መጠንን በተመለከተ ከ1ኛ-3ኛ አመልካቾች ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 113179 በተወሰነው መሰረት የ1ኛ አመልካች በወር ብር 3,500.00፣ 2ኛ አመልካች ብር 2,586.00፣ 3ኛ አመልካች ብር 5,050.00፣ 4ኛ አመልካች በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠውን ብር 3,150.00 እና 5ኛ አመልካች ብር 2,935.70 ሂሳብ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ ሁለት ቅርንጫፍ አለው፣ መዝጋቱን ለሚመለከተው አካል ያላሳወቀ በመሆኑ በሕጋዊ መንገድ እንደተዘጋ ሊቆጠር አይገባም፡፡ ቀደም ሲል ደመወዘ እንዲከፈለን ክስ አቅርበን እስከ ግንቦት 2012 ዓ/ም ድረስ እንዲከፈለን ተወስኖ እያለ ውሳኔው ሳይለወጥ አሁን በተያዘው ጉዳይ በየካቲት 2012 ዓ/ም ነው የተዘጋው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሥርዓቱን የጠበቀ ስንብት ሆነ ቅነሳ አልተደረገም፡፡ የኮቪድ ስርጭት እያለ የሥራ ውል ማቋረጥ አይቻልም፡፡ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፡፡ የደመወዝ መጠን አመልካቾች ቀደም ሲል በሌላ መዝገብ አስወሰነን እያለ የ4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች የደመወዝ መጠን ከውሳኔው ውጭ በሌላ ማስረጃ ተመስርቶ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ያልተከፈለ ደመወዝ ሊከፈለን ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ተጠሪ ሥራው ያቆመበትን ምክንያት ለትምህርት ሚኒስቴር ካለማሳወቁና የኮቪድ ወረሽኝ የነበረበት ከመሆኑ አኳያ ስንብቱ ሕጋዊ ነው መባሉና ክፍያዎች የተወሰነበት አግባብነትን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ባቀረበው መልስ ተማሪ ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንዱ ቅርንጫፍ ተዘግቷል። የኮቪድ ወረሽኝ ከመከሰቱ በፊት ታህሳስ 2012 ዓ/ም ላይ ነው ትምሕርት ቤቱ የተዘጋው። ስንብቱ ሕጋዊ ነው። ላልተሰራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብሏል። አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካቾች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ትምሕርት ቤት ተቀጥረን ነበር፣ በ2013 ዓም ስራ እንጀምራለን ብለን ስንጠብቅ ትምሕርት ቤቱን በመዝጋት በሕገ-ወጥ መልኩ ያሰናበተን በመሆኑ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ያልተከፈለ የስድስት ወር ደመወዝ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈለን የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በቂ ተማሪዎች ባለመገኘቱና ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ ትምሕርት ቤቱ ስለተዘጋ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል። በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል። የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል። የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል። ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል።

አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ሆነ ተጠሪም እንዳመነው አመልካቾች የሚያስተምሩበት ትምሕርት ቤቱ መዘጋቱ አከራካሪ አይደለም። ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ተጠሪ ከአንድ በላይ ቅርንጫፍ ያለው ሲሆን የተዘጋውም ተጠሪ ድርጅት ሳይሆን አመልካቾች የሚያስተምሩበት የነበረው መርካቶ የሚገኘው ቅርንጫፍ ነው። ስለሆነም ተጠሪ ድርጅት ለዘለቄታው ያልተዘጋ በመሆኑ ለጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 24(4) ተፈጻሚነት የለውም። የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት መርካቶ የሚገኘው የተጠሪ ትምሕርት ቤት ቅርንጫፍ በፋይናንስ ችግር፣ ግንብ በመፍረስ

ምክንያት መዝጋቱ ስለመረጋገጡ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይሕም ሠራተኞች የተሰማሩባቸው ሥራዎች በከፊል ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቂታው የሚያስቆም የሥራ ውል መቋረጥ የሚያስከትል ሁኔታ መከሰቱን ስለሚያረጋግጥ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ቅነሳው ሥርዓቱን የጠበቀ አይደለም ያሉ ሲሆን ክስ ሲያቀርቡ ቅነሳ መደረጉን መሠረት አድርገው ያልተከራከሩ ከመሆኑም በላይ ቅነሳ ለማለት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 29(1) የተመለከተው መስፈርት ስለመሟላቱ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች (የሥራ ውላቸው የተቋረጠው የሠራተኞች ቁጥር ከአጠቃላይ የተጠሪ ድርጅት ሠራተኛ ብዛት አንጻር ምን ያህል እንደሆነ) በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርበው ያላረጋገጡ በመሆኑ ክርክሩ በዚህ ፍርድ ቤት ደረጃ አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የኮቪድ 19 ወረሽኝ በተከሰተበት ሁኔታ ከነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከወጣው ሕግ ተጠሪ የሥራ ውል ለማቋረጥ መብት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው የኮቪድ 19 ወረሽኝ አስመልክቶ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከመታወጁ በፊት ከየካቲት ወር 2012 ዓ/ም ጀምሮ የተጠሪ ትምሕርት ቤት የተዘጋ በመሆኑና የኮቪድ 19 ወረሽኝ ከተከሰተ በኋላ ትምሕርት ቤቱ የተዘጋ ቢሆን እንኳን ሥራው በሌለበት ሁኔታ አሠሪው ሠራተኞችን ይዞ እንዲቀጥል ሕጉ እንደሚያስገደድ ሆኖ ሊተረጎም ስለማይገባ የሥራ ስንብት ሕጋዊ ነው መባሉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

በሌላ በኩል በሥር ፍርድ ቤት ለተወሰኑ ክፍያዎች የደመወዝ መጠን አስመልክቶ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ከ1ኛ - 3ኛ አመልካቾች ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 113179 በነበራቸው ክርክር ለውሳኔ መሠረት የሆነውን የደመወዘን መጠን ሲቀበል የ4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን የደመወዝ መጠን የቀደመውን ውሳኔ ሳይሆን በሌሎች ማስረጃዎች አረጋግጦ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበው የሰበር አቤቱታ ለመመርመር የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነው አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው የጠቀሱት የመዝገብ ቁጥር 113179 ሲሆን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የሚገኘውም በዚሁ መዝገብ ቁጥር ከ1ኛ-3ኛ ያሉት አመልካቾች ነሀሴ 29 ቀን 2012 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ 4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች ከዚህ ክርክር በፊት ከተጠሪ ጋር ሌላ ክርክር ያደረጉ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበ ውሳኔ ግልባጭ ባለመኖሩ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ሌሎች ማስረጃዎች መሠረት አድርጎ የደመወዘን መጠኑ ላይ የሠጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 250742 ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም